አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና

የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የሐረሪ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች

ገላጭ- ጥናት

በ

ገነት ሽኩር

ጥቅምት 2005 ዓ.ም

# የሐረሪ ብሔረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች

## ገላጭ- ጥናት

አዲስ  አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ለጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር የኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ገነት ሽኩር

ጥቅምት 2005 ዓ.ም

# የሐረሪ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች

## ገላጭ- ጥናት

በ

## ገነት ሽኩር

ጥቅምት 2005 ዓ.ም

## የፈተና ቦርድ አባላት


| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
| --- | --- |
| ፈቃደ አዘዘ (ዶ/ር)________________ | ________________ |
| ________________ | ________________ |

| የፈታኝ ስም | ፊርማ |
| --- | --- |
| አቶ ዘሪሁን አስፋው | ________________ |
| አቶ አህመድ ዘከሪያ | ________________ |




ጀጎል እና በሮቿ

# Location map of Harari National Regional State



# ምስጋና

ለአማካሪዬ ለዶ/ር ፈቃደ አዘዘ በጥናቴ ወቅት ላደረገልኝ እገዛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ከጅማሬው እስከ ፍፃሜ ድረስ ከኔ ጋር ብዙ ለለፋው ለባለቤቴ ለዳንኤል ሰልፉ የማቀርበው ምስጋና ያንስበታል፡፡ አይዞሽ በርቺ እያሉ ላበረታቱኝ ልጆቼለቲቶ ዳንኤል እና ለምስጋና ዳንኤል ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ ለመምህሬ ለአቶ ዘሪሁን አስፋው በጥናቴ ወቅት ላደረጉልኝእገዛ ከልቤ አመሰግናለሁ፡፡አቶ ዋልተንጉስ መኮንን የንድፈ ሃሳባዊ መፅሀፎችን በማዋስ፣ ለማቀርብለት የተለያዩ ጥያቄዎች ሳይሰለች ላደረገልኝ ቀና እርዳታ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

በመስክ ስራዬ ላይ የተሟላ መረጃ እንዳገኝ ለረዱኝ ለአቶ ጃሚ ኡመር፣ ለአቶ ያሬድ ለማ ለመረጃ አቀባዮቼ ወ/ሮ ሰፊያ አብራሒም፣ወ/ሮ ኪሚይ አቢበከር፣ ወ/ሮ አሚና አህመድ፣ ወ/ሮ ኪሚያ ኡመር፣ አቶ እድሪስ አብዲ፣ ወ/ሮ ዘቢዳ አብዱረህማን፣ ወ/ሮ ቢፍቱ ኡመር፣ አቶ ጃሚ ኡመር፣ ወ/ሮ ከዲጃ ቡሽራ ኡመር፣ አቶ አብዱመህይመን አብዱልናስር፣ ወ/ሮ ፈቲሀ አህመድና አቶ አህመድ ዘከሪያምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም ይህንን ትምህርት ስማር ስፖንሰር ለሆነኝ ለጡሎ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ዋና አስተዳዳሪ ለአቶ አብዲ ሽኩር እና ለጥናቴ የሚሆነኝን ገንዘብ ለሰጠኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የሀረሪ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ገለፃጭ ጥናት በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ነው፡፡በሰባትምእራፎች ተከፋፍሎቀርቦአል፡፡እነሱም መግቢያ፣ክለሳድርሳን፣የተጠኚው ብሄረሰብ ዳራዊመግለጫ፣ የእደጥበብ ባለሙያዎች ህይወት እና የሙያ ውጤቶች፣የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ትንተና፣ በመገልገያ ቁሶቹ ላይ ያለ ለውጥ፣ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳቦች ናቸው፡፡

የማህበረሰቡን የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች በናሙናነት በመምረጥ ቁሶቹ ከቁስነታቸው አንፃር አሰራራቸውን፣ ተግባራቸውን፣ ማህበራዊ ፋይዳቸውን፣ በቁሶቹ እና በቁሱ ባለቤት ማህበረሰብ መካከል ያለውን ግንኙነት እና በቁሶቹ ላይ የተደረገባቸውን ለውጦች ማሳየት የሚችሉአላማዎች ተዘጋጅተውለት የተከወነ ጥናት ነው፡፡

አላማዎቹን ከግብ ለማድረስ ቃለ መጠይቅ እና ምልከታን በዋነኛ መረጃ ማሰባሰቢያነት፣ የቡድን ተኮር ውይይትን በከፊል ተገልግያለሁ፡፡ መረጃዎቹ በምዕራፍ ሁለት ለጥናቱ ፊር እንዲቀዱ ከተገለፁት ትውሮች አንፃር ተተንትነዋል፡፡

በጥናቱ አስራአምስት ቁሶች ትንተና ተሰጥቶባቸዋል፡፡እነሱም 6 የስፌት፣ 4 የሸክላ፣ 2 የቅል እና 3 የእንጨት ቁሶች ትንታኔ ተደርጎባቸዋል፡፡ ቁሳቁሶቹ ከአክርማ፣ከገብስ ቀርማ፣ ከቅል፣ ከእንጨት፣ እና ከአፈር የተሰሩ ናቸው፡፡ ቁሶቹ ከተሰሩበት ንጥረ ቁስ አንፃር ከአለላ የሚሰሩቁሶች፣ከሸክላ የሚሰሩ ቁሶች፣ ከቅል የሚሰሩ ቁሶች እና ከእንጨት የሚሰሩ ቁሶች በማለት በአራት ወገን ተመድበዋል፡፡

እነዚህ ቁሶች ማህበረሰቡ እስከ ዛሬ እየሰራ የሚገለገልባቸው የመኖራቸውን ያህል ከመሰራትና ከአገልግሎት እየወጡ ያሉ ቁሶችም አሉ፡፡ለምሳሌ፡- የአለላ ስራ በከፍተኛ ሁኔታ እየተሰራ በአገልግሎት ላይ ሲሆን የሸክላ ስራ ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ጥቅም ላይ ይገኛል፡፡ ከቅል እና ከእንጨት የሚሰሩት ቁሶች ሲሰሩም ሆነ በአገልግሎት ላይ ሲውሉ አይታዩም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በመስራት እና በአገልግሎት ላይ ያሉት ቁሶችም በመስሪያ ንጥረ ቁሶቹ ላይ ለውጥ ይታያል፡፡

## ሙዳየ ቃላት

| በሀረሪ | ...........................................በአማርኛ |
|---|---|
| ሐይ | ............................................ ወተት |
| ሐይቀጻድ | ............................................የወተት መያዣ ቅል |
| መስሎላሀቲ | ............................................ማንቆርቆሪያ |
| ማሀጂጃ | ............................... ናሙና ቂስ (እያየች የምትሰፋበት) |
| ሚጊር | ............................................ ሰበዝ |
| ሞት | ............................................ሰፌት |
| ሞአይ ጋር | ............................................ ሞያ የሚለመድበት ቤት |
| ሱጉድ ምኦት | ............................................ ጉድጓዳቂና |
| ሸግሬ | ............................................ምላጭ |
| ሺብሪያ | ............................................ ወንበር |
| ቀርማ | ............................................ ቃርሚያ |
| ቀጻድ | ............................................ቅል |
| ቶሕቶሕ | ............................................ረጋሠራሽ (የለማጅ ሰፌድ) |
| አደጋር | ............................................ ባህል ቤት |
| አገርገራ | ............................................ አክርማ |
| አፈርጌይብ | ............................................ከሸክላ አፈር የተሠራ ኩባያ |
| አፍላላ | ............................................ትንሽ ማሰሮ (ገንቦ) |
| ኡኸት | ............................................እንጀራ |

| | |
|---|---|
| ኡፉ | ...............................................................................ክዳን |
| ኢጃይ | ........................................................................የብረዝ ቅል |
| ወስክምባይ | ...............................................................................ክዳን |
| ጊዲርጋር | ........................................................................ትልቁ ቤት |
| ጋር | ................................................................................ ቤት |
| ጋይ ቁሉ | ........................................................ ሺሻ የሚሳብበት ቅል |
| ጌይ | ................................................................................ራስ |
| ጌይጋር | .............................................................የሀረሪ ቤት (ባህላዊ) |
| ጢትጋር | ........................................................................ትንሹ ቤት |
| ጫት ቁሉ | .............................................ጫት ሲቃም ውሃ የሚጠጣበትቅ |

## ማውጫ

ገጽ


ምስጋና ........................................................................................ i

አጠቃሎ ........................................................................................ii

ሙዳየ ቃላት....................................................................................iii.

ማውጫ........................................................................................iv

1. መግቢያ......................................................................................1

1.1 የጥናቱ ዳራ...............................................................................1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት.....................................................................2

1.3 የጥናቱ አላማዎች...........................................................................2

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ.............................................................................3

1.5 የጥናቱ ወሰን................................................................................3

1.6 የመረጃ አሰባሰብና የአጠናን ዘዴ..........................................................4

1.6.1 ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡበት ዘዴ........................................4

1.6.1.1 ቃለ መጠይቅ..........................................................................4

1.6.1.2 የተተኳሪ ቡድን ውይይት.............................................................5

1.6.1.3 ምልከታ..................................................................................5

1.6.1.4 የጽሑፍ መጠይቅ......................................................................6

1.6.2 ካልአይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡበት ዘዴ.......................................6

1.7 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ.........................................................................6

1.8 የመስክ ቆይታ....................................................................................7

1.9 ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎች.........................................................8

2. ክለሳ ድርሳን.................................................................................... 10

2.1 የተዛማጅ ጥናት ቅኝት.......................................................................10

2.1.1 ለመጀመሪያ እና ለሁለተኛዲግሪ ማሟያ የቀረቡ የቁሳዊ ባህል ጥናቶች...10

2.1.1.1ለመጀመሪያ ዲግሪ የቀረቡ የቁሳዊ ባህል ጥናቶች.....................10

2.1.1.2 ለሁለተኛ ዲግሪ የቀረቡ የቁሳዊ ባህል ጥናቶች.....................11

2.2 የንድፈ ሃሳብ ቅኝት ............................................................................ 18

2.2.1 ቁሳዊ ባህል ምንድን ነው ............................................................ 18

2.2.2 የቁሳዊ ባህል ዘርፎች.........................................................................21

2.2.3 የቁሳዊ ባህል ጥናት አስፈላጊነት ................................................ 25

2.2.4 ቁሳዊ ባህልን የመመደቢያ መስፈርቶች........................................ 27

2.2.5 የቁሳዊ ባህል አንፃሮች እና የአተናተን ሂደቶች ........... ................. 28

2.2.6 ቁሳዊ ባህልን የመተንተኛ ሂደቶች ............................................ 29

2.2.6.1 ገለፃ................................................. ................. 29

2.2.6.2 ትርጓሜ.................................................................. 30

2.2.6.3 ግምገማ.................................................................. 30

2.2.6.4 ጥቆማ ................................................................... 30

3. የተጠኚ አካባቢውና የነዋሪ ብሔረሰብ ዳራዊ መግለጫ.......................................32

3.1 የተጠኚ አካባቢው ዳራዊ መግለጫ ................................................ 32

3.2 የሀረሪ ብሔረሰብ ዳራዊ መግለጫ ................................................ 33

3.2.1 ማህበረ ባህላዊ ዳራ ............................................................ 34

3.2.1.1 ጀጎል................................................................................ 35

4. የእደጥበብ ባለሙያዎች፣ ህይወት እና የሙያ ውጤቶች.............................. 38

4.1 የእደጥበብ ባለሙያዎች እና ሕይወታቸው ....................................... 38

4.2 የእደጥበብ ባለሙያዎች ሙያውን የለመዱበት መንገድ .................. 40

4.3 በእደ ጥበብ ሥራ ላይ ያለ ማህበራዊ አመለካከት ............................ 41

5. የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ትንተና .............................................. 44

5.1 የአለላ ቁሶች ........................................................................ 44

5.1.1 ሐማትሞት .................................................................... 50

5.1.2 ሌማትሞት .................................................................... 55

5.1.3 ጉፍተሙዳይ .................................................................. 59

5.1.4 ሰጋሪወስክምባይ ........................................................... 62

5.1.5 ሳንቡሳ ......................................................................... 66

5.1.6 ሚህካክናወስክምባይ ...................................................... 68

5.2 ከሽክላ የሚሰሩ ቁሶች ............................................................ 71

5.2.1 አፍላላኡፋ .................................................................... 72

5.2.2 ጊርጊራ ........................................................................ 77

5.2.3 መስሎላቲ ..................................................................... 80

5.2.4 ማሰሮ .......................................................................... 82

5.3 ከቅል የሚሰሩ ቁሶች ............................................................. 84

5.3.1 ሃይቀዳድ ...................................................................... 85

5.3.2 ኢጃይ .......................................................................... 87

5.4 ከእንጨት የሚሰሩ ቁሶች .......................................................... 88

5.4.1 ቆሪ (ገበታ) .................................................................... 89

5.4.2 ጭልፋ .......................................................................... 90

5.4.3 ሺብሪያ ........ 92

6. በመገልገያ ቁሶቹ ላይ ያለ ለውጥ ........ 93

6.1 መጠነኛ ለውጥ የተደረገባቸው ባህላዊ ቁሶች ........ 93

6.2 ሙሉ በሙሉ ለውጥ የተደረገባቸው ቁሶች ........ 95

7.ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳቦች ........ 98

7.1 ማጠቃለያ ........ 98

7.2 የይሁንታ ሀሳቦች ........ 100

ዋቢ መፃህፍትና ፅሁፎች ........ 101

# መግቢያ

ይህ ክፍል የተለያዩ ንኡሳን ክፍሎችን የያዘ ሲሆን፣ በቀጣይ ክፍሎቹ የተተኮረባቸው የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ አላማዎች፣ ጠቀሜታዎች፣ የአጠናን ዘዴ፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፤ የጥናቱ ወሰን እና ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሔዎች ናቸው።

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ጥናቱ በሀረር ከተማ የሚገኙ ሀረሪዎች "ቁሳዊ ባህል" (የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን) የሚያጠና ነው።

ቁሳዊ ባህል የሚለው የአማርኛ ፍቺ አቻ ሆኖ የሚያገለግለው "material culture" ለሚለው የእንግሊዝኛ ስያሜ እንደሆነ ፈቃደ (1991፣15) ገልፀዋል። ቁሳዊ ባህል ከፎክሎር ዘውጎች መካከል አንዱ መሆኑን በርካታ ምሁራን ይገልፃሉ። ከምሁራኑም መካከል Dorson (1972፣2)፣ፈቃደ (1991፣10-16) እና Bartis (2002፣4) ይጠቀሣሉ። ለአብነት ያህል ከምሁራኑ መካከል ፈቃደ የሚከተለውን ገለፃ ሰጥተዋል።

> *ቁሳዊ ባህል በአይን የሚታየውን በእጅ የሚዳሰሰውን፣ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች እነዚህ ቁሳቁሶች የተሰሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ፣ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሰራር፣ የቅመም አቀማመም ብልሀትን፣ የልብስ፣ ቤት አጥር ወዘተ. አሰራርን፣ ሰዎች ልዩ ልዩ ሥራዎችን የሚያከናውኑባቸው መሳሪያዎችንና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ያጠናል (ፈቃደ፣ 1991፣15)።*

ከቀረበው ጥቅስ የምንረዳው ቁሳዊ ባህል የተለያዩ ክፍሎች ኖረውት የሚጠና ሰፊ የፎክሎር ዘርፍ መሆኑን ነው። ይህ ጥናትም የዚህ ሰፊ የፎክሎር ዘርፍ ከሆነው ቁሳዊ ባህል ማዕቀፍ ውስጥ ከሚገቡት የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ላይ ትኩረቱን አድርጓል። ጥናቱ በስድስት ክፍሎች ተከፋፍሎ ቀርቧል። በምዕራፍ አንድ በመግቢያው አብይ ርዕስ ስር እየተገለፀ ያለውን በክፍል ጨምሮ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ አላማዎች፣ ጠቀሜታዎች፣ የአጠናን ዘዴ፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፣ የጥናቱ ወሰን እና ያጋጣሙ ችግሮች ቀርበዋል። በሁለተኛው ምዕራፍ ከጥናቱ ርእስ እና አካባቢ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጥናቶች እና ለጥናቱ ፊር የቀደዱ የንድፈ ሃሳቦች ቅኝት ቀርቧል። የጥናቱ አካባቢ፣ የታሪካዊ፣ ባህላዊ፣

ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና መልክአምድራዊ ሁኔታዎች በምዕራፍ ሦስት ቀርበዋል። በምዕራፍ አራት የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ህይወት፣ የስመዳ ሂደት እና የማህበረሰቡ አመለካከት ቀርቧል። በምዕራፍ አምስት የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ትንተና ቀርቧል። በምእራፍ ስድስት በመገልገያ ቁሶች ላይ ያለ ለውጥ ተዳሶበታል።በምራፍ ሰባት ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳቦች የቀረቡ ሲሆን ዋቢ ፅሁፎች እና አባሪዎችም ከዋናው ፅሁፍ ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የተጠቀሰውን ርእስ ይዤ ጥናት ለማድረግ ያነሳሳኝ ምክንያት ቀድሞ የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበርኩበት ወቅት ጓደኞቼ በአብዛኛው የሀረሪ ብሄረሰብ አባላት ነበሩ ።ቤታቸውን የሚያስውቡበት ቁሳቁስ እና የሚለብሱት አልባሳት ይመስጸኝ ነበር።እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች በጣም ያሸበረቁ እና ለአይን ማራኪ በመሆናቸው ይህንን ባህል ከየት አዳበሩት የሚል ጥያቄ በውስጤ ብዝ ጊዜ ይመላለስ ነበር።ይህንን ቁሳዊ ባህል ለማጥናት የምችልበት ሁኔታ ሲፈጠርልኝ ያስደምመኝ የነበረውን ጉዳይ ለመመርመር ወሰንኩ።በመሆኑም ይህ ቁሳዊ ባህል እኔ በማጠናው መልክ ከአሁን በፊት ባለመጠናቱ ለማጥናት ተነሳሳሁ።

## 1.3 የጥናቱ አላማዎች

የጥናቱ ዋና አላማ የሀረሪ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች አሠራር ምን መልክ አላቸው፣ የቁሶቹ የአሁንና የቀድሞው ይዞታ ምን ተመሳስሎና ልዩነት አላቸው፣ በቁሳዊ ባህሎቹ ውስጥ ማህበረሰቡን እንዴት አገኘነው የሚለውን መመርመር ነው። የሚከተሉት ደግሞ በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎች ናቸው።

- በአለላ ስራዎቹ ላይ ያረፈው ዲዛይን ተምሳሌት አለው ወይ?
- የዲዛይኖቹ ፋይዳ ምንድን ነው?
- የተመረጡ ናሙና ቁሶች እንዴት ይሰራሉ ለምን አገልግሎት ይውላሉ?
- ቁሶቹ ከሀገረሰባዊ ማንነት ጋር የሚያቆራኛቸው ምንድነው?
- የቁሳዊ ባህሎቹ ተምሳሌት ምንድን ነው?

- በሙያው ላይ የሚታየው ፆታዊ ተሳትፎ ምን ይመስላል?
- በቁሶቹ አሰራርና አጠቃቀም ላይ እየመጣ ያለው ለውጥ አለ ወይ? የሚሉ ናቸው፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ሲሆን ከዚህ በታች የቀረቡትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታሰባል፡፡ እነሱም፡-

- በርዕሰ ጉዳዩ ላይ በቀጣይነት ሰፊና ጥልቅ ጥናት ይካሄድ ዘንድ አዎንታዊ ግፊት ይፈጥራል፡፡
- በጥናት አካባቢውም ሆነ በርእሰ ጉዳዩ ላይ ወደፊት ጥናት ለሚያካሂዱ ወገኖች መነሻ መረጃ በመስጠት ያገለግላል፡፡
- ስለአካባቢው ቁሳዊ ባህል ማወቅ ለሚፈልጉ በጥናት የተደገፈ መረጃ በመስጠት ያገለግላል፡፡
- በቁሳዊ ባህል ጥናት በኩል በሀገራችን ያለውን የዘርፉን ክፍተት ለመሙላት የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከቦታ እና ከርዕሰ ጉዳይ ወሰን የተበጀለት ነው፡፡ ከቦታ አንፃር የሀረሪ ብሔረሰብ አባላት እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በተለያየ ምክንያት በተለያዩ የሀገራችን ከተሞች እና በውጪ ሀገራትም ይኖራሉ፡፡ ታዲያ ምንም እንኳን በበርካታ ቦታዎች ላይ የሀረሪ ማህበረሰቦችን ብናገኝም ይህ ጥናት ግን በብዛት የሚገኙበትን ቦታ በመምረጥ በሀረሪ ክልላዊ መንግስት በሐረር ከተማ የሚገኙትን ሀረሪዎች መርጧል፡፡

ከቋንቋ አንፃር የሀረሪ ብሔረሰብ አባላት አብዛኞቹ ማለት ይቻላል ከሀረሪ (ጌይሲና) ቋንቋ በተጨማሪ አማርኛ አቀላጥፈው ስለሚናገሩ በሀረሪ እና በአማርኛ ቋንቋ የተገኙ መረጃዎች ለጥናቱ ውለዋል፡፡

በቁሳዊ ባህል ጥናት ስር የሰው ልጅ ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት ፈጥሮ የተገለገለባቸውን በአይን የሚታዩና በእጅ የሚዳሰሱ ቁሳቁሶችን በሙሉ የሚያካትት ነው ፡፡ ይህ የጥናት

ዘርፍ ስፋቱ የትየለሌ ነው። በመሆኑም ጥናቱ ከዚህ ዘርፍ እንጎቻ የሆነውን የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች በመውሰድ ቆንጥሮ ይመለከታል። ሰበቡም ካለው የጊዜና የአቅም መጠን አኳያ ርዕስ ጉዳይን ማጥበብ ተገቢ በመሆኑ ነው።

## 1.6 የመረጃ አሰባሰብ እና የአጠናን ዘዴ

በዚህ ጥናት አላማዎቹን ለማሳካት እና የምርምር ጥያቄዎቹን ለመመለስ ቀዳማይ እና ካልአይ የመረጃ ምንጮች ተግባር ላይ ውለዋል።

### 1.6.1 ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡበት ዘዴ

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ ቀዳማይ መረጃዎች ፊቃደ አዘዘ 1991 እና Godl Stein 1972 የመከሩትን ተግባር ላይ በማዋል አጥኚዋ በማህበረ ባህላዊ አውዱ ላይ በመገኘት በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ መረጃዎቹ ተሰብስበዋል።

#### 1.6.1.1 ቃለ መጠይቅ

ይህ ክፍል በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንዴት እንደተሰበሰቡ እና በቃለ መጠይቁ የተሳተፉ መረጃ አቀባዮችም በምን መልኩ እንደተመረጡ ተገልጾበታል።

ጥናቱ ቃለመጠይቅ ለማድረግ መረጃ አቀባዮችን ሲመርጥ የተጠቀመው አካሄድ የእጅ ባለሙያ የሆኑ፣ ታሪክን ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ የተለየ የህይወት ተሞክሮ ያላቸው፣ ያገላለፅ ብቃታቸው ላቅ ያለ እና የእድሜ ባለፀጋ የሆኑ ሰዎችን ፆታ ሳይለይ ትኩረት በማድረግ መርጧል።

ቃለ መጠይቅ ያደረግኩት በሁለት አይነት መንገድ ነው። አንደኛው ቀጠሮ በመያዝ ሲሆን ሁለተኛው ድንገት በተገናኘንበት ወቅት ነው። ቃለ መጠይቆቹን በተመለከተ በፅሁፍ የተዘጋጁና (structured interview) ከአውዱ የመነጩ (unstructured interview) ናቸው።

ቃለ መጠይቁን በማደርግበት ጊዜ በዋናነት መቅረጸ ድምፅ፣ ቪዲዮ ካሜራ እና ፎቶካሜራ በመጠቀም መረጃውን ሰብስቤያለሁ።

መረጃ አቀባዮቼን ያገኘሁባቸው አውዶች ባለሙያዎቹ ሙያዊ ስራቸውን በሚያከናውኑባቸው ቦታዎች ፣ በቤት ውስጥ፣ በቢሮ ውስጥ እና በሙዚየም ውስጥ ነው፡፡ በዚህ የመረጃ አሰባሰብ ሂደትም ስለ ሀረሪዎች ታሪክ፣ ስለ የመገልገያ ቁሶች ተግባር፣ ስለ ባለሙያዎች ማህበራዊ ህይወት እና ባህላዊ ቁሶቹ ላይ ስለተደረገው ለውጥ ጥሩ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

#### 1.6.1.2 የተተኮረ ቡድን ውይይት

የምፈልጋቸው መረጃዎች እየተድበሰበሱ ሲቀሩና ለአንድ ጥያቄ የተለያየ መልስ ሲሰጡኝ በቡድን አወያይቼ አንድ ወጥ የሆነ መረጃ አግኝቻለሁ፡፡ለምሳሌ ስለአፍላላኡፋ መረጃዎች እርስበእርሳቸው ሲጋጩ እናይ አሲያ የአለላ ስራ ማህበር ያሉትን ባለሙያዎች በማወያየት ወጥ የሆነ መረጃ ወስጃለሁ፡፡እነዚህን ባለሙያዎች ያወያየሁበት ዋነኛ ምክንያት ከሌሎቹ ባለሙዎች ይልቅ ለማሰባሰብ ሳልቸገር በቀላሉ ስላገኘኋቸው ነው፡፡

#### 1.6.1.3 ምልከታ

ይህ ክፍል አጥኚዋ በጥናቱ ትኩረት ያገኘችውን ናሙና ቁሶች እንዴት እንደመረጠች እንዴት ተግባር ላይ እንዳዋለችው የሚያሳይ ነው፡፡

በሀረሪዎች ዘንድ ለቤት ውስጥ መገልገያነት የሚውሉ ቁሶች በሙሉ ታይተዋል፡፡ ቁሶቹን ለማየት እድል የገጠመኝ በማህበር ተደራጅተው የሚሰሩ ማህበራት በመኖራቸው፣ እያንዳንዱ የሀረሪ ቤት ውስጥ ቁሶቹ ልዩ ክብርና ጥንቃቄ ተሰጥቷቸው የሚገኙ በመሆናቸው፣ እድሜ ጠገብ የሆኑትን እና ጠቀሜታቸው እየተቀዛቀዘ የመጡት ቁሶች ተቀርሰው በአራት ሙዚየም ውስጥ በመገኘታቸው እና የባህላዊ ቁሶች መሸጫ ሱቆች በመኖራቸው ቁሶቹን ለመመልከት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮልኝ ነው፡፡

ቁሶቹ እኩል ትኩረት አግኝተው እንዳይተነተኑ ያደረጉ ምክንያቶች አሉ፡፡ አንዱ የመረጥኩበት ምክንያት ማህበረሰቡ የኔ ናቸው ከአያት ቅድማያቶቻችን የወረስናቸው ናቸው ያሏቸውን፣ እነዚህ ቁሶች የእከሌ ማህበረሰብ ናቸው እኛም እንጠቀምበታለን ያሉትን መሰረት በማድረግ መረጣ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ማህበረሰቡ የኔ ናቸው ያላቸው ቁሶች በጣም በርካታ በመሆናቸው ከነዚህም ውስጥ ለየት ያለ ትእምርት የተሸከሙትን በመምረጥ እና በቁጥር ትንሽ የሆኑትም ያለመረጣ በመውሰድ ነው፡፡

በምልከታ የተገኙ መረጃዎች እንዳይዘነጉ አጥኚዋ በማስታወሻ ደብተር ቀልቧን የሳቡትን እና ትኩረቷን የገዙትን መረጃዎች በፍጥነት እና በንቃት መዝግባ ይዛለች፡፡

#### 1.6.1.4 የፅሁፍ በመጠይቅ

የፅሁፍ መጠይቅ ዋነኛ አላማ በክልሉ የሚገኙ በሀላፊነት ቦታ ላይ የተቀመጡ ባለሙያዎች ስለ ክልሉ ቁሳዊ ባህል ያላቸውን መረጃ ለመፈተሽ እና ለእደ ጥበቡ ባለሙያዎች የባህልና ቱሪዝም ቢሮ የሚያደርገው እገዛ ካለ ለማረጋገጥ ታስቦ ነው፡፡ከዚህም በተገኘው መረጃ የይሁንታ ሀሳቦች ተዘጋጅተውበታል፡፡

### 1.6.2 ካልአይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡበት ዘዴ

የተሟላ የመረጃ ስብስብ መጀመር ያለብን ከቤተመፃህፍት መሆኑ የተረጋገጠ ነው፡፡ አንድ ተመራማሪ መስክ ከመውጣቱ አስቀድሞ መስክ ላይ ሊተገብራቸው የሚገቡ እያንዳንዷን ቅንጣት መረጃ የሚያገኘው ከቤተ መፃህፍት ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ካልአይ የመረጃ ምንጮች ከመስክ በፊትና ከመስክ በኋላ መመርመር በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡

ከቤተ መፃህፍት ያገኘኋቸው መረጃዎች ንድፈ ሃሳቦች፣ ያልታተሙ ጥናታዊ ፅሁፎች፣ ድረ ገፆች ሲሆኑ የንባብ እና ማስታወሻ የመያዝ ዘዴን በመጠቀም መረጃዎቹን አደራጅቻለሁ፡፡

## 1.7 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

በቀደሙት የዚህ ምዕራፍ ክፍሎች እንደተገለፀው ለጥናቱ በግብአትነት የሚያገለግሉ ወሳኝ መረጃዎች በተለያዩ ዘዴዎች ተሰብስበዋል፡፡ እነዚህም መረጃዎች የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ በሚያስችል አኳኋን በሚከተለው ሂደት መሰረት ተተንትነዋል፡፡

በምሁራን የተሰጡ ትውሮችን መሰረት በማድረግ ቁሦቹን በምድብ በምድብ ማደራጀት ቀዳሚ ተግባሬ ነበር፡፡ ከዚህ አንፃር የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶቹን ከተሰሩበት ንጥረ ቁስ በመነሳት ከአለላ የተሰሩ፣ ከሸክላ ፣ ከእንጨት እና ከቅል የተሰሩ በማለት ከፋፍያዋለሁ፡፡ መከፋፈሉን ከተገበርኩ በኋላ በገላጭ የአቀራረብ ስልት ትንተናውን አከናውኛለሁ፡፡

## 1.8 የመስክ ቆይታ

ከጥር 15-የካቲት10 2004 ዓ.ም ድረስ በሀረር ከተማ ቆይታ በማድረግ መረጃዎቼን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ከመስክ ከተመለስኩ በኋላ መረጃውን በምተነትንበት ወቅት የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም የሙዚየም አስተባባሪ የሆኑት አቶ አህመድ ዘካሪያ የሀረሪ ማህበረሰብ ተወላጅ እና ባህሉንም ጠንቀቀው የሚያውቁ በመሆናቸው መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

ለጥናቱ የመረጥኩትን አካባቢ የማውቀው ነው፡፡ ማህበረሰቡን እና ባህሉን በአብሮነት እየኖርኩበት ያደኩበት ቢሆንም በአጥኚ እይታ አይቼው አላውቅም፡፡ በመሆኑም በአካባቢው ላይ ከዚህ ቀደም ጥናት ያደረጉ እና ከኔ ጥናት ጋር በተመሳሳይ ርዕስ በሌላ ቦታ ያጠኑ ሰዎችን አነጋግሬ የጥናት ተሞክሯቸውን ተካፍያለሁ፡፡ አቶ አህመድ ዘካሪያ፣ ዋልተንጉስ መኮንን እና አብዩ አስማማው በዋናነት የሚጠቀሱ ልምዳቸውን ያጋሩኝ ምሁራን ናቸው፡፡ ዋልተንጉስ መኮንን እና አብዩ አስማማው በመስክ ቆይታዬ መረጃዎችን ለመሰብሰቢያነት የምጠቀምባቸው ዘዴዎች ምን ምን እንደሆኑ፣ በመረጃ መሰብሰብ ሂደት ላይ ምን ማድረግ እንዳለብኝ በሚገባ ምክር የሰጡኝ ሰዎች ናቸው፡፡

በመቀጠልም ከትምህርት ክፍሉ ማንነቴን እና ለምን ተግባር እንደተሰማራሁ ለሚመለከተው ክፍል የሚገልፅ ደብዳቤ በማፃፍ ወደ መስክ አመራሁ፡፡ ሐረር ከተማም እንደ ደረስኩ ከትምህርት ክፍሉ የተፃፈልኝን ደብዳቤ ለክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስገባሁ፡፡ የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮም አንድ ሰራተኛ የተሰማራሁበትን የመስክ ተግባር እስክጨርስ ድረስ ከስራ ነፃ በማድረግ መደበልኝ፡፡የተመደበልኝ ሰው አቶ ጃሚ ኡመር ይባላል፡፡ ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲ በባህልና ታሪክ ጥናት የመጀመሪያ ዲግሪ አለው፡፡ አቶ ጃሚ የጥናቴ ትኩረት የሆኑት የሐረሪ ማህበረሰብ ተወላጅ በመሆኑ የመረጃ አቀባዮችን[1] መረጣ በሱ እገዛና ከሀረሪ ክልል ማዘጋጃ ቤት በተሰጠኝ ጥቆማ መሰረት አከናወንኩ፡፡

---

[1] አስራ ስምንት መረጃ አቀባዮች ተመርጠው ነበር ነገር ግን ከነዚህ ውስጥ አስሩን በቁልፍ መረጃ አቀባይነት መርጫቸዋለሁ፡፡ እነሱም ወ/ሮ ሶፊያ ኢብራሂም፣ ወ/ሮ ከሚየ አቢበከር፣ ወ/ሮ አሚና አህመድ፣ ወ/ሮ ኪሚያ ኡመር፣ ወ/ሮ ፈቲሀ አህመድ፣ ወ/ሮ ዘቢዳ አብዱረህማን፣ ወ/ሮ ቢፍቱ ኡመር፣ አቶ ጃሚ ኡመር፣ ወ/ሮ ከዲጃ ቡሽራ ኡመር፣ አቶ አብዱል መሀይመን አብዱልናስር፣ እና አቶ እድሪስ አብዲ ናቸው፡፡ እነዚህ መረጃ አቀባዮች ቁልፍ መረጃ አቀባዮች በመባል የተመረጡት

ለጥናቱ ይሰማማሉ ያልኳቸውን በጥናቱ ዘዴ በተገለፀው መሠረት በመምረጥ መረጃውን ሰበሰብኩ፡፡ ከሰአት በፊት በማህበራት በመደራጀት የሚሰሩ ማህበራት ጋ እና ሙዚየሞች ውስጥ መረጃዎችን እሰበስባለሁ፡፡ ከሰአት በኋላ በግል የሚሰፉ ባለሙያዎች ዘንድ በመሄድ መረጃውን ሰብስቤያለሁ፡፡

መረጃውን በምሰበሰብስበት ወቅት ከአቶ አብዱ መሀይመን በስተቀር በማህበራት የተደራጁትም፣ በግል የሚሰፉትም፣ ሙዚየምቹም የሚገኙት በጆጎል ውስጥ ስለነበር የመረጃ አሰባሰቡ ተግባር 99 (ዘጠናዘጠኝ ከመቶ) የተገኘው በጀጎል ውስጥ ነው፡፡

በማህበር ተደራጅተው የስፌት ስራ የሚሰሩትን ባለሙያዎች ለተተኳሪ ቡድን ውይይት አመቺ በመሆኑ ከነርሱ ጋር እናይ አሲያ የአላላ ስፌት ማህበር ውስጥ የቡድን ውይይት አከናውኛለሁ፡፡

የሀረሪዎች ቁሳዊ ባህሎች በተለይም የስፌት ስራ እጅግ ማራኪና አስደሳች በመሆናቸው ቀልቤን ለረጅም ደቂቃዎች እየማረኩኝ እመለከታቸው ነበር፡፡ ሌላው የማልሸሸገው ነገረ ቁሶቹ የተሸከሙት ትዕምርት በጣም የሚገርምና የሚያስደንቅ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ እድሉን ካገኘሁ በሀረሪ ማህበረሰብ ላይ ሰፋ ባለ የማንነት ጥናት ላይ ምርምር ብሰራ ምኞቼ ነው፡፡

## 1.9 ያጋጠሙ ችሮችና መፍትሔዎች

1. በቤተመፃህፍት ውስጥ ያሉ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፎች ከካታሎግ ላይ ተቀደው መውጣታቸው እና አንዳንደቹም ካታሎጉ እያለ የፅሁፎቹ አለመኖር ችግር ተፈጥሮብኝ ነበር፡፡ ለምሳሌ የአብይ አስማማው ካታሎጉ ተቀዶ ወጥቶ ነበር፡፡ እኔ የነበረኝን ቁጥር ሰጥቼ በድጋሜ ተዘጋጅቷል፡፡ የአበበ መርዕድ ካታሎጉ አለ፡፡ ጥናቱ ጠፍቶ ከቀናት በኋላ ሌላ ሼልፍ ላይ ተገኝቷል፡፡ ነገር ግን ቀደም ሲል ርዕስ ስመርጥ የያዝኳቸው call No (ቁጥሮች) በመኖራቸው ችግሩ ተቃሎልኛል፡፡
2. በሀረር አደጋር ሙዚየም ውስጥ ካሉ መረጃ አቀባዮች መረጃ ለመውሰድ ቀላል ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ መረጃ እንዲሰጡኝ የምጠይቃቸው ሰራተኞች አገሌ ካልሆነ እኛ

ላቀረብኩላቸው የመረጃ ማሰባሰቢያ ቃለመጠይቆች የተብራራና ተገቢ ገለፃ የሠጡኝ፣ ቁሳዊ ባህሎቹን ባለሙያ በመሆን የሚሰሩና፣ ታሪክ አዊቂ በመሆናቸው ነው፡፡

ልንሰጥሽ አንችልም በማለት ከፍተኛ የመግለፅ እና የማስረዳት ብቃት እንዳላቸው የተገነዘብኩት አስጎብኚዎች አለቆቻቸው እኔ እያለሁ ለምን እናንተ መረጃ ሰጣችሁ እንባላለን ብለው በመፍራት መረጃውን ሳይሰጡኝ ቀርተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከሌሎች ዋናዋና ናቸው ከተባሉት አስጎብኚዎች በቀጠሮ ቢያመላልሱኝም ያለመሰልቸት ተመላልሼ መረጃውን አግኝቻለሁ፡፡

3. በግል ስፌት የሚሰፉ ሞያተኞች መረጃ ለመስጠት ካሜራውን እና መቅረፀ ድምፁን ሲያዩ በእኔ ግምት ነፃነታቸውን ያጡ ስለሚመስላቸው በፍፁም ፍቃደኛ አንሆንም በማለታቸው ጀጎል ውስጥ በስፌት ሞያ አሉ የተባሉ ሴቶችን ፍለጋ ባጣም ተንከራትቻለሁ፡፡ በመጨረሻም ሙያቸውን ለማስረዳት ፈቃደኛ የሆኑ ግለሰቦችን በማግኘቴ ይሄ ችግር መፍትሄ አግኝቷል፡፡

የሀረሪ ብሔረሰብ አባላት የሆኑት አስሩም መረጃ አቀባዮቼ ከአቶ አብዱ መሀይመን ጀምሮ እያንዳንዳቸው ከኔ ምንም አይነት ክፍያ ያልጠየቁ ሲሆን ለመስጠት የሞከርኳቸው ግለሰቦች ጭምር በፍፁም እንደማይቀበሉኝ በመግለፅ እምቢ ብለውኛል፡፡ በመሆኑም ክፍያ አይገባንም የሚል መልዕክት አለው፡፡ ያለ ክፍያ የባህሉን ሙሉ መረጃ ለተመራማሪ መስጠታቸው የሚያስመሰግናቸው ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

4. አንዳንድ መረጃ አቀባዮቼ ምስላቸውን በካሜራ ለማስቀረት በምፈልግበት ጊዜ ፎቶ ለመነሳት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡ ምክንያቱ ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ ሳይሆን እንዳልቀረ አቶ ጃሚ ነግረውኛል፡፡

# 2. ክለሳ ድርሳን

ይህ ክፍል ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮችን አካቶ ይዟል፡፡ ቀዳሚው ንኡስ ርዕስ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ቀደምት ጥናታዊ ፅሁፎች ተቃኝተውበታል፡፡ በተከታዩ ንኡስ ርዕስ ስለ ቁሳዊ ባህል የመስኩ ምሁራን የሠነዘሯቸው ንድፈሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

## 2.1 የተዛማጅ ጥናት ቅኝት

በዚህ ርዕስ ስር በቁሳዊ ባህል ጥናት ስር የሚካተቱ እና ለጥናቱ ፈር የቀደዱ ጥናቶች እንደያዙት ርዕስ ተከፋፍለው ይዘው የተነሡት ጉዳይ ምን እንደነበር ቀርቧል፡፡ ከኔ ርዕስ ጋር ያላቸው ተመሳስሎና ልዩነትም ተገልጿል፤ የቁሳዊ ባህል ጥናት በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል ለመጠቆም የተገኙ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያና የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ቀርበዋል፡፡

በርዕስ ባይገናኙኝም በሀረር ከተማና በሀረሪዎች ላይ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የተጠኑ ጥናቶች ዳሰሳ ተደርጎባቸዋል፡፡ በመሆኑም የኔ ጥናት ቀድሞ ከተጠኑት ጥናቶች ተለይቶ የሞላው ክፍተት ምን እንደሆነም ተጠቁሟአል፡፡

### 2.1.1 ለመጀመሪያና ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ የቁሳዊ ባህል ጥናቶች ዳሰሳ

በዚህ ክፍል በሁለትየትምህርት ደረጃዎች የቀረቡ የቁሳዊ ባህል ጥናቶች በማን እንደተጠኑ፣ ምን እንደተጠና፣ ጥናቱ የተከናወነበት አካባቢ እና የተጠናበት አመት ቀርበዋል፡፡

#### 2.1.1.1 ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ የቁሳዊ ባህል ጥናቶች

ብርሃኔ ትንሳኤ ወልደሰንበት በ1963 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ የሸመናና የቆዳ ሥራ ጥናት አካሂዷል፡፡ ውብሸት አሰፋ በ1978 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ ጌጣጌጥና አልባሳትን አጥንቷል፡፡ አያል አድማሱ በ1992 የጐጃም አልባሳትን አጥንቷል፡፡ ተሾመ ፎርሲዶ በ1993 የሀዲያ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን እና የእርሻ መሳሪያዎች ላይ ጥናት አካሂዷል፡፡ ጌታቸው ግርማ በ1998 የራያን ጌጣጌጥና አልባሳት አጥንቷል፡፡

#### 2.1.1.2 ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ የቁሳዊ ባህል ጥናቶች

ሔለን አላምረው በ1999 ዓ.ም ደንበጫ ላይ የሸመናና የቆዳ ሥራ ጥናት አካሂዳለች፡፡ ዋልተ ንጉስ መኮንን በ2000 ዓ.ም የሸመና ስራ ጥናት በአክሱም አክናውኗል፡፡ አብዩ አስማማው በ2000 ዓ.ም በአርጎባ ልዩ ወረዳ በጌጣጌጥና በቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ላይ ጥናት አድርጓል፡፡ አስቴር ሙሉ በ2000 ዓ.ም በዘጌ ባህረ ሰላጤ የቤት አሰራርና የመገልገያ ቁሳቁሶች ጥናት አድርጋለች፡፡ የኔ አለም አረዶ በ2000 ዓ.ም የአርሲ ሴቶችን ጌጣጌጥና አልባሳት ጥናት አድርጋባቸዋለች፡፡ አበበ መርዕድ በ2000 ዓ.ም የአርሲን የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች አጥንቷል፡፡ እራሔል እንዳለው በ2000 ዓ.ም የአኝዋ ማህበረሰብን ባህላዊ ምግቦች አጥንታለች፡፡ ሀብታሙ እንግዳው በ2001 በደቡብ ጎንደር ሊቦከምከም ወረዳ የሻም መድሃኒአለም ሸክላ ስራ የአሠራር ሂደትና ጠቀሜታውን አጥንቷል፡፡ ያሬድ ተፈራ በ2002 ዓ.ም በሰቆጣና አበርገሌ ወረዳ የጌጣጌጥ እና የአልባሳት ጥናት አካሄዷል፡፡ በ2002 ዓ.ም አብዲ ተማም የስልጤ ማህበረሰብ ባህላዊ የምግብ አዘጋጃጀት ላይ ጥናት አካሂዷል፡፡ ደግሰው ጥላሁን "ባህላዊ የሸክላና የቆዳ ስራ በቡሬና ወንበርማ ወረዳ" (2003)፣ በ2004 አብይ አክሊሉ የክስታኔ ማህበረሰብ የቤት ውስጥ የመገልገያ ቁሶች ላይ ጥናቱን ሠርቷል፡፡

ቁሳዊ ባህልን ዋና ጉዳያቸው በማድረግ የተጠኑ በርካታ ጥናቶች በመጀመሪያ ዲግሪ እና በሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ቀርበዋል። ቢሆንም በዚህ ክፍል ዳሰሳ የተደረገባቸው ከኔ ርአስ ጋር ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል የሚገናኙት ጥናቶች ላይ ይሆናል።

በኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሀግብር የተጠኑ ጥናቶች ከኔ ርዕስ ጋር የሚገናኙት የሚከተሉት ናቸው።  አብዩ አስማማው "የአርጎባ ብሔረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች" (2000)፣ አበበ መርዕድ "በጎባ ወረዳ የኦሮሞ ብሔረሰብ የመመገቢያ ቁሳቁስ አሰራር አገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ትንተና" (2000)፣ አስቴር ሙሉ "ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌባህረ ሰላጤ" (2000)፣ ሀብታሙ እንግዳው "በደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ በሻም ጎድጓዲት ገጠር ቀበሌ የሻም መድሃኒአለም ሸክላ ስራ ውጤቶች የአሰራር ሂደትና ጠቀሜታ ትንተና" (2001)የሚገናኙት ፤ ደግሰው ጥላሁን "ባህላዊ የሸክላና የቆዳ ስራ በቡሬና ወንበርማ ወረዳ" (2003 ናቸው።

እኔ የመረጥኳቸውን ብሔረሰቦች ተተኳሪ በማድረግ የተሰሩ ጥናቶች እና ከእኔ ጥናት ርዕስ ጋር በከፊል ተመሳሳይ የሆኑ ጥናቶች የአሰራር ስልት ስለቀሰምኩባቸው በተዛማጅነት ተመልክቻቸዋለሁ፡፡

አብይ አስማማው "የአርጎባ ብሔረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች በአማራ ክልል በደቡብ ወሎ ዞን፣ አርጎባ ልዩ ወረዳ" (2000) የአብይ ጥናት ዋና አላማ የአርጎባን ብሔረሰብ ማንነት ከቁሳዊ ባህሎቻቸው አንፃር ለማጥናት ወዲያውም መረጃዎችን በፅሁፍ ከትቦ ለማስቀመጥ አልሞ የተነሳ ነው፡፡ ከብሔረሰቡ ቁሳዊ ባህሎች ናሙና የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች የጥናቱ ዋነኛ ተተኳሪዎች ሲሆኑ እነዚህ ቁሶች ከቁስነታቸው አንድም በከባህላዊ ገፅታቸው አንፃር ለመመልከት አስቦ ነው የተነሳው፡፡

አብይ በጥናቱ "11" ቁሶችን በናሙናነት መርጦ ትንታኔ ሠጥቷል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አምስቱ የቤት ውሰጥ መገልገያ ሲሆኑ ስድስቱ ደግሞ የማጌጫ ቁሶች ናቸው፡፡ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶቹን ከተሰሩበት ንጥረ ቁስ አንፃር ከቆዳ፣ ከእንጨት፣ ከድንጋይ፣ ከአፈር፣ ከቅል የተሰሩ መሆናቸውን በግኝቱ ላይ ገልጿል፡፡ የማጌጫ ቁሶቹ ደግሞ ከብር፣ ከነሀስ፣ ከኒኬል እና ከሸማ የተሠሩ መሆናቸውን አስረድቶ ለማጌጫነት ከሚውሉበት የሰውነት ክፍል አንፃርም የአንገት፣ የእጅ፣ የወገብ እና የእግር ብሎ ከፋፍሎ መድቧቸዋል፡፡

የአብይ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው የቤት ውሰጥ መገልገያ ቁሶችን በመመልከቱ ነው፡፡ የኔ እና የአብይ ጥናት ከአካባቢ ልዩነት በስተቀር ተመሳሳይ ነው፡፡ ነገር ግን አብይ ከቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች በተጨማሪ ማጊያጊያጫዎችንም አይቷል እኔ ግን የቤት ውስጥ መገልገያዎችን ብቻ ነው ያጠናሁት፡፡ እሱ ቁሶቹን መድቦ ባያጠናም ግኝቱ ላይ ከቅል፣ ከቆዳ፣ ከእንጨት ከድንጋይ የተሰሩ ናቸው በማለት ከተሰሩበት ንጥረ ቁስ አንፃር በየምድባቸው ሰይሟቸዋል፡፡ የኔ ጥናትም ከተሰሩበት ንጥረ ቁስ አንፃር በወገን በወገን መድቦ በማጥናቱ ያመሳስለናል፡፡ አላማው ላይም የቁሶቹ ተምሳሌት ማሳየት ትኩረቱ ነበር፡፡ የእኔም ጥናት ተምሳሌቶቹን ማሳየት ዋና አላማው ነው፡፡

አስቴር ሙሉ "ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ" (2000)፣ አስቴር አላማ ያደረገችው በዘጌባህረ ሰላጤ ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶችን ከሸክላ የተሠሩ የቤት ቁሶችን በሳይንሳዊ የአጠናን መንገድ መግለፅ፣ መቅረስ፣ መሰነድና እነዚህ ቁሶች

ህልውናቸው ፈፅሞ ከመጥፋቱ ተጠብቆ ለማህበረሰቡ ጠቀሜታ የሚሰጡበትን መንገድ መጠቆም ነው፡፡ አስቴር መረጃዎቿን ከቤተመፃህፍት፣ ከመረጃ መረብ (internet) እና ከመስክ ሰብስባለች፡፡ በተለያዩ የፎክሎር ባለሙያዎች የተባሉ ትውራዊ ዳራዎችና ከጥናቷ ርዕስ ጋር የሚዛመዱ ሌሎች ጥናቶች ላይ ዳሰሳ አድርጋለች፡፡

አስቴር በምልከታና በቃለ መጠይቅ የሰበሰበችውን መረጃ Amos (1982), Kenneth (1978) Glassie (1991)ን መሠረት በማድረግ ማህበረሰቡ ባህላዊ ቤቶችን ቅርፅን መሠረት አድርጎ በመደባቸው መንገድ እና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶችን በተግባራቸው አወግናለች፡፡ መረጃዎች በትወራው ከቀረቡት ንድፈ ሃሳቦች ጋር በመገናዘብ በገላጭ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ በትንታኔዋ የባህላዊ ቤቶቹን ስያሜ፣ አሰራር እና አገልግሎት ገልፃለች የቁሶቹን ማህበራዊ ፋይዳ በትርጓሜ አሳይታለች፡፡

አስቴር በጥናቷ በሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶችን በማየቷ ከእኔ ጥናት ጋር በመጠኑ ትገናኛለች፡፡ የሸክላ ቁሶች በእኔ ጥናት ውስጥም ከተጠኑት የቤት መገልግያ ቁሶች መካከል በመሆናቸው እና በተጨማሪም በሸክላዎቹ ላይ ያለውን ተምሳሌት አይታለች፡፡ይህ ጉዳይ ደግሞ ከኔ ጥናት ጋር ያገናኛታል፡፡

በአስቴር ጥናት ባህላዊ የቤት አሰራር የሚለው በኔ ጥናት በፍፁም ያልታየ ክፍል ነው፡፡ እኔ ያጠናሁት የቤት ውስጥ መገልገያዎችን ነው፡፡ አስቴር ግን የሸክላ ስራ ብቻ ነው ነጥላ ያየችው፡፡ ይሄ አንዱ ልዩነታችን ነው፤ እኔ የባህላዊ ቁሶቹን የተለያየ ገፅታ የቀድሞና የአሁኑን አይቻለሁ፣ የኔ ጥናት በቁሶቹ ሥራ ላይ ያለውን የፆታ ተሳትፎም የሚመረምር መሆኑ ከአስቴር ጥናት የሚለይበት ሌላ መልክ ነው፡፡

ሀብታሙ እንግዳው "በደቡብ ጎንደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ በሽም ጎድጓዲት ገጠር ቀበሌ የሻም መድሃኒአለም ሸክላ ስራ ውጤቶች የአሰራር ሂደትና ጠቀሜታ ትንተና" (2001) የሀብታሙ ጥናት ዋና አላማ በርእሱ በተጠቀሰው አካባቢ የሸክላ ስራ ውጤቶችን የአሰራር ሂደትና ጠቀሜታ መተንተን ሲሆን በተጨማሪም ከባለሙያዎቹ የህይወት ልምድ በመነሳት የባለሙያዎቹን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ቦታዎችን በመለየት ባለሙያዎቹ በሙያው ምን ያህል እንደተጠቀሙ መመርመር ነው፡፡

የጥናቱን አላማዎች ከግብ ለማድረስ መረጃ የሰበሰበባቸው መንገዶች ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት በማድረግ ነው፡፡ የሰበሰባቸውን መረጃዎች በክፍል ሁለት ባቀረባቸው ትውሮች መሠረትነት ተንትኗል፡፡

አጥኚው በጥናቱ የሸክላ ውጤቶች የአሰራር ሂደትን፣ የሸክላ ውጤቶችን ጠቀሜታ፣ ከሸክላ ባለሙያዎች ህይወት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ቃል ግጥሞች፣ ተረኮችና ምሳሌያዊ ንግግሮችን ተንትኗል፡፡

የሀብታሙ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ለኔ ጥናት አንድ ዘውግ የሆነውን የሸክላ ስራን በማጥናቱ የሱ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ይዛመዳል፡፡ ነገር ግን በእኔ ጥናት እሱ ያላያቸው ቁሶች፡- ከቅል፣ ከአለላ፣ ከእንጨት የሚሰሩ የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች ተተንትነዋል፡፡ በተጨማሪም ሀብታሙ የቁሶቹን አሰራርና ጠቀሜታ ትኩረት በማድረግ መርምሮአል፡፡ የኔ ጥናት ከአሠራርና ጠቀሜታ በተጨማሪ ቁሶቹ ከማህበረሰቡ ማንነት ጋር ያላቸውን ግንኙነት እና የተሸከሙትን መልእክት (ተምሳሌት) ተንትኖአል፡፡ በመሆኑም ይህም ቁም ነገር የኔ ጥናትና የሀብታሙ ጥናት ሌላ ልዩነት ማሳያ ነው፡፡

አበበ መርዕድ "በጎባ ወረዳ የኦሮሞ ብሔረሰብ የመመገቢያ ቁሳቁስ አሰራር አገልገሎትና ባህላዊ ፋይዳ ትንተና" (2000) በጥናቱ ዋና አላማ በጎባ ወረዳ ኦሮሞ ብሔረሰብ መመገቢያ እቃዎች አሰራር አገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ፣ የባህላዊ ቁሶቹንአሰራርና አጠቃቀምም ገልጿል፤ በተለይም ሴቶች የሚሰፏቸው ስፌቶች ምን ትዕምርት አላቸው የሚለውንም አይቷል፤ ቅርሶቹንም ቀርሶ ማስቀመጥም ከአላማዎቹ ውስጥ ተካቷል፡፡ መረጃውን የሰበሰበው በምልከታና በቃለ መጠይቅ ነው፡፡ ቀዳሚ ያለው የአጠናን ስልት የመመገቢያ እቃዎችን አሰራር፣ አገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ መተንተን ሲሆን ተከታዩ የአተናተን ዘዴ ከቃለ መጠይቅ የተገኘውን ሃሳብ ከፎቶ ግራፍ መረጃ ጋር በማቀናጀት መተንተን ነው፡፡

አበበ በጥናቱ እያንዳንዱ ቁስ ከምን፣ እንዴት እንደተሰራና የሚሰጠውን አገልግሎት የተነተነ ሲሆን የቁሶቹን ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ ገልጿል፡፡ ከዚ.ህም በተጨማሪ ቁሶቹን ከተሰሩበት ንጥረ ቁስ አንፃር አወግኖ ነው ያጠናቸው፡፡

የኔ ጥናትና የአበበ ጥናት በአብዛኛው በቅርበት የሚገናኝ ነው፡፡ አንዳንድ የአሰራር ቴክኒኮች ላይ እና የተወሰኑ አላማዎች ላይ ብቻ ነው የተለያየ ነው፡፡ ለምሳሌ በኔ ጥናት የቁሶቹን የአሁኑን እና የቀድሞ ይዞታ አይቻለሁ፤ በሙያው ላይ ያለ የፆታ ተሳትፎ እና በቁሶቹ አሰራር ላይ እየመጣ ያለውን ለውጥ አይቻለሁ፡፡

"ባህላዊ የሸክላና የቆዳ ስራ በቡሬና ወንበርማ ወረዳ" በሚል ርእስ በደግሠው ጥላሁን በ(2003) የቀረበው ጥናት አላማ ያደረገው ባህላዊ የቆዳና የሸከላ አሠራር ሂደትና ጥቅም ማሣየትና መቀረስ የሚል ነው፡፡ ደግሠው ስለ ሸክላና ቆዳ ሥራ ስታጠና በዋናነት ትኩረት ያደረገችው የአሰራር ሂደት የቁሶቹ አይነትና አገልግሎት፣ የቁሶቹ መስሪያ ጥሬ እቃዎችን መዘርዘር ላይ ነው፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀመችበት ዘዴ ምልከታና ቃለመጠይቅን ናቸው፡፡ ጥናቱንም የተነተነችው በገላጭ (በገለፃ) ዘዴ ተጠቅማ ነው፡፡ የደግሰው ግኝት የሸክላና የቆዳ ስራ በስፋት ሲመረቱ እና አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ቢሆንም በአሁኑ ሰአት ግን የመመረቱ ሁኔታ በጣም እያሽቆለቆለ መምጣቱን ጠቁሟል፡፡ ምክንያቱንም ማህበረሰቡ ለሙያው ያለው አሉታዊ አመለካከትና ፋብሪካዎች ባህላዊ ቁሶቹን የመተካት አዝማሚያ መሆኑን ገልፃለች፡፡ በተጨማሪም አጥኚዋ ጥናቱን ባካሄደችበት አካባቢ የሚኖሩ ባለሙያዎች ከማህበረሰቡ የተገለሉ እና በአካባቢው በሚከወኑ የተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የመሣተፍ እድል እንደሌላቸው ገልፃ በሌላ አካባቢ ቡዳ የሚለው የስድብ መጠሪያ በጥናቱ አካባቢ እንደሌለም አረጋግጣለች፡፡

የኔ ጥናት ከደግሰው ሚለየው በእኔ ጥናት የቆዳ ስራ ሙሉ በሙሉ ያልታየ ሲሆን የምንገናኘው ሁለታችንም የሸክላ ስራን በማጥናታችን ነው፡፡

ለመጀመሪያ ዲግሪ እና ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በሀረር ከተማና ሀረሪዎች ላይ የቀረቡ የተወሰኑ ጥናቶች ላይ መጠነኛ ዳሰሳ አደርጋለሁ፡፡ በተጠኚ ማህበረሰብና በቦታ ስለምንመሳሰል የነሱ ጥናት ምን አንስቷል፡፡ የኔ ጥናት ምንድነው የሞላው ክፍተት የሚለውን ለማየት ይጠቅማል፡፡ "የሀረሪ ብሔረሰብ ሀገረሰባዊ መድሃኒት" (2000) በሚል የቀረበ ኤልያስኤልያስ ደሳለኝ አቅርባል፡፡ በጥናቱ የዳሰሰው የሀገረሰባዊ መድሃኒቶችን ከዕፅዋት ሥር፣ ቅጠል፣ ዘር፣ ፍሬ፣ እና ከእንስሳት ተዋፅኦ የሚገኙ በማለት ከፋፍሎ አጥንቷል፡፡ ምንም እንኳን የእኔ ጥናት እና የኤልያስ ጥናት በሀረሪ ብሔረሰብ ላይ ቢሆንም እሱ ያጠናው ባህላዊ መድሃኒት ሲሆን የኔ ጥናት ደግሞ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ገለፃዊ ጥናት ነው፡፡

ተሾመ ወልደማርያም "በአደሪኛ ተረትና ምሳሌዎች (1973)፣)፣ ሀኒም ይስሐቅ "የአደሬ ብሔረሰብ የልጆች ግጥም" (1974)፣በዙ እሸቱ "የአባድር ትውፊት" (1980)፣ አለማየሁ እንግዳ፣ "የአደሬ ሠርግ" (1981) ናቸው፤ ዚነት አብዱ ረሻድ "የሀረሪ ተረቶች ሰብስብና ትንተና" (1992)፣ ፀዳለ ካሣ "የአደሬ ብሔረሰብ የሠርግ ሥርዓትና የዘፈን ግጥሞች" (1993) ናቸው።

ከዚህ በላይ የቀረቡት ሰባት ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ጥናቶች በተጠኚ ማህበረሰብና በቦታ ከኔ ጥናት ጋር አንድነት ያላቸው ሲሆን እኔ የመረጥኩት ርዕስ እነሱ ካነሡት ርእስ ጋር ምንም ዝምድናና ግንኙነት ስለሌለው ተመሳስሎና ልዩነት በማለት አልገለፅኩም። በመሆኑም ያገኘኚቸው የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች እኔ ካጠናሁት ርዕስ ጋር ግንኙነት የላቸውም።

Belle Asante በሀረሪዎች የአለላ ስራ ላይ በ2005 "womens craft guilds and the traditional basketry (GEMOT) of Harar, Ethiopia" በሚል ርእስ ጥናት አድርጋለች የጥናቷን ጨመቅ (highlights) የሚከተውን ይመስላል

> Belle Asante, 2005 traditional Harari basketry (gemot) continues to be a highly praised craft within the Harari ethnic group. However between the mid- 1970s and the mid-1990s, a sharp decline in wearing among the younger generation of women become apparent to outside researchers. NGOs and Harari alike. Moreover, the production of several gemot styles seems to have been significantly reduced in those waning years of craft production. By the late 1990s, the rewash an attempt to preserve the material culture of the Harari people, and also provide a forum for groups of Harari women to gain greater economic self-reliance through craft work.

ባህላዊው የሀረሪዎች የአለላ ስራ (Gemot) በሀረሪዎች ዘንድ ከፍተኛ ዋጋ ያለው እደ ጥበብ እንደሆነ፣በ1970ዎቹ እና በ1990ዎቹ እ.ኤ.አ መካከል ከፍተኛ መቀዛቀዝ ታይቶበት እንደነበር፣ በ199.ዎቹ እ.ኤ.አ መጨረሻ የሀረሪ ህዝቦች ቁሳዊ ባህል እንደገና እንዳንሠራራ፣ የሀረሪ ሴቶች በማህበር በመሆን ከእደጥበብ ስራው የራሳቸውን ኢኮኖሚ መርዳት እንደጀመሩ፣ ሦስት የሴቶች

ማህበራት በጀጎል ውስጥ እንደማገኙና ጥናቱን እስካጠናችበት ጊዜ በተግባር ላይ መሆናቸውን ገልጻለች፡፡

Elisabeth Dorothea Hecht "Harari Basketry an art and its function in Harari society" በሚል ርእስ ጥናት አካሂዳለች

Hecht የአለላ ስራዎቹን ከአገልግለታቸው አንፃር በስድስት ምድብ መድባ አይታቸዋለች፡፡

ከዚህ በተማሪ ጥናቷን በተለያዩ ርእሶች ቀንብባ አቅርባለች እነሱም፡- Baskets in Harari life, techniques, dyes and colors, natural dyes, Types of Baskets, arrangement of baskets in a Haraari house, basketry in olden times, the tourist trade, the basket maker and the present financial situation of the basket maker የሚሉ ናቸው፡፡ በየጥናቷ ክፍሎች በርእሱ ላይ የተጠቆሙትን ቁም ነገሮች ዳሳባቸዋለች፡፡

የ"Belle Asante እና ፡ ፡ የ'Hecth'" ስራ ከእኔ ጥናት ጋር የሚለየው እነሱ ያጠኑት የአለላ ስራን ብቻ ሲሆን እኔ ደግሞ ቁሳዊ ባህል በሚል ርዕስ የቤት ውስጥ መገልገያዎችን ማለትም የአለላ ስራዎችን፣ የሸክላ ስራዎችን፣ ከእንጨት የሚሰሩ ቁሶችን እና ከቅል የሚሰሩ ቁሶችን ነው፡፡ አንድ በሆንበት በአለላ ስራ ላይ እኔ ቁሶቹ(symbolic) ናቸው ብዬ አላለፍኩም፡፡ ተምሳሌትነታቸው ምን እንደሆነ ተንትኛለሁ፡፡

## 2.2 የንድፈ ሃሳብ ቅኝት

### 2.2.1 ቁሳዊ ባህል ምንድነው?

በዚህ ርዕስ ስር ቁሳዊ ባህል ምንድ ነው? በውስጡ ምን ምን ያካትታል? ለምን ይጠናል? እንዴት ይጠናል? የሚሉት ነጥቦች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

> በርካታ ምሁራን ቁሳዊ ባህልን በተለያየ መልኩ በይነውት እናገኘዋለን፡፡ የቁሳዊ ባህል ብያኔ መለያየት የመነጨው ቁሳዊ ባህል ፈርጁ ብዙ በመሆኑና በሥሩ የሚያካትታቸው ጉዳዮች በርካታ በመሆናቸው ጭምር ነው፡፡*(Schlereth፣ 1985፣22)*ይህንን እንደሚከተለው አበራርተውታለል፡፡

> *በአሁኑ ሰአት አጥኚዎች ቁሳዊ ባህልን የራሳቸውን መስክ አመለካከት በሚያሳይ መልኩ በተለያየ መንገድ ብያኔ ይሠጡታል፡፡ ቀዳሚ የሆኑት የቁሳዊ ባህል አጥኚዎች አንትሮፖሎጂስቶችና አርኪዎሎጂስቶች በተጨማሪ በሌሎች መስኮች ውስጥ ያሉ በርካታ ምሁራንም ቃሉን ይጠቀሙበታል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የጥበብ ታሪክ፣ የቅሪተአካልተመራማሪዎች፣ የባህል አካባቢያዊነትና ፎክለረኞች ቃሉን ይጠቀሙበታል ፡፡*

'Currently, researchers define material culture in various ways, often reflecting their disciplinary perspectives. In addition to anthropologists and archeologists who pioneered in material culture research, scholars in several other disciplines such as art history, history of technology cultural geography, and folk logistics now use the term.

Prow (1982:2)ደግሞ "material culture" የሚለው ሥያሜ ጥያቄ እንዳለበት ሲገልፅ "material culture የሚለው ሥያሜ ከአመቺነቱ አንፃር ቀድሞ ለመጠሪያነት አገለገለ እንጂ ጥያቄ የማያስነሳ ሆኖ አይደለም፣ እንዲያውም እርስበርስ የሚጋጩ ጥያቄዎችን ይዟል" ብሏል፡፡ "despite its concision adeptness, the term material culture seems unsatisfactory, indeed, self contradictory".

Glassie,1999፣ 41 "Material culture" "ቁሳዊ ባህል" ፈቃደ እንደተረጎሙት (1991፡ 15) "ቁሳዊ ባህል የሚለው ስያሜ ግራ የሚያጋባ ነው ይሉና ግራ አጋቢነቱንም ያመጣው

የባህል ፅንሰ ሃሳብ በተፈጥሮ፣ በአእምሮ ያለ ውቅርን ውስጣዊና ሊታይ የማይችልን እንደሁም ተቀያያሪ እና በአንድ ቅርፅ የማይፀና ነገር አመላካች መሆኑ ነው”፡፡

ከላይ ያለውን የሙሁራኑን ገለፃ ስናስተውል በርግጥም የቁሳዊ ባህል ሥያሜ ይሄ ነው ተብሎ መወሰን እና አንድ አቅጣጫ መያዝ እንዳልተቻለ ያስገነዝባል፡፡ ሆኖም ቁሳዊ ባህል የሚለውን ቃል/ሀረግ ወስደን ስንጠቀም እንደያዝነው ጉዳይ ይዘት ብያኔዎቹን እያጣጣምን መጠቀም ግድ ይለናል፡፡

አስተሳሰብ እያደገ እውቀት እየመጠቀ በሄደ ቁጥር ልዩነቶች በመረጃ እየጠበቡ መሄዳቸው አይቀሬ ነው፡፡ በቁሳዊ ጥናት መስክ የተፈጠረው የሃሳብ ልዩነት እያደር በሚገኙ ጥናቶች በመታገዝ መቀዛቀዝ ሊታይበት ይችላል፡፡ በአንድ አቅጣጫ የአንድ ሰው ሃሳብና የራስን ጎዳና ብቻ መርጦ ከመነጠል ይልቅ የጎንዮሽ እየተያዩ በዘርፉ ዙሪያ የተነሱ ጥያቄዎች መልስ የሚያገኙበትን መንገድ መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡ “በአለም ውስጥ በዩኒቨርስቲዎች፣ በኮሌጆችና በምርምር ተቋሞች ውስጥ ያሉ ሌሎች ሙያተኞች ስለሚሠሩት ስራ ለማወቅ ከጣረ ግን ከእነርሱ ልምድ ሊማርና መሰናክሎቹን በቀላሉ ሊያስወግድ ይችላል፡፡ የራሱን ልምድ በማካፈልም እነርሡም መሰናክላቸውን እንዲያስወግዱ ማድረግ ይችላል” (ፈቃደ 1991፡132) በማለት የመፍትሄ ሃሳብ አስፍረዋል፡፡

ቁሳዊ ባህልን የተለያዩ ምሁራን እንዴት በየኑት የሚለውን ቀጥለን እናያለን፡፡ ቁሳዊ ባህልን ራሱን እንደቻለ አንድ የጥናት ዘርፍ በመቁጠር እንደሚከተለው ፈቃደ Dorson ንን ጠቅሠው እንዲህ ብለዋል፡፡

*“ቁሳዊ ባህል” በአይን የሚታየውን በእጅ የሚዳሰሰውን ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣ እነዚህ ቁሳቁሶች የተሰሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ፣ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሠራር የቅመም አቀማመም ብልሀትን፣ የልብስ የቤት የአጥር ወዘተ አሠራርን፣ ሰዎች ልዩ ልዩ ሥራዎችን የሚያከናውኑባቸውን መሣሪያዎችና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ያጠናል ማለት ነው (ፈቃደ፣ 1991፣ 15)፡፡*

ይህ ጥቅስ በቁሳዊ ባህል ጥናት ስር ሊካተቱ የሚችሉ ነገሮች ምንምን ናቸው ብለን ለምናነሳቸው ጥያቄዎች በግልፅና በዝርዝር መልስ የሰጠ ከመሆኑ ባሻገር ቁሳዊ ባህል እራሱ አንድ የጥናት ዘርፍ ነው የሚል ሃሳብ እንዳለው እንረዳለን፡፡

Jones, 2000:9 በበኩላቸው ሥለቁሳዊ ባህል ምንነት ወይም ትርጓሜ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡-

> *ቁሳዊ ባህል ማለት ምጥን ያለ የባህል መጥሪያ ሲሆን ቁሳዊ ባህሎች በሰው የተሰሩ ሰዎች የሚገለገሉባቸው ከጥቅማቸውና ከአገልግሎታቸው ባሻገር ትርጉምና ጠቀሜታ ያላቸው ከቀድሞውና ከአሁኑ የሰው ልጅ እሴቶች አመለካከቶችና ፍላጎቶች ጋር የዘመንን መንፈስ የማህበረሰቡን ወይም የተወሰነን ቡድን ወይም የግለሰቦችን የህይወት ልምድ የሚያንፀባርቁ ናቸው የሚል ትርጓሜ ይሰጣሉ፡፡ የጆንስን ብያኔ ስንረዳው ቁሳዊ ባህል ማለት የቁሶች ሥብሥብ መሆኑን የሚገልፅ ብያኔ ነው፡፡*

Material culture is an abbreviation for material manifestations of culture, i.e. objects made by human begins the tangible things that people make, alter, and use, and to which they often attribute meanings and significance beyond utility or practicality. Artifacts relate to human values, concerns, needs, and desires both past and present. They may reflect the spirit of an age, the belief of a society or a sub group, or the experience of individualJones.

በቁሳዊ ባህል ምርምር ያደረጉትHenry Glassise (1991:1) ደግሞ ቁሳዊ ባህልን እንዲህ በይነውታል፡-"የቁሳዊ ባህል ጥናት በተፈጥሮና በባህል መካከል ያለውን ልዩነት በአእምሮአችን የምንስልበት ወዲያውም በእለት ከእለት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ፍላጎታችንን መሪ አድርገን ተፈጥሮን መልሰን መላልሰን የምንለዋወጥበትና አዲስ ቅርፅ የምናስይዝበትን መንገድ የምናጤንበት ዘዴ ነው"፡፡

Material culture records human intrusion in the environmental. It is the way we imagine a distinction between nature and culture, and then rebuild nature to our desire, shaping, reshaping, and arranging things during life.

ስለቁሳዊ ባህል ብያኔ Prown(Prowin, 1982:1)ያሉት ነገር አለ፡፡ "ቁሳዊ ባህል ማለት ቁስን በዋና መረጃነት ይዞ የቁሶቹ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ በአንድ በተወሰነ ጊዜ

በቁሶቹ አማካይነት ምን ዕምነት ሃሳበና አመለካከት እንደሚያስተላልፍ የሚፈተሽ የጥናት ዘርፍ ነው" በማለት ቁሳዊ ባህልን እንደ አንድ የጥናት ዘርፍ በመቁጠር ፈቃደ ዶርሠንን ጠቅሰው ከሠጡት ብያኔ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ብያኔ ሠጥተዋል፡፡

ቁሳዊ ባህል ማህበረሰቡ በራሱ በተሰሩ ቁሶች እሴትነቱን፣ ማንነቱን፣ ውሎውና አዳሩን፣ ሀዘንና ደስታውን፣ የቅርብ ግቡን የሩቅ ህልሙን የሚገልጽባቸው ቁሶች ናቸው፡፡ የቁሳዊ ባህል እና የማህበረሰብ ትስስር ተራ የሚባል ትስስር አይደለም፡፡ ሰው በሌለበት ጊዜና ቦታ ወክለውት የተሸከሙትን ትእምርት አስረጅ ናቸው፡፡ ይህ የያዙት ጉዳይ ተደጋግመው ቁሳዊ ባህሎችን ቢጠኑ ሚስጥራቸው የማያልቅና ጥልቅ ያደርጋቸዋል፡፡ስለሆነም ማህበረሰብ ስልጣኔ ሳይገድበው እራሱን በቁሳዊ ባህሎች ይገልጻል(ይህ ሀሳብ የአጥኚዋ ነው)፡፡

## 2.2.2 የቁሳዊ ባህል ዘርፎች

"ቁሳዊ ባህል" ከስነቃል፣ ሀገረሰባዊ ልማድና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ጋር በመሆን ፎክሎር ከሚያካትታቸው የጥናት ዘርፎች ተርታ ይመደባል፡፡ ቁሳዊ ባህል በስሩ አምስት መሠረታዊ ነጥቦችን ያቅፋል" (Dorson ውስተ ፈቃደ፣ 1991፣ 15)፡፡ እነዚህም አምስት ነጥቦች ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ፣ ሀገረሰባዊ ስእል፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስና፣ ሀገረሰባዊ ልብስ፣ ሀገረሰባዊ የምግብ አሠራር ናቸው፡ ከአምስቱ የቁሳዊ ባህል ዘርፎች መካከል የጥናቱ ትኩረት የሆነው ሀገረሰባዊየእጅ ስራ የተባለው ዘርፍ ነው፡፡

**ሀገረሰባዊ ስዕል** :-(Glasise ውስተ Dorson፣ 1972፣253)፡፡ሀገረሰባዊ ስእል የምንላቸው ከተግባራዊ አገልግሎት ይልቅ ለባለቤት ማህበረሰብ የደስታ ስሜትን የመፍጠር አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፡፡በማለት ይገልጻሉ፡፡እነዚህንየቁሳዊ ባህል ወገኖች ምሁራኑ "ሀገረሰባዊ ስዕል" (folk art) በማለት ይጠሯቸዋል ፡፡

የGlassieንብያኔ መሰረት በማድረግ ለሀገረሰባዊ ስእል የተለያዩ ምሳሌዎችን ማቅረብ እንችላለን ለአብነት የተለያዩ ቀለማትን ቀብተን የሸለምናት ቅል፣ የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ክሮች ተጠቅመን የጠለፍነው ጥልፍ (የቀሚስ፣የነጠላ፣ የመቀነት፣ወዘተ.)የጎጆአችን ግድግዳ ላይ የነደፍናቸውና የጭቃ ቀለም የቀባናቸው ስእሎች ተጠቃሾች ናቸው፡፡

**ሀገረሰባዊ ምህንድስና**:-ሌላኛው የቁሳዊ ባህል አይነት ሀገረሰባዊ ምህንድስና ሲሆን በባህላዊ መንገድ የሚሰሩ ማንኛቸውንም አይነት የምህንድስና ሥራዎች ይመለከታል (Roberts ውስተ Dorson፣ 1972፣281)፡፡ ለምሳሌ የሰዎች መኖሪያ ቤት፣ የከብቶች ማደሪያ በረት፣ ዳስ፣ የጭስ ቤት፣ ወዘተ. በአስረጅነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

"ሀገረሰባዊ ምህንድስና ከላይ የተጠቀሱትን ባህላዊ የምህንድስና ሥራዎች ውጤቶችን ብቻ አይደለም የሚመለከተው፡፡ ይልቁንም ውጤቶቹ የተገኙበትን (የተሰሩበትን) ንጥረ ቁስ፣ በሥራው ሂደት አጋዥ የነበሩ የተለያዩ መሣሪያዎችን እንዲሁም የአሰራር ጥበቡን ወዘተ አብሮ ይመለከታል" (Roberts ውስተ Dorson፣ 1972፣281)፡፡

**ሀገረሰባዊ ልብስ**፡-የልብስ ዋነኛ አላማ ከላይ እንደተጠቀሰው የተራቆተ ገላን ለመሸፈን ቢሆንም ከዚህ ባሻገር ግን ለተለያዩ አገልግሎቶች ይውላል፡፡ ይህንን ነጥብ አስመልክተው Yodor "ሀገረሰባዊ ልብስ፣ የሰዎችን አፋዊ ማንነት ለአካባቢያቸው ማህበረሰብ ወይም ከአካባቢያቸው ራቅ ብለው ለሚኖረ ለባዕድ ወገኖች ገልጦ የሚያሳይ መለያ ነው" (Yodor ውስተ Dorson፣1972፣295) በማለት ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም ልብሱ የለባሹን ሰው ፆታ፣ ዕድሜ፣ የመኖሪያ አካባቢ፣ ብሄረሰብ፣ የስራ መስክ፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ወዘተ. ለተመመልካቹ የመንገር ባህርይ አለው ፡፡

እንደ Yodor ገለፃ ሀገረሳባዊ ልብስ በአንድ አካባቢ የመወሰን ባህርይ አለበትና ከቋንቋ ዘዬ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ምክንያቱም ለቋንቋ አካባቢያዊ ዘዬ እንዳለው ሁሉ ለልብስም አካባቢያዊ ልብስ አለና፤ ይህም "ሀገረሳባዊ ልብስ" ያለነው ነው፡፡

**ሀገረሰባዊ የምግብ አሰራር**፡-"ሀገረሳባዊ የምግብ አስራር ከቁሳዊ ባህል አይነቶች አንዱ ሲሆን ሰዎች በአካባቢያቸው የሚያመርቷቸውን ጥሬ ነገሮች ተገልግለውና አካባቢ በቀል በሆነ እውቀት ተመርኩዘው ለእለት ጉርሳቸው የሚያዘጋጁትን ምግብ ይመለከታል" (Yodor ውስተ Dorson፣1972፣325)፡፡

> *ሀገረሳባዊ ምግብን ጉዳዩ ብሎ የሚያጠና ተመራማሪ በጥናቱ ሂደት፣ ምግቡ ከምንና እንዴት እንደሚሰራ መቼና በምን መልኩ ለምግብነት እንደሚውል፣ በምን ባህላዊ ዘዴ ለረዥም ጊዜ መቆየት እንደሚችል፣ ምግቡ ለባለቤት/ተጠቃሚ ማህበረሰቡ የሚሰጠው ማህበራዊና ሥነ አእምሯዊ ጥቅም ምን እንደሆነ፣ ከምግቡ ጋር ተያይዞ የሚወሱ ቃላዊ*

*ትውፊቶች ምንምን እንደሆኑ ወዘተ. ትኩረት ሰጥቶ ሊፈተሽ ይገባዋል (እንደላይኛው፣ 325፡፡)*

ከዚህም ባሻገር ማህበረሰቡ ምግቡን ባህላዊ እሴቱ አድርጎ የወሰደበት መነሻ ምክንያት ምን እንደሆነ አብሮ ሊያጤን ይገባዋል፡፡

ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ፡-በቁሳዊ ባህል ጥናት ስር ከሚዳሰሱት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ሀገረሳባዊ የእጅ ስራ ነው ሲሉ (Dorson 1972፣2) ይገልፃሉ፡፡ ሀገረሰባዊ የእጅ ስራዎች የምንላቸው የማህበረሰቡን ባህል የሚያንፀባርቁትን፣ በእጅ የሚያበጇቸውን፣ የአሠራር ዘዴያቸውና ቅርፃቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገሩ የቆዩትን የሚመለከት መሆኑን ይናገራሉ፡፡

የእጅ ሥራ የሚለው ፅንሰ ሃሳብ የሰው ልጅ በአእምሮው ውስጥ ያሰበውን ዲዛይን በአካባቢው ከሚገኝ ንጥረ ነገር ጋር በማቀናጀት በእጁ የሚሠራውን ረቂቅ የሆነ ጥበብ ያረፈበትን ቁስ የሚገልፅ ነው፡፡ የእጅ ሥራ ብለን የምንጠራቸው ሸክላ ስራ፣ ስፌት፣ የእንጨት ስራ ወዘተ. አካቶ ይይዛል፡፡ “ሐገረሰባዊ የእጅ ስራ ደግሞ በባህላዊ ዘዴ የሚሰሩ የእጅ ስራዎችን ይመለከታል” (Robert, 1972፣233)፡፡

ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ የምንለው ቁስ የለመዳ ሂደቱ ምን እንደሚመስል (Robertm,1972:232) እንዲህ በማለት ይገልፃሉ፡-

> One can say generally that folk crafts are traditional crafts. It is indeed in the crafts that one can observe with special clarity the operation of traditional until relatively recent times. Craft techniques and designs were passed down with on family for many generation or were transmitted by the apprentice system where a boy learning the craft served for as long as seven years under a master crafts man (Robert, 1972: 232).

ከዚህ የምንገዘበው ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ የአሰራር ቴክኒኩም ሆነ የዲዛይኑ ከየት መጥነት ሲጤን ከቤተሰብ እየተላለፈ ለበርካታ ትውልድ ሊደርስ የሚችል እና እወቀቱም ሀገር በቀል መሆኑን ጭምር ነው፡፡ የእጅ ስራ ጥበብ በዘመናዊ መልኩ ትምህርት ቤት ገብተው

የሚቀስሙት ሳይሆን፤ አዲሱ ትውልድ ከቀደመው ትውልድ ባህላዊ በሆነ ዘዴ ከቤተሰቡም ሆነ ከማህበረሰቡ በሙያው ከተካኑ ሰዎች ሊማረው የሚችል ጉዳይ መሆኑንም እንረዳለን፡፡

*ሌላው ከግንዛቤ መግባት ያለበት ቁም ነገር አንድ የእጅ ስራ ሀገረሳባዊ የእጅ ስራ ለመባል የግድ በርካታ ዘመናትን ያስቆጠረና ጥንታዊ መሆን አይጠበቅበትም፡፡ ጥንታዊነትና ሀገረሰባዊነት የራሳቸው የሆነ መደጋገፍ በመሀላቸው ቢኖርም አንዱ ሌላውን መሆን ግን አይችልም፡፡ ሀገረሰባዊነት በመሠረታዊነት የሚለካው ቀጣይነቱና ህልውናው የሚረጋገጠው በቅብብሎሽ አዝልቆ የሚይዘው ባህላዊነቱ ላይ ነው ይላሉ (Robert፣ 1972፣234)፡፡* ስለዚህ አዲስም ሆኖ ሀገር በቀል የሆነና ባህላዊነቱን ጠብቆ በቅብብል የሚዘልቅ ከሆነ ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ከመሆን የሚያግደው የለም፡፡

Oring የላይኛውን ሃሳብ በመደገፍ"the designation "folk objects is not restricted to objects only from the past. New folk objects are continually emerging" በማለት ሃሳባቸውን አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም ሀገረሳባዊ የእጅ ሥራዎች ስር የሚካተቱት እና ሀገረሰባዊ ካልሆኑት የሚለዩት በእድሜ ጠገብነታቸውና አዲስ በመሆናቸው ሳይሆን ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ለመባል የማህበረሰቡን ማንነት የሚገልፁ፣ የማህበረሰቡን የፈጠራ ችሎታ የሚያንፀባርቁ፣ የማህበረሰቡን ባህል ወግ እና ልማድ ጠብቀው የተሰሩ፣ ተሰተላልፎአቸውም መደበኛ ባልሆነ መልኩ ከቤተሰብ ወደ ቤተሰብ አሊያም ከትውልድ ወደ ትውልድ የሆኑትን ቁሶች እንደሆነ ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡

የሀገራችንን ሀገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ስንፈትሽ ሰዎች ለእለት ተግባራቸው የሚገለገሉባቸው፣እርቃናቸውን ለመሸፈን የሚሰሯቸው ፣ለማጌጫ የሚጠቀሙባቸውን ፣ለማህበረሰቡ ግልጋሎት የሚሰጡ እንዲሁም የራሳቸው የሰሪዎቹ እና ሰሪዎቹ የበቀሉበት የጠቅላላው ማህበረሰብ መገለጫ የሆኑና ኢመደበኛ በሆነ መልኩ ከቀዳሚው ትውልድ በተለይም ከቤተሰቦቻቸው ወርሰው ወይም ለምደው የሰሯቸውና እየሰሯቸው ያሉ በርካታ ሀገረሰባዊ የእጅ ስራዎች መኖራቸውን እንገነዘባለን፡፡

ስለኢትዮጵያውያን የእጅ ስራዎች ጥንታዊነት (Richard Pankhurst1964፣221)እንዲህ ብለዋል "ከኢንዱስትሪ አብዮች በፊት እንደ አውሮፓውያን ሁሉ ኢትዮጵያውያን ህዝቦች

ፍላጎታቸውን ለማርካትእናመጠቀሚያበመሆን የሚያገለግሏቸውን ቁሳቁስ ለመስራት ከመጀመሪያዎቹ ዘመናት ጀምሮ የራሳቸው የሆኑ የእደ ጥበብ ኢንዱስቲሪዎችን ያራምዱ ነበር"፡፡

Silverman ስለ ኢትዮጵያውያን ሀገረሰባዊ የእጅ ስራዎች እንዲህ ብለዋል "የሸክላ ስራ ውጤቶች፣ የስፌት ሥራ የሆኑ ቁሳቁሶች በየሰው ቤት ሁል ጊዜም መጠቀሚያዎች ናቸው" (Siliverman 1999፣51)፡፡ በ Siliverman መፅሐፍ ውስጥ አአርትክል የፃፉት አህመድ ዘካርያ ስለ ስፌት እንዲህ ሲሉ ገልፀዋል፡፡

"Basket making is an ancient art found in many societies throughout the world. Nevertheless, every basket tradition has its unique dimensions and not all traditions share equal weight in the realm of art appreciation. (Ahmad Zakariya, 1999፣51)"

የአለላ ስራ ጥንታዊ መሆኑን እና በአለም ላይ ብዙ ማህበረሰቦች ዘንድ ሞያው እንደሚታወቅ፣ ሁሉም የስፌት ስራ የራሱ የሆነና ከሌሎች የተለየ ቅርፅ እንዳለው፣ ሁሉም ባህል ለስፌቶቹ ያለው ግምትና አድናቆት ተመሳሳይ ሊሆን አይችልም በማለት አጠቃላይ ለስፌት ያላቸውን ሃሳብ ገልፀዋል፡፡ አህመድ ዘከሪያ ስለ አለም ብቻ አውርተው ዝም አላሉም ስለ ሀረሪዎች ስፌትም የሚከተለውን ብለዋል፡-

"ሀረርን የጎበኙ በርካታ ስዎች በሀረር ሴቶች ለምዕተአመት እየተሰፉ ያሉትን የሚያምሩ የስፌት ስራዎች አድንቀዋቸዋል፡፡ ዛሬ ዛሬ ታዋቂ የሆኑት የሀረር የስፌት ስራዎች ለጥንታዊቷ የሀረር ከተማ በቱሪስት መስህብነት ዋና እና ተጠቃሾች ናቸው፡፡... የስፌት ስራ ለሀረሪ ሴቶች ማንነት ትእምርት ነው (አህመድ ዘከርያ ውስተ Siverman 1999፣ 51)፡፡ በማለት የሀረሪ ስፌቶች ብዙ የሚነበቡ ትእምርቶች እንዳሏቸውና ውብና ማራኪ መሆናቸውንም ጭምር ገልፀዋል፡፡

### 2.2.3 የቁሳዊ ባህል ጥናት አስፈላጊነት

ይህ ጥናት ሊጠና ይገባዋል ወይስ አይገባውም የሚለውን የምሁራን ሀሳብ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

“ቅርሶች በባህል፣ በስነውበት ይዘታቸው ተደናቂነት፣ ውበትና ታሪካዊነት ያላቸው ውርሶች ሆነው በተሰሩበት ዘመን ለተለያየ አይነት አገልግሎት ማለት ለሀይማኖት መገልገያ፣ ለንግድና ለልውውጥ፣ ለመከላከል፣ ለማህበራዊ ግንኙነት፣ ለቤት አገልግሎት፣ ለጌጥ ለክብርና ለዝና ማትረፊያ ወዘተ ታስበው የተሰሩ ናቸው” (በላይነህ፣ 1981፣8)።

ቁሳዊ ባህል የፈለቀበትን ማህበረሰብ ሁለንተና ገላጭ ነው። አስቀድሞ ማህበረሰቡ ይሁንኝ ብሎ ቁሱን ሲሰራ እሡን ሊወክሉ፣ ሊገልፁ የሚችሉ የሚነበቡ በርካታ ጥበባት አሳርፎበት ነው የሚሠራው።

ቁስን ማጥናት ማለት የቁሱን ባለቤት የሆነውን ማህበረሰብ ማጥናት ማለት ነው።ማራኪ ውበት ያረፈባቸው ቁሶች ስለፈጠራቸው ማህበረሰብ የሚናገሩት ነገር አላቸው። እድሜ ጠገብ የሆኑ ቁሶች ባለቤት ማህበረሰቡ በሌለበት ጊዜና ቦታ፣ ባለቤት ማህበረሰቡን ማግኘት በማይቻልበት ሁኔታ ስለዛ ማህበረሰብ እድገትም ሆነ ውድቀት፣ ደስታም ሆነ ሀዘን፣ በርካታ መረጃዎች ይሠጣሉ።

ቁሳዊ ባህል ድሮን በመስታወትነት የሚያሳየን ነው። የሌለንበትን ዘመን ምን እንደነበር የምንረዳበት ነው። ቁሳዊ ባህል የድሮና ያለፈ ብቻም አይደለም። ማህበረሰቡን ከነቁሱ ዛሬም እናገኘዋለን። በዚህ ጊዜ ግን ቁሶቹ ያላቸውን ትርጉም ከራሱ ከማህበረሰቡ ጠይቀን መረዳትና መረጃ መሰብሰብ እንችላለን።

Schlerth ደግሞ “ቁሳዊ ባህሎች እድሜ ጠገብ ቁሶች ብቻ ሳይሆኑ ያለፈውን ጊዜ በተጨባጭ ለዛሬው (ለአሁኑ) ጊዜ ያቆዩም ናቸው” Schlerth(1985፣24)። በማለት ቁሳዊ ባህሎች መጠናት እንዳለባቸው የሚጠቁም ሀሳብ ሰንዝረዋል። “material culture is notonly the most ancient of time’s shapes; it is also a tangible form of a past time persisting in present time.”

Prownም እንደ Glassie እና Schlerth ሁሉ “ቁሳዊ ባህሎች ተፈጥሮአዊና ተምሳሌታዊ ተግባር ስላላቸው፣ ስለማህበረሰቡ መረጃ ስለሚሰጡ፣ ማህበረሰቡን ሊወክሉ የሚችሉ እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ እውነታዎችን የሚገልፁ በመሆናቸው ይጠናሉ” (Prown 1982፣1-4)።

ምሁራኑ በተለያየ አገላለፅ ይግለፁት እንጂ አጠቃላይ ሀሳባቸው ምን ላይ ነው ትኩረቱ የሚለውን ስናስተውል ቁሳዊ ባህልን በምናጠናበት ጊዜ ቁሱን ብቻ አይደለም የምናጠናው ቁሱን የፈጠረውን ማህበረሰብ ነው የምናጠናው የሚል አንድምታ አላቸው፡፡ በመሆኑም Glassie እንደጠቀሱት ቁሳዊ ባህልን ማጥናት ማለት ማህበረሰቡን ማጥናት ማለት ነው Glassie፣ 1999፣1 ያሉትን ሃሳብ በቀጥታም ባይሆን የሚያጠናክሩ ሃሳቦች ናቸው፡፡

Fleming የ'Glassie"ን ሃሳብ በማጠናከር ማንኛውም ባህል ኋላቀርም ይሁን ዘመናዊ ህልውናው እውን የሚሆነው በጥበባዊ ተግባሮች (artifacts) አማካይነት ነው፡፡ ቀዳሚ የሁኑት የሰው ልጅ ጥበባትና ቁሶች ጠቀሜታቸው የተለያየ ፍላጎቱን ለማሳካት ነበር፡፡… በመሆኑም ሰውን ለማወቅ በሱ የተሰሩ ነገሮችን ማጥናት የግድ ይላል በማለት ከGlassie ጋር ተደጋጋፊ ሃሳብ ሠንዝረዋል፡፡

### 2.2.4 ቁሳዊ ባህልን የመመደቢያ መስፈርቶች

ቁሳዊ ባህል ስፋትና ጥልቀት ያለው ዘርፍ በመሆኑ፤ ጥናቱን የተቀላጠፈና ግልፅ ለማድረግ በቁሳዊ ባህል ዙሪያ የሚያጠና ተመራማሪ መድቦ ቢያጠናው የተሻለ ይሆናል፡፡ ነገርግን መመደብ አስፈላጊ ስለሆነ በዘፈቀደ አይመደብም ተጨባጭ መስፈርቶችን ይዞ በወገን በወገኑ ማወገን የግድ ይላል፡፡ በመሆኑም እንደ Prown ያሉ ምሁራን በየምድብ ክፍሉ መድቦ ማስቀመጡ አስቸጋሪ በመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ተግባር ነው ሲሉ ያስገነዝባሉ (Prown 1982፣1)፡፡

በዘርፉ ያሉ ምሁራን ቁሳዊ ባህል እንዴት መመደብ እንዳለበት የየበኩላቸውን እንደሚከተለው አብራርተዋል፡፡ Prownከመስሪያ ንጥረ ቁስ፣ ከአሠራር ጥበቡ እና ከአገልግሎቱ አንፃር መከፋፈል ይቻላል ሲል Ames ደግሞ ከዘመን፣ ከባለሙያ፣ ከሥልት፣ ከመሥሪያ ንጥረ ቁስ፣ ከአገልግሎት እና ከቅርፅ አንፃር መድቦ ማየት ይቻላል በማለቱ በቁጥርም ሆነ በሃሳብ ሰፋ አድርጎ አቅርቧል (Prown፣ 1982፣2፤Ames፣ 1978፣20)፡፡

መሥሪያ ንጥረ ቁስ፣ አሠራር (ሥልት) እና አገልግሎት በጋራ ያነሷቸው ነጥቦች ናቸው፡፡ ነገር ግን Prown ም ሆነ Ames ያሳዩቸው የመመደቢያ መስፈርቶች የራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎን አሏቸው በማለት ገልፀዋል፡፡

### 2.2.5 የቁሳዊ ባህል አንፃሮች ወይም ሞዴሎች

በዚህ ክፍል የቁሳዊ ባህል አንፃሮችናየአተናተን ሂደቶች ምን እንደሚመስሉ ምሁራንን ዋቢ በማድረግ ገለፃ የሚሠጥበት ሲሆን የጥናቱንም አተናተን የትኩረት አቅጣጫ ያሳያል፡፡ ቁሳዊ ባህልን የጥናቱ ዋና አካል ያደረገ ተመራማሪ በዋናነት ሊያጤናቸው የሚገቡ ሞዴሎችን Schlerteh በ9 መድቦ አሳይቷል፡፡ እነሱም፡- ባህላዊነት፣ አገልግሎት፣ መዋቅራዊነት፣ ጥበብን አመላካችነት፣ ተምሳሌታዊነት፣ ባህሪይ አመላካች፣ አካባቢያዊነት፣ ማህበራዊነት፣ማህበረሰብ ጠቃሽነት ሲሆን Fleming ደግሞ ያመላከታቸው ነጥቦች 5 ናቸው፡፡ ነጥቦቹም የቁሱን ታሪክ ማጥናትን ፣ምስሉን ማጥናት፣ ተግባሩን ማጥናት፣ የቁሱን አወቃቀር ከነባለሙያው ማጥናት እና የተሰራበትን ንጥረ ነገር ከአካባቢው ጋር ማጥናት ናቸው (Fleming 1974፣156)፡፡

Fleming ካሳያቸው አምስት ነጥቦች ይልቅ የ "Schlereth" ዘጠኝ ሞዴሎች የተሻሉና የተጠኚውን ቁስ ተምሳሌት አውጥቶ ለማየት እድል ስለሚሰጡ የሱን ሞዴሎች እንደሚከተለው አብራራለሁ፡፡

- **ጥበብን አመላካችነት፡-** ሞዴሉ ከተጠኚ ቁሶቹ ጥበብ ወይም ማራኪነት የሚፈልግ እና ይህንንም አጉልቶ የሚገልፅ ነው፡፡
- **ተምሳሌታዊነት፡-** ቁሶችን በተምሳሌታዊነት ወይም የወከሉትን ጉዳይ የሚፈትሽ ሞዴል ነው፡፡
- **ባህላዊነት፡-** ይህ ሞዴል ተጠኚ ቁሱ የአንድን ቡድን ወይም ማህበረሰብ ባህል ያመለክታሉ ወይ የሚለውን ጥያቄ አንድንመረምር ያደርጋል፡፡
- **አገልግሎት ሰጪነት፡-** የሚጠኑት ቁሶች ጥቅምና አገልግሎታቸው ምንድነው? በአሁኑ ሰአት አገልግሎት ላይ ካሉ አስቀድሞ ሲሰሩ ይውላሉ ለተባለለት ጉዳይ ነው? ወይስ አገልግሎታቸው ተቀይሯል? አገልግሎት ላይም ካልዋሉ ለምን የሚል ጥያቄ እንድናነሣ የሚያደርግ ሞዴል ነው፡፡
- **መዋቅራዊነት፡-** ቁሱ ከምንና እንዴት እንደሚሠራ፣ በአሠራሩ ሂደት በአገልግሎት ላይ የሚውሉ መሣሪያዎች ምንምን እንደሆኑ በጥናቱ ትኩረት እንዲሠጣቸው የሚያደርግ ሞዴል ነው፡፡

- አካባቢያዊነት፡- ተፈጥሮአዊ ነገሮች ለምሳሌ መልክአምድር፣ የአየር ፀባይ በቁሱ ላይ የሚያመጣው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅእኖ ምንድነው? የሚል ጥያቄ እንድናነሣ የሚያደርግ ሞዴል ነው፡፡
- ባህሪይ አመላካችነት፡- ይህ ሞዴል ቁሱ ባለቤት በሆነው ማህበረሰብ ውስጥ መገኘቱ እና አገልግሎት መስጠቱ በማህበረሰቡ ላይ ያሣደረው ተፅእኖ ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ እንድንመልስ የሚያደርግ ነው፡፡
- ማህበራዊነት፡- በማህበረሰብና በቁሶች መካከል ያለው ተራክቦ ቁሶች ለማህበረሰቡ፣ ማህበረሰቡ ለቁሶች ያላቸውን ሚና ምንድነው? የሚለውን እንድናይ የሚያደርግ ሞዴል ነው፡፡
- ማህበረሰብ ጠቃሽነት፡- ይህ ሞዴል ቁሶቹ የማናቸው? መቼ ተሠሩ? ማንሠራቸው ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት ይጠቅማል፡፡

### 2.2.6 ቁሳዊ ባህልን የመተንተኛ ሂደቶች

ቁሳዊ ባህልን መተንተኛ አድርገን የምንገለግልባቸው ሞዴሎች ከላይ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ ሞዴሎቹ የቀረቡት ጥናቱ ከነሡ በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ እንዳስፈላጊነቱ እንደሚገለገልባቸው ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ ሞዴሎቹን ብቻ መጠቀም በቂ ስላልሆነ በትንታኔ ላይ ልንጠቀምባቸው የሚገቡ ሂደቶች እንዳሉ ምሁራን ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም በጥናቱ ይዘን የተነሳነውን ጉዳይ ለማሣየት አቅም ስለሚፈጥሩልን በነሡ መቃኘት የግድ ይላል፡፡

Prown ቁስን መሠረት ያደረገ ትንታኔ ሊያልፍ ይገባዋል ያላቸው ሂደቶች ሦስት ናቸው፡፡ እነሱም በገለፃ (Description)፣ በትርጓሜ (Dedication) እና በመላምት (speculation) ናቸው Prown፣ 1982፣7-10፡፡ Fleming በበኩሉ የመተንተኛ ሂደቶቹን Prown በጠቀሳቸው በሶስቱ ላይ አንድ አክሎበታል፡፡ Fleming የጨመረው አንዱ የመተንተኛ ሂደት "ግምገማ" (Evaluation) የተባለ ነው (Fleming፣ 19754፣ 154-161)፡፡

#### 2.2.6.1 ገለፃ

በትንታኔ ወቅት ገለፃ ግንባር ቀደም ተግባር ነው፡፡ ናሙና ቁሱን የተመለከተ ሰው ቁሱን ላላዩ ሰዎች የቁሱን ምስል በአእምሯቸው እንዲከስቱ ማድረግን ይመለከታል፡፡ ገለፃ

ስናደርግ ቁሱ የተሰራበት ንጥረ ነገር፣ ቅርፁ፣ ቀለሙ፣ ክብደቱ፣ ርዝመቱ ወዘተ. በገለፃው መካተት ይኖርባቸዋል፡፡ በገለፃው ክፍል የቁሱንም ስዕል አካቶ ማቅረብ ቁሱን ይበልጥ ተጨባጭ ያደርገዋል፡፡

### 2.2.6.2 ትርጓሜ

ትርጓሜ በናሙና ቁሱና በባለቤት ማህበረሰቡ መካከለ የተፈጠረውን መስተጋብር የምናጤንበት እና የምንፈልግበት ነው፡፡ ትርጓሜ ቁሱ ከቁስነት ባሻገር ስለ ማህበረሰቡ የተሸከመውን ትእምርት ፈልፍለን የምናወጣበት ነው፡፡

ትርጓሜው በገለፃው ላይ ሥለገለፅናቸው ከቅርፅ፣ ከቀለም፣ ከርዝመት፣ ከክብደት፣ ወዘተ. ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሊገለፅ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- የቅርፁ መሾል፣ መጠማዘዝ ወዘተ ስለማህበረሰቡ የሚነግረው ጉዳይ ሊኖረው ይችላል፡፡ ቀለሙም፣ ክብደቱም ሌሎቹም የሚያስተላልፉት ትርጉም ስላለቸው የቁሳዊ ባህል ተመራማሪ በጥንቃቄ ሊመረምራቸው የሚገቡ ቁም ነገሮች ናቸው፡፡

### 2.2.6.3 ግምገማ

ግምገማ ስለ ቁሱ ገለፃ ከሰጠን፤ትርጓሜውን ፈልፍለን ካሳየን በኋላ የምንፈፅመው ሦስተኛ ተግባር ነው፡፡ በገለፃው ምንነቱን ያሣወቅነው ቁስ በትርጓሜው ደግሞ ገለፃው ላይ እንደዋዛ የታለፉ ቀለማት፣ ቅርፅ፣ ርዝመት፣ ክብደት ባለቤት ማህበረሰቡን እንዴት ገለፀውታል ማህበረሰቡስ ራሱን በቁሶቹ እንዴት አሳይቷል ማንነቱን እንዴት ነው እንዲወክሉት ያደረገው ብለን ስናጤን ግምገማ ተከትሎ ይመጣል፡፡ ቁሱ ላይ ያረፈውን ጥበባዊ (ስነ ውበታዊ) ብቃት ይመለከታል፡፡ ለምሳሌ፡- የአለላ ስራ ከሆነ የስጋጃዎቹ አጣጣል፣ የቀለማቱ ውህደት፣ በአእምሮ ውስጥ የሚፈጥሩት ሀሴት፣ የባለሙያው ብቃት፣ የጥበባት የተለያየ ስልት፣ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም የግምገማ ሂደት አንድን ቁስ ከሌላ ቁስ ጋር በተለያየ መስፈርት በማወዳደር ተመሳስሎና ልዩነታቸውን ይጠቁማል፡፡

### 2.2.6.4 ጥቆማ (የግኝት ትንተና)

ይህ የትንተና ሂደት ከገለፃ፣ ትርጓሜና ግምገማ በመቀጠል የሚመጣ ነው፡፡ በሦስቱ ሂደት የተገኙትን መረጃዎች አጥኚው ከራሱ እውቀት ጋር በማቀናጀት የሚተገብርበት ነው፡፡ አጥኚው ይሄንን ሂደት ሲያከናውን ስለ ቁሱ በቂ መረጃ ስላለው ከቁሱ ርቆ

የሚያከናውነው ተግባር ነው፡፡ በዚህ የትንተና ሂደት የሚተገበሩ ዋና ዋና ጉዳዮች በጥናቱ የተገኙ መረጃዎች ስለ ቁሳዊ ባህል ከተሠነዘሩ ቲዎሪዎች ጋር ማጣጣም፤ ጥናቱን ተዛማጅ ከሆኑ ጥናቶች አንፃር ማየት፤ መረጃዎች ከተገኙ አገር በቀል ንድፈ ሃሳቦችን መቀመር (ከተቻለ) አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ የሚገኙት ቁሶች የሚተነተኑት፡- ከላይ የተጠቀሱትን የቁሶች የመመደቢያ መስፈርቶችን፣ ሞዴሎችን እና የመተንተኛ መንገዶችንታሳቢ በማድረግ ቁሶቹን በተመረጠ መስፈርት በማወገን ነው፡፡ ቁሳዊ ባህል እንዴት መመደብ እንዳለበት Prown ከመስሪያ ንጥረ ቁስ፣ ከአሰራር ጥበቡና ከአገልግሎቱ አንፃር መከፋፈል ይቻላል ሲሉ፤ Ames ደግሞ ከዘመን፣ ከባለሙያ፣ ከስልት፣ ከመስሪያ ንጥረ ቁስ፣ ከአገልግሎት እና ከቅርፅ አንፃር መድቦ ማየት ይቻላል ብለዋል (Pronw 1982: Ames, 1978:20)፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑት የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች አገልግሎታቸውንእና አሰራራቸውን ለማሳየት እና ለመተንተን ተስማሚ ሆኖ የተገኘው መስሪያ ንጥረ ቁስን መሰረት አድርጎ መመደቡ ነው፡፡ በመሆኑም ቁሶቹ ከተሰሩበት ንጥረ ቁስ አንፃር ተመድበዋል፡፡ የ “Schlereth”ን ዘጠኝ ሞዴሎች በመጠቀም የተጠኘውን ቁስ ባህላዊነት፣ አገልግሎት ሰጪነት፣ መዋቅራዊነትና ተምሳሌታዊነት ወዘተ. ለመፈተሽ ተገልግዬባቸዋለሁ፡፡ በሞዴሎቹ ብቻ መጠቀም በቂ ስላልሆነ ትንታኔ ላይ ልንጠቀምባቸው የሚገቡ Prown እና Fleming ያቀነቀኗቸውን ሂደቶች በማዛነቅ በገለፃ፣ በትርጓሜ፣ በግምገማና በጥቆማ የተመረጡ ናሙና ቁሶች ትንተና ተሰጥቶባቸዋል፡፡

## 3. የተጠኚ አካባቢውና የነዋሪ ብሔረሰብ ዳራዊ መግለጫ

በዚህ ምዕራፍ የተጠኚ አካባቢውና የነዋሪው ማህበረሰብ ዳራዊ ሁኔታ ትኩረት ተሰጥቷቸው ተዳሰዋል፡፡

### 3.1 የተጠኚ አካባቢው ዳራዊ መግለጫ

የሀረሪ ክልል በኢትዮጵያ ከሚገኙት ዘጠኝ ክልሎች አንዱ ነው፡፡ክልሉ በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍልይገኛል፡፡ክልሉ በሁሉም አቅጣጫ ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ጋር ይዋሰናል፡፡ ክልሉ ከሀረሪዎች በተጨማሪ አማራ፣ አርጎባ፣ ኦሮሞ፣ ሶማሌ፣ ጉራጌ እንዲሁም ሌሎች በቁጥር ጥቂት የሆኑ ብሔረሰቦችን አቅፎ የያዘ ነው (Azime A. Hassen, 2000, 1)፡፡ ሀረር ከተማ የተመሠረተችበትን ትክክለኛ ቀን ማስቀመጥ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ነገር ግን ከአንድ ሺ አመት በፊት እንደተመሰረተች ይነገራል (Azime A. Hassen, 2000, 1)፡፡ ሀረር መልክአምድራዊ አቀማመጧ ባደረገላት እገዛ በአካባቢው በንግድ እንድታድግ አድርጓታል፡፡ ከተለያዩ የምስራቅ አፍሪካ የንግድ ተቋማት ጋር ግንኙነትም ነበራት፡፡

ሀረር በምስራቅ ኢትዮጵያ በቀዳሚነት የምትጠቀስ ታሪካዊ ከተማ ነች፡፡ ከአዲስ አበባ በስተምስራቅ 525 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ከድሬዳዋ በስተምስራቅ 51 ኪ.ሜ ላይ ነች፡፡ ሀረር በከተማነት ተዋቀረች የሚባልበት ጊዜ ከአስራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን በፊት ነው (A. Muheimen, 2001, 2)፡፡

ከሐረሪ ክልላዊ መንግስት እስታትስቲክስ ቢሮ የተገኘው መረጃ በ1999ዓ.ምበተደረገው የህዝብና የቤቶች ቆጠራ የክልሉን አደረጃጀትና የህዝብ ብዛት እንደሚከተለው ይገልፃል፡፡ ክልሉ በዞን ወይም በወረዳ የተከፋፈለ አይደለም፡፡ አጠቃላይ የሀረር ከተማ ቀበሌዎች ብዛት 19 ሲሆን 17 የቀበሌ ገበሬ ማህበራት አሏት፡፡ አጠቃላይ ስፋቷ 340 ስኩዌር ኪ.ሜ ነው፡፡ የህዝብ ብዛቷ በሀረር ከተማ 99,368 ሲሆን በገበሬ ማህበራት 84047 በድምሩ 183,415 ነው፡፡

በዩኔስኮ በቅርስነት ከተመዘገቡት መስህቦቻችን ውስጥ ሐረር አንዷ ናት፡፡ በቅርስነት የተመዘገበችው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2006 ነው፡፡ የቱሪዝም መዳረሻ በመሆን ከቱሪስት የሚገኘውን ገቢ ለሀገራችን በማስገኘት ላይ ትገኛለች፡፡ ፍሰቱም ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በቱሪስቶች ከሚጎበኙት መካከል በሀረሪዎች የተሰፋ የተለያዩየአለላ

ስራ፣ ጥንታዊ የቤት ውስጥ መገልገያዎችና አልባሳት መሆናቸውን በቆይታዬ አረጋግጫለሁ፡፡

ሐረር በተለያዩ ማህበረሰብ የተለያየ አጠራር አላት፡፡ ኦሮሞዎችና ሶማሌዎች "አደሬ" ሲሏት፤ አማሮች እና አውሮፓውያን "ሐረር" ይሏታል፤ አፋሮች "ሁሩር" ይሏታል፤ ሀረሪዎች ደግሞ "ጌይ" ይሏታል፡፡ አቶ አብዱ መሀይመን ጌይ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲህ ሲሉ ገልፀወል፡፡

"ሀረሪዎች አደሪዎች ከተማችንን ጌይ ይሏታል፡፡ እራሥጌ፣ ግርጌ እንደምንለው፡፡ ጌይ ማለት ራስ ማለት ነው፣ የከተማ ሰው ማለት ነው ሀረር በማህበራዊ እድገት አድጎ ራስ ወይም ዋና የሚባል ደረጃ ደርሷል ማለት ነው" (አብዱ መሀይመን፣የካቲት፣ 2004፣44)፡፡[2]

## 3.2 የሐረሪ ማህበረሰብ ዳራዊ መግለጫ

የሀረሪዎች ጥንተ አመጣጥ "ኡልረኝ ብራው"ንን ጠቅሶ ሐረር ብሔራዊ ጉባኤ ያሳተመው "የሐረሪ አመጽ" የሚለው መጽሐፍ ላይ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡ "... የሐረር አምባ ነዋሪዎች እንደሚጠቀሙት የመጀመሪያዎቹ የሀረር አምባ ነዋሪዎች "ሐርላ" የሚባሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች በ14ኛውና 16ኛው ክፍለ ዘመን በጣም ያደገ የግድብ ስልጣኔና የድንጋይ ግንብ ስራ ችሎታ ነበራቸው፡፡... የዛሬዎቹ ሀረሪዎች ምናልባትም አብዛኛዎቹ በ16ኛው ክፍለ ዘመን በደረሰው ጦርነትና ረሃብ ወይም ከዚያ በኋላ በተከሰተው የኦሮሞ መስፋፋት ተደበላልቀዋል፡፡ እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ በምስራቁ የሶማሌ ክልል ሕዝብ የጠፋት የሐርላ ዝርያዎች ይሆናሉ የሚል ግምት አለ (ሐረር ብሔራዊ ጉባኤ፣ 1992፣12)፡፡

---

[2] አቶ አብዱ መሃይመን የተባሉት መረጃ አቀባይ የሀረሪ ማህበረሰብ የእድሜ ባለጸጋ አዛውንት ናቸው፡፡ ስለ አካባቢው፣ ስለ ማህበረሰቡ፣ ስለ ቁሳዊባህሎች፣ወዘተ.እውቀት አላቸው ብሎ ማህበረሰቡ ስለሚተማመንባቸው ከሃረሪ ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ፣ ከሀረሪማዘጋጃ ቤት እሳቸው ዘንድ ሄጄ መረጃ እንድወስድ በተጠቆምኩት መሰረት ብዙ ምረጃዎችን ከሳቸው አግኝቻለሁ፡፡ ይህም መረጃ ለጥናቱ የጀርባ አጥንት በመሆን ጠቅሞኛል፡፡

አብዱል ሼህ አህመድ በበኩላቸው ሀረርን ማን እንደመሠረታት ሲገልፁ፡፡"ሐረር በ9ኛው ክፍለ ዘመን ከአረብ ሀገር የመጡ ሐድረሚዎች ያቋቋሟት ከተማ መሆንዋ ይነገራል" (አብዱል ሼህ አህመድ፣ 1998፣1) ብለዋል፡፡

ሀረሪዎች የዘር ግንዳቸው ከአረብ እንደሆነ የሚነገሩ አፈታሪኮች አሉ። ይሄን ደግሞ የማህበረሰቡ አባላት የሆኑየድሜ ባለፀጋዎችና ምሁራን ምን እንደሚሉ እንደሚከተለውአረጋግጫለሁ አብዱመሀይመን የተባሉና የሰባ አመት አዛውንት የሆኑት ዋና መረጃ አቀባይ ያደረኳቸው ግለሰብ እንዲህ በማለት አመጣጣቸውን ገልፀዋል።"…ማህበራዊ እድገቱ ከደቡብ አረቢያን ሴሜቲኮች በ300 BC በመጡ ጊዜ አደሬዎች የከተማ ሰው ሆነው ነው የመጡት›› (አብዱ መሀይመን፣የካቲት፣2004፣45)። በመሆኑም የሀረሪዎች ጥንተ አመጣጥ ከደቡብ አረቢያ መሆኑን ይህ መረጃ በግልፅ የሚያስገነዝብ ነው።

በሀረሪዎች ቁሳዊባህል ላይ የሚገለጹትን ትምርቶች ስንመለከት ልዩ ጥበብ ያረፈባቸው ድንቅ ስራዎች ናቸው።እነዚህ ቁሶች ባለቤት ማህበረሰቡ ያዳበረው ከፍተኛ እውቀት እና ችሎታዎች መኖራቸውን ጠቋሚዎች ናቸው።እነዚህ እውቀቶች በብሄረሰቡ አጠቃላይ አኗኗር ላይ እጅጉን ተንጸባርቀው ይታያሉ።በመሆኑም በቀድሞ ጊዜ ሀረሪዎች በብዙዎች ዘንድ በምስራቅ አፍሪካ ስልጡን ህዝቦች ተደርገው ይቆጠሩ ነበር።

ሀረሪ ፈረንጆች ለብሔረሰቡና ለቋንቋው መጠሪያነት የሚጠቀሙበት ስያሜ ቢሆንም ባሁኑ ግዜ በመደበኛ ደረጃ ይሄው ስያሜ እያገለገለ ይገኛል፡፡ ህዝቡ እራሱን ጌይ ሰብ "የከተማ ሰው" ሲል ቋንቋውን ደግሞ ጌይ ሲናን "የከተማ ቋንቋ" ይለዋል፡፡ በአማርኛና ኦሮምኛ ተናጋሪው ዘንድ ብሔረሰቡ አደሬ ሲባል፤ ቋንቋው በኦሮምኛ ተናጋሪው አፋን አደሬ፣ በአማርኛ ተናጋሪው ደግሞ አደርኛ በመባል ይታወቃል፡፡ ሀረሪ.. የሴም ቋንቋ አካል ሲሆን የቅርብ ምደባውም ከነስልጤ፣ ወለኔና ዛይ ሆኖ ከአማርኛና አርጎብኛ ጋር በሁለተኛ እርከን ላይ ይገኛል (አህመድ ዘካሪያ፣ 1992፣ viii)፡፡

### 3.2.1 ማህበረ ባህላዊ ዳራ

በዚህ ክፍል የሐረሪ ብሄረሰብ ባህላዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ተዳሰዋል፡፡ እነዚህ የተቃኙ ቁም ነገሮች የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ ስለሆኑ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪው መንገድ ግንኙነት አላቸው ተብሎ አስቀድሞ የታሰቡ በመሆናቸው ነው፡፡ በምዕራፍ አምስት ለሚሰጠው ትንተና እንደ መንደርደሪያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡

#### 3.2.1.1 ጀጎል

የጀጎል ግንብ በዩኔስኮ በቅርስነት ከተመዘገቡት መሰህቦቻችን ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህ ግንብ መቼ ተሰራ? በነማን ተሰራ?በዩኔስኮ በቅርስነት ሊያስመዘግበው የቻለው ምንድነው? ወዘተ. የሚሉትን ጥያቄዎች ከተለያዩ መረጃዎች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የተለያዩ የታሪክ ፀሀፊዎች ስለነዚህ በሮች ስያሜና አገልግሎት የሚከተለውን ብለዋል፡፡ፀሀፊ ትእዛዝ ገ/ስላሴ የሐረርጌም ከተማ ከግራኝ አስቀድሞ የተሠራች ናት፡፡ የዕድሞውም በር ቁጥር 5 ነው፡፡ መጀመያው ታላቁ መግቢያ አስበዲን በር ይባላል፡፡ በዚህ ታላቅ መድፍ ተጠምዶበት ነበር፡፡ ይህ የጨርጨሮች መግቢያ ነው፡፡ 2ኛው ሱቅጣጥ በር ይባላል፤ ይህ ያሩሲዎች የጋራ ሙለታ መግቢያ ነው፡፡ 3ኛው አርጐባ በር ይባላል፡፡ ይህ የፈዲሶችና ያርጎቦች መግቢያ ነው፡፡ 4ኛውም አሱም በር ይባላል፡፡ ይህም የኢሶች መግቢያ ነው፡፡ በዚህ ታላቅ መድፍ ተጠምዶበታል፡፡ 5ኛው የሐረር በር ይባላል የየረሮች መግቢያ ነው (ፀሐፊ ትእዛዝ ገ/ስላሴ፣ 1959፣ 46)፡፡

አቶ አብዱላሂ ሼህ አህመድ በበኩላቸው ስለበሮቹ "እነዚህ አምስት የሀረር ከተማ በሮች መጠሪያ ስሞች የሚከተሉት ናቸው፡፡"

| በሐረሪ | በአማርኛ | በአረብኛ |
|---|---|---|
| 1. ሱቅጣጥ በሪ | ሠንጋበር | ባቡ አል ሰላም |
| 2. አስማዲን በሪ | ሸዋበር | ባቡ አልነስር |
| 3. አሱም በሪ | ፈላና በር | ባቡ አልፈትህ |
| 4. አርጎበሪ በሪ | ኤረር በር | ባቡ አልራህማ |
| 5. በድሮ በሪ | ቡዳ በር | ባቡ አልበድር |

ይባላሉ በማለት ገልፀዋል (አብዱላሂ ሼህ አህመድ፣ 1998፣1)፡፡

አቶ አብዱ መሀይመን የሀረሪዎች የድሜ ባለፀጋና ታሪክ አዋቂ የሆኑ ሰው ደግሞ ....

የጀጎል ግንብ ለምን እንደተገነባ? ስለ ስፋቱ፣ ስለ ርዝመቱ፣ ስለበሮቹ ቁጥር፣ አራተኛው ቅዱስ ከተማ ያሰኛት ምን እንደሆነ እና መቼ በዩኔስኮ እንደተመዘገበች ከዮኔስኮ ዌብሳይት የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ይገልፃል፡፡

> The wall was constructed to protect the city as its people from the possible attacks. It is 3-5 km long wall with a height of nearly 4 meters. It has five gates and the wall is still in fact and is a symbol of the town. The presence of 99 Mosques made Harar to be considered as the fourth holiest city in Islam next to Mecca, medina and Jerusalem. Harar is a symbol of tolerance and peaceful co-existence of peoples and religions.
>
> In recognition of its cultural heritage, the historic city of Harar (Jugol) was registered by UNESCO as world heritage site in 2006.[3]

አቶ አብዱ መሀይመን የተባሉ የእድሜ ባለፀጋ ስለ ጀጉል ግንብ አሰራር ስለበሮቹ አሰያየም እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

"የጀጎል ግንብ የተሠራው በአሚር ኑር ጊዜ ነው፡፡ ሁሉም የራስ የራሱን ሲያጥር ሂደት የፈጠረው ነው፡፡ በ15ኛው ክፍለ ዘመን ነው የተሰራው፡፡ አስራ ሁለት አመት ፈጅቷል ሁሉም በየአካባቢው (በየሰፈሩ) ያለውን አጥር ይጠብቃል፡፡... የጀጎል ግንብ የተሰራው አገሪቱን ከወራሪ ለመከላከል ነው፡፡... በኦሮሞ ማይግሬሽ ወቅት ሀረሪዎች ዘጠኝ ወር ከጀጎል ሳይወጡ ጦርነት ነበር፡፡ ያንን ወረራ ለመከላከል ነው ግንቡ የተሰራው (አብዱመሀይመን፣ 44-45)

በጀጎል ግንብ የታጠረችው ከተማ ሀረር ወደከተማይቱ የሚመጡና በከተማይቱ የሚኖሩ ሰዎችን የምታስገባበትና የምታስወጣበት አምስት በሮች አሏት፡፡እነሱም አስማአዲን በር (ሸዋበር)፣ አሱምበሪ (ፋላናበር)፣ አርጎበሪ (ኤረርበር)፣ በድሮበሪ (ቡዳበር)፣ ሱቅጣጥበሪ (ሰንጋበር) የሚል መጠሪያ አላቸው፡፡

[3] http//wrightspottour.com/UNESCO_Registered-sites.htm. Access date 07/06/2012.

እያንዳንዱ በር ለተሰየመለት ስም መነሻ የሚሆን ምክንያት አለው፡፡ ሸዋበር የክርስቲያን ሀይማኖት ወይም ክርስቲያኖች እና የሸዋ ሰዎች የገቡበት በር ስለሆነ ሰዎቹ የመጡበት አገር ለበሩ መጠሪያ ሆነ፣ ሰንጋ በር ለእርድ የሚውሉ የሀረር ሰንጋዎች የሚገቡበት በር ስለሆነ ሰንጋበር ተባለ፣ አሱሞበሪ (ፈለናበር) በአጠገቡ ያለው ወንዝ ቀይ ስለነበር አሱሚማለት በርበሬ ማለት ስለሆነ የወንዙን ቀለም ከበርበሬጋር በማመሳሰል አሱም በሪ አሉት፣ በድሮበሪ (ቡዳበር) በዚህ በር በኩል የብረታብረት ስራ ተግባር የሚያከናውኑ የእጅ ሙያተኞች የሚኖሩበትና ስራቸውንም የሚሰሩት እዚህ በር አካባቢ በመሆኑ ቡዳ በር ተባለ፡፡ አርጎበሪ የተባለው በር ደግሞ ከሀረሪ ብሔረሰቦች ጋር በመጋባት እና በተለያየ መልኩ ግንኙነት በመፍጠር ጀጎል ውስጥ የሚኖሩ አርጎባዎች አሉ፡፡ ይህበር በነሱ ስም የተሰየመው አርጎባዎች ወደ ጀጎል የገቡበት በዚህ በር ስለሆነ አርጎባ የገባበት በር ብለው ሰየሙት፡፡ እነዚህ በሮች በጥንት ዘመን ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰአት ላይ ተዘግተው ንጋት ላይ ይከፈቱ ነበር፡፡ በሮቹ የሚከፈቱትና የሚዘጉት በመድፍ ትእዛዝ ነው (የካቲት፣ 2004፣ አብዱ መሀይመን፣ 44-45)፡፡

# 4. የእደጥበብ ባለሙያዎች፣ ህይወት እና የሙያ ውጤቶች

ፈቃደ (1991፣15) እና Glassie (1999፣85) እንደገለፁት የቁሳዊ ባህል ጥናት ባለሙያውን ከዘነጋ ጎዶሎ ነው፡፡ በመሆኑም ቁሳዊ ባህልን በምናጠናበት ወቅት ቁሱንና ባለሙያውን ለያይቶ ማየት በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ቁሱ ህልውናውን ከባለሙያው ያገኘዋል፣ ባለሙያው የማህበረሰቡ አንድ አካል በመሆኑ እሱነቱን እና ማንነቱን ራሱ ህልው ያደረገው ቁስ ይገልፀዋል፡፡ ስለዚህ ስለ ቁሶቹ ትንተና ከመሰጠቱ በፊት በዚህ ክፍል ስለ ባለሙያዎቹ ሕይወት እና የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶቹን አሠራር የለመዱበት ሂደት ተዳሷል፡፡

## 4.1 የእደጥበብ ባለሙያዎች እና ሕይወታቸው

ዳሰሳ ካደረግኩባቸው የእደ ጥበብ ባለሙያዎች መካከል በተግባር ላይ ያሉት እና ያገኘኋቸው የሰፌድ ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎችን በመሆኑ የነሱን ሕይወት እንደሚከተለው ተመልክቼዋለሁ፡፡

የስፌድ ስራ ባሉሙያዎች በአብዛኛው የሚገኙት በጅጎል ውስጥ ባሉት ቀበሌዎች ነው፡፡ አብዛኞቹ ኑሮአቸው ደህና የሚባል ቢሆንም ከነሱ ደግሞ ሻል ያለ ሕይወት (ኑሮ) ያላቸውም አሉ፡፡ አብዛኞቹ ባለሙያዎች ኑሮአቸውን የሚደጉሙት በሚሰሩት የሰፌድ ስራ ሽያጭ ነው፡፡ በዚህ ሙያ ተሰማርተው የሚገኙትም ሙሉበሙሉ ሴቶች ናቸው፡፡

የሰፌድ ስራው በሀረሪዎች፣ በተለያዩ ማህበረሰቦች እና ከውጭ ሀገር በሚመጡ ጎብኚዎች በጣም ተፈላጊ ስለሆነ እና ዋጋውም ውድ በመሆኑ ባለሙያዎች በቂ ነው የሚባል ባይሆንም ጥሩ የሆነ ገቢ እንደሚያገኙ በመስክ ቆይታዬ አረጋግጫለሁ፡፡

የአለላሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያጠፉት ሰፌትበመስፋት ሥራ ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም የሰፌት ስራ ረጅም የሚባል ጊዜ የሚወስድና በጥንቃቄ የሚሰራ በመሆኑ ነው፡፡ባለሙያዎች ሙያቸውን የሚያከናውኑት በሁለት መልክ ነው፡፡ አንደኛው በግል እቤታቸው ውስጥ በመስፋትና በመሸጥ ሲሆን ሁለተኛው በማህበር በመደራጀት ከሌሎች የሞያ አጋሮቻቸው ጋር በመጣመር ነው፡፡

ከኢህአዴግ የስልጣን ዘመን እኩሌታ በኋላ እነዚህ ባለሙያዎች በማህበር የሚደራጁበት ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል፡፡ በዚህም አጋጣሚ አብዛኞቹ ባለሙያዎች በማህበር ተደራጅተው መስፋት ሲጀምሩ የተወሰኑት በእድሜ መግፋት እና በተለያየ የግል ሰበብ ሳይደራጁ ቀርተዋል፡፡ ወ/ሮ ዘቢዳ የተባሉ በግል የሚሰፉ መረጃ አቀባይ በማህበር ያልተደራጁበትን ሰበብ እንዲህ በማለት ይገልፃሉ፡፡"በማህበር ያልተደራጀሁት እነሱ ልጆች ናቸው እኔ አልችልም ብዬ ነው፡፡ ለብቻዬ እሰራ ነበር፡፡ አሁን አረጀሁ ደከመኝ (ዘቢዳ፣ጥር፣ 2004፣ 25)፡፡"

በማህበር ተደራጅተው ያሉት የስፌት ባለሙያዎች መደራጀታቸው ምን ፋይዳ እንዳስገኘላቸው እና በማህበር ከመደራጀት እና በግል ከመስፋት የቱ እንደሚሻል ለቀረበላቸው ጥያቄ ቀጣዩን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ "በማህበር ተደራጅቶ መስራት ይሻላል፡፡ ሰፍተን አዙረን አንሸጥም፡፡ ማህበሩ ሸጦ ገንዘብ ይሰጠናል፡፡ መተዳደሪያዬም ይሄ ነው፡፡ እኛ አላህ በሰጠን ነው የምንተዳደረው፡፡ እዚህ ማህበር ውስጥ ያለነው የተለያየ የኑሮ ደረጃ ነው ያለን፡፡ ፓስተና ሩዝ በልቶ የሚያድር አለ፡፡ ደረቅ እንጀራም በልቶ የሚያድር አለ፡፡ አሁን ግን ጥሩ ነው በማህበር መሆናችን (ከዲጃ፣ጥር፣ 2004፣ 35)፡፡

ወ/ሮ ከዲጃ እንዳሉት ሰፍተው የሚገዛቸው ፍለጋ አይዞሩም፡፡ ማህበሩ ራሱ ሸጦ ገንዘብ ይሰጣቸዋል፡፡ ይሄ ደግሞ ያመረቱትን ምርት ለመሸጥ ገበያ በማፈላለግ ጊዜያቸውን ስለማያጠፉ ያላቸውን ሰአት በሰፌት ስራው ላይ እንዲያሳልፉ ያደርጋቸዋል፡፡

ወ/ሮ ሰፊያ የተባሉት መረጃ አቀባይ በማህበር መደራጀት ስለ ሰጣቸው ጠቀሜታ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

> *... ጥቅምስ አለው፡፡ አሁን በደንብ ነው የምንሰራው፡፡ በፊት ስንፈልግ እንሰራለን ሳንፈልግ እንተወዋለን፡፡ ይሄ እንደ መንግስት ሰራ ሦስት ሰአት እንገባለን ስድስት ሰአት እንወጣለን፡፡ ስምንት እንገባለን አስራ አንድ እንወጣለን ጊዜው ይሄድልናል፡፡.... ማህበሩ ብዙ ጊዜ ተሸልሟል፡፡ ሁል ጊዜም ሁሉ ቦታ የሄድንበት አለ፡፡ ባህር ዳር፣ ሀዋሳ ሄደናል፡፡ ከነእቃችን ሽለማትም ተሰጥቶናል፡፡ ቴሌቭዥኑ ሽልማት*

*ነው በማለት ጊዜን በአግባቡ ስራ ላይ ለማዋል ማህበሩ እንደረዳቸው፣ የማህበሩ መሸለምም ለበለጠ ተግባር እንዲነሳሱ እንዳደረጋቸው ገልፀውልኛል (ሰፊያ፣ጥር፣ 2004፣ 3)፡፡*

## 4.2 የእጅ ባለሙያዎች ሙያውን የለመዱበት መንገድ

በዚህ ክፍል የእደጥበብ ባለሙያዎቹ ሙያውን እንዴት እንደለመዱት የሚያሳይ ፅሁፍ ቀርቧል፡፡ ትኩረት የሚያደርገው የስፌት ስራ ለመዳ ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም አሁን ድረስ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ዘርፍ በመሆኑ ነው፡፡

ሀረሪዎች የስፌትን ሞያ ወላጆቻቸው በህይወት ካሉ ከእነሱ ይማራሉ፡፡ ወላጆቻቸው በህይወት ከሌሉ በሙያው የተካኑ ጎረቤቶቻቸው ስር ቁጭ በማለት ሙያውን ይለምዳሉ፡፡ የስፌት ስራ ሞያ ለመዳ በጣም አድካሚና እልህ አስጨራሽ ስራ ነው፡፡ በተለይም ዲዛይን አገባብ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄና ብልህነትን የሚጠይቅ ተግባር በመሆኑ እያንዳንዷ ለማጅ አስለማጇን በጥሞና ማዳመጥ እና እነሱ ተግብሪ የሚሏትን ተግባራት ተጠንቅቃ ማከናወን ይጠበቅባታል፡፡ ስለ ስፌት ስራው የለመዳ ሂደት ወ/ሮ ከዲጃ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

> "በሰፈር ከኛ ትላልቅ ሰዎች ያስተምሩናል፡፡ ትንንሽ ሆነን ከጎረቤቶቻችን ነው የወረስኩት፡፡ እናቴ ትንሽ እያለሁ ስለሞተች ከጎረቤት ነው የወረስኩት፡፡… ሴት ልጅ ስፌት ለመስፋት ጓደኞቿ ጋ ስትሔድ ስፌት ሲያለማምዷት አንዱን ቤት ብቻ ነው እንድትሰፋ የሚያደርጉት፡፡ ወይ ገብረ መርፌ ይሁን መቅናቱን አንዱን ቤት ብቻ ነው የምትሰፋው፡፡ እሱን ከሰፋችና ችሎታው ካላት ወደ ሌላ ቤት ትሻገራለች፡፡ እሱንም ስትጨርስ ወደ ሌላ ሁሉንም ስትጨርስ ችሎታዋ ሲታይ ይህኛው ሀማትሞት ከአስር ስጋጃ በላይ የያዘ ነው፡፡ ይህን ስትጀምር በስፌት ስራ ከፍተኛውን እውቀት ወይም ክህሎት ጨብጣለች ማለት ነው፡፡ ይሄ የመጨረሻው ስፌት ነው ሀማትሞት በማለት የስፌት ስራ ከማን እንደለመዱ እና የለመዳው ሂደት ምን መልክ እንዳለው ገልፀዋል(ከዲጃ፣ጥር፣ 2004፣ 39)፡፡

ከወ/ሮ ከዲጃ ገለፃ እንደምንረዳው በማህበረሰቡ ሁሉም ባለሞያአከሊት ከእከሊት ብሎ ሳይለይ የሙያው ሽግግር ቀጣይነት እንዲኖረው ለተተኪ ትውልድ የማስለመድ ሀላፊነት እንዳለበት በመገንዘብ ለጎረቤት ልጆች የእደ ጥበብ ሙያውን እንዲለምዱ ያደርጋሉ፡፡በመሆኑም ቤተሰብ የሌላቸው ልጆች ጭምር ሙያውን የመልመድ ችግር አያጋጥማቸውም፡፡

ከወ/ሮ ከዲጃ ገለፃ እንደተገነዘብነው Silverman የእጅ ሙያ መማሪያው መንገዶች ካላቸው ከመደበኛ ስልጠና፣ ከምልከታ እና ከተደጋጋሚ ሙከራዎች ውስጥ ወ/ሮ ከዲጃና ሌሎች መረጃ አቀባዮች ሙያውን የለመዱት በተደጋጋሚ ሙከራ ነው፡፡ ተደጋጋሚ ሙከራ ስህተትን ወዲያው ወዲያው ለማረም ስለሚያግዝ የሙያውን ክህሎት በተሻለ ፍጥነት ለመጨበጥ ይረዳል፡፡

አቶ አህምድ ዘከሪያ ስለ አለላ ስራ ለመዳ(Harari Basketry through the Eyes of Amina Ismael sherif)በሚለው አርትክላቸው ውስጥ ልጃገረዶች በልጅነታቸው በእናቶቻቸውአስለማጅነት ስፌት እንዴት እንደሚሰፋና እጃቸውን አንደሚያስለምዱ፣የአለላ ስራ ሀብታም እና ደሀ ሳይለይ ሁሉም የማህበረሰቡ አባል የሚለምዱት ሙያ መሆኑን....የጌይላች አባላት የመጀመሪያውን የልጅነት አመታት የሚያሳልፉት በሞይ ጋር መሆኑን ፣በሞይጋር(ሞያ መልመጃ ቤት) ቆይታቸው የሚማሩት የአለላ ስራ ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ ስነምግባሮችንም እንደሚቀስሙ ገልጸዋል(አህመድ ውስተ silverma,1999,53-54)::

## 4.3 በእደ ጥበብ ሥራ ላይ ያለ ማህበራዊ አመለካከት

በዚህ ክፍል አጠቃላይ በእደ ጥበብ ስራ ላይ ያለውን አመለካከት እና በተናጠል በስፌት ስራ ላይ ያለውን ማህበራዊ አመለካከት አቅርቤያለሁ፡፡

በሀረሪ ማህበረሰብ ከአሚሮች ጊዜ ጀምሮ የነበረ የእደ ጥበብ ተግባር አለ፡፡ አሚር አብዱላሂ በሚኒሊክ ጦር ተሸንፈው ከሀገር ከወጡ እና ሀረር በሚኒሊክ አስተዳደር ስር ከገባች በኋላ በእደጥበብ ሙያ ላይ የሚሰጠው አመለካከት አዎንታዊ መሆኑ ቀርቶ አሉታዊ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይህንን ጉዳይ እንድሪስ የተባሉ መረጃ አቀባይ እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡ “ቆዳ ፋቂዎች፣ ሸማኔዎች፣ ቀጥቃጮች፣ እነኚህ ሁሉ የእጅ ባለሙያዎች ናቸው፡፡ በፊውዳሉ ዘመን ምን ይባላሉ ቡዳዎች ይባላሉ፡፡

እቃውን እየፈለጉ ሰዎቹን ያጥላላሉ፡፡ በስልጣን ላይ የነበሩ ሀረሪዎች ነበሩ እነሱም አመለካከታቸው ያው ነበር፡፡ ከቀጥቃጮች ጋር አይጋቡም ነበር" (ኢ.ድሪስ፣የካቲት፣ 2004፣ 48)፡፡

ከጀጎል ግንብ አምስቱ በሮች መካከል አንደኛው በር ቡዳ በር ይባላል፡፡ በመስክ ቆይታዬና ከዚያም በፊት እንዳረጋገጥኩት በዚህ ቡዳ ተብሎ በተሰየመው በር መውጫ አካባቢ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ስለሚገኙ ማህበረሰቡ እነሱን ቡዳ ናቸው ብሎ ስለሚላቸው የሙያተኞቹ ስም ለበሩም ተርፏል፡፡ይሄ አመለካከት ከምኒሊክ ወረራ በፊት በሀረሪዎች ዘንድ ያልተለመደ ነበር፡፡

ሀረሪዎች ዛሬ የሚኮሩበት የቱሪስት መስህብ የሆነው ሀገረሰባዊ የእለላ ስራ የትኛውም የሀረሪ ተወላጅ የሚኮራበት እንጂ የሚያፍርበት ተግባር አይደለም፡፡ ሀረሪዎች ይህንን የስፌት ስራ ከእለት ወደ እለት እያሻሻሉት የራሳቸው መገለጫ በማድረግ ማንነታቸውን፣ ፍላጎትና ውስጣዊ ስሜታቸውን እያሸከሙት ዛሬ የደረሰበት ደረጃ አድርሰውታል፡፡

የሀረሪ ማህበረሰብ ስፌት ለሚሰፉ ሰዎች ያለው አመለካከት እንዴት ነው በማለት ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ወ/ሮ ዘቢዳ እንደሚከተለው አብራርተውልኛል፡፡ "ስራ አይደለም በህበረተሰቡ የሚሰፋ ሰው ከበሬታ አለው፡፡ ይሄን የምትሰፋ ሴት በማህበረሰቡ ባለሙያው ትባላለች፡፡ እርስ በእርስም በሞያ አንዱ ከአንዱ ይለያያል፡፡ አንዱ ከእኔ በላይ ያለም ይኖራል፡፡ ከእኔ በታችም ያለም ይኖራል፡፡ ሁሉም በየእውቀቱ ይሰራል (ዘቢዳ፣ጥር፣ 2004፣ 25) በማለት ማህበረሰቡ ስፌት ለሚሰፉ ሴቶች ያለውን አክብሮት አስረድተውኛል፡፡

ወ/ሮ ቢፍቱ የተባሉ መረጃ አቀባይ ስለ ስፌት ሞያ በማህበረሰቡ ለሰፊዎች ያለውን ምላሽ እንዲህ ይገልፁታል፡፡ "በኛ ባህል ስፌት የሚሰፋማ በጣም ይከበራል፡፡ ጥሩ አመለካከት አላቸው፡፡ ድጋፍ ሁሉ አለው፡፡ የሀረሪ ሴቶች ብዙዎቹ ይችላሉ፡፡ ይህንን ስፌት የማይችል የለም እና አልቀረም አሁንም ይገለገሉበታል በማለት ባህሉ ለስፌት እና በሀረገሰባዊ የስፌት ስራ ለተሰማሩ ሴቶች እየሰጠ ያለውን ከበሬታ በአፅንኦት ገልፀውልኛል፡፡

መረጃ አቀባዮቹ እንዳረጋገጡልኝ እና በመስክ ቆይታዬ እንደተረዳሁት የሀረሪ ማህበረሰብ ዘንድ ስፌት ከፍተኛ ፍቅርና ከበሬታ የሚሰጠው የቁስ አይነት ነው፡፡ በመሆኑም በጣም ውድ የሆኑትን እነኚህን ቁሶች በመግዛት እያንዳንዱ ጎጆ የወጣ ሀረሪ ቤቱን የማሳመር ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ምክንያቱም ማህብረሰቡ ወዶና ፈቅዶ የተቀበለው ባህል በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቁሶቹን ወዶ ባለሙያዎቹን የሚያገል አመለካከትም ፈፅሞ የለም፡፡ በስፌት ሞያ ላይ የተሰማሩ ሴቶች አንቱ ተብለውና ተከብረው እንደሚኖሩ አረጋግጫለሁ፡፡

## 5. የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ትንተና

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ጉዳይ የሆኑት የሀረሪ ብሔረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች በምዕራፍ ሁለት በቀረቡት ንድፈ ሃሳቦች ተቀንብበው ትንተናና ትርጓሜ ተሰጥቶባቸዋል፡፡


### 5.1 የአለላ ቁሶች

በዚህ ክፍል ስለ ሀረሪዎች ሀገረሰባዊ የአለላ ስራ ውጤቶች አይነት፣ ጠቀሜታ፣ የአሰራር ሂደት፣ ስለሚያስተላልፉት መልዕክትና ማህበረሰቡ ራሱን በቁሶቹ እንዴት እንደገለፀ ትንተና ተሰጥቶባቸዋል፡፡ የሚተነተኑትም ቁሶች ሐማትሞት፣ ጉፍተሙዳይ፣ ሌማትሞት፣ ሰጋሪወስክምባይ፣ ሳንቡሳ እና ሚህካክናወስክምባይ ናቸው፡፡

**የአለላ አቀላለም፡-**ለሁሉም ሰፌቶች አንድ አይነት ስለሆነ አቀላለሙን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡በመስክ ቆይታዬ እንዳረጋገጥኩት የሚያቀልሙበት የራሳቸው ወይም ባህላዊቀለም የላቸውም፡፡ ከገበያ ላይ ገዝተው እንደሚያቀልሙ ተረድቻለሁ፡፡ በመሆኑም ለማቅለሚያ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ከገበያ ተገዝተው ወደ ቤት እንዲመጡ ይደረጋል፡፡ በዱቄት መልክ የተዘጋጁ ቀለማት ለምሳሌ ቀይ፣ ቢጫ፣ አረንጓዴ፣ ሰማያዊ ወዘተ. ዝግጁ ይሆናሉ፡፡ የሳር ዝርያዎቹ አክርማ፣ ስንደዶ እና የገበስ ቀርማ(ብር) ከገበያ ላይ ተገዝተው ይመጣሉ፡፡እነዚህን የሳር ዝርያዎች ነጋዴዎች ከጂጂጋ እና ከአዲስ አበባገዝተው ያመጣሉ፡፡ የሚቀልሙት ሳሮች እና አቅላሚ ቀለማቱ ከተዘጋጁ በኋላ ቀለም ለማቅለሚያነት የተለየ ብረት ድስት ይዘጋጃል፡፡ በብረት ድስቱ ውሃ በግምት ተለክቶ ይጣዳል፡፡ ውሃው መፍላት ሲጀምር የሚፈለገው ቀለም ቀይ ከሆነ ቀይ ፣ ቢጫ ከሆነ ቢጫ ቀለም መፍላት በያዘው ውሃ ውስጥ ይጨመራል፡፡ ቀለሙና ውሃው ተዋህደው ሲፍለቀለቁ ሳሮቹ ይከተታሉ፡፡ በደንብ ትክትክ እንዲሉም ይደረጋል፡፡ ምክንያቱም በደንብ ካልተንተከተከ ስለማይቀልም በሚል ነው፡፡ መቅለማቸው ሲረጋገጥ ሳሮቹ ከድስቱ ውስጥ እየወጡ ፀሀይ ላይ ይሰጣሉ፡፡ ከደረቁ በኋላም በየ ዝርያቸው ቀርማውም፣ አክርማውም በየወገኑ ተደርጎ በሳር አሰር፣ አሰር እየተደረገ ለአገልግሎት ተዘጋጅቶ ይቀመጣል፡፡

ወ/ሮ ቢፍቱ እና ወ/ሮ ዘቢዳ ስለ አለላዎች አቀላለም አጠር በማድረግ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡"በድስት ቀለሙን ጨምረሽ ይጣዳል፡፡ ቀይ ከፈለግሽ ቀይ፣ ቢጫ ከፈለግሽ ቢጫ፣ አረንጓዴ ከፈለግሽ አረንጓዴ አድርገሽ ይተከተካል፡፡ ከዚያም አገራው ይደርቃል"(ቢፍቱ፣ጥር፣ 2004፣ 29)፡፡

"... መጀመሪያ አክርማው ይገዛል፤ ይሰነጠቃል፣ ከዚያም ቀለም እንገዛና ውሃ ውስጥ ቀለሙን ከተን በድስት እናንድቢታለን፡፡ ስንደዶውን ጨምረን ቀይም ቀይ ይሆናል፣አረንጓዴውም አረንጓዴ ይሆናል፣ ቢጫውም ቢጫ ይሆናል (ዘቢዳ፣ጥር፣ 2004፣ ፣27)፡፡



የተቀለሙ አክርማዎችና የገብስ ቀርማዎች(ብር)

ለመውጊያ የሚያገለግል ወስፌ፣ ለመቁረጫ የሚያገለግል መቀስ እና ቀርማውና አለላው እንደተፈለገው ሳይሰባበሩ መተጣጠፍ እንዲችሉ በውሃ ውስጥ ስለሚዘፈዘፉ ለመዘፍዘፊያ ወይም መንከሪያነት የሚያገለግል ውሀ መያዣ ሰፋ ያለ ሳህን ያስፈልጋል፡፡

ለስፌት መስፊያነት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ዝርዝር እና ስለ አለላ ቀለም አዘገጃጀት ሂደት ወ/ሮ ቢፍቱ ኡመር የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> በድስት ቀለሙን ጨምረሽ እሳት ላይ ይጣዳል፡፡ ቀይ ከፈለግሽ ቀይ፣ ቢጫ ከፈለግሽ ቢጫ፣ አረንጓዴ ከፈለግሽ አረንጓዴ አድርገሽ

ይተከተካል ከዚያም አገገራው ይደርቃል፡፡ ከዚያ ይገዛል እያዘጋጁ የሚሸጡ ሰዎች አሉ ይቺን በአምስት ብር እንገዛለን፡፡... አሁን አገገራው ውሃ ውስጥ ተዘፍዝፎ ነው ያለው እንደምታይው ቀለሙ አይለቅም፡፡... ለስፌት መስሪያ የምገለገለው መቀስ፣ መውጊያ ወስፌ፣ መቀሱ ቀርማውን ባጫጭር ለመቁረጥ ነው" (ቢፈቱ፣ጥር፣ 2004፣ 29)፡፡

## የአለላስራ ዲዛይኖች

የሀረሪዎች የአለላ ስራ የተለያዩ ዲዛይኖች የሚታይበት ነው፡፡እያንዳዱ ዲዛይንም የራሱ ስምአለው፡፡ለምሳሌ፤ገብረመርፌ፣ቀዲም፣ቢሳጥ፣ሰሌንጋር፣ኡፋርዳ፣መቅናቲን፣ፈረሽመሀለቅ፣ከዲጃብሩቅ፣አዱረኢን፣መሀመድአሊጋር፣ወዘተ.በመባል ይታወቃሉ፡፡

ስለዲዛይኖቹ ትርጉም እና አገልግሎት ለመረጃ አቀባዮቹ ጥያቄ በማቅረብ መረጃ ለማግኘት ሞክሬያለሁ፡፡አቶ አብዱ መሀይመን ስለ ዲዛይኖቹ የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

> *አሁን መሀመድ አሊ ቤት የሚባል ስጋጃ አለ፡፡ መሀመድ መጣ ቤቱን አሳየት ያንን የመሀመድ አሊን ቤት መስኮት ላይ ያየችውን አንዱን ክፍል አነሳቻት፡፡ ያስጋጃ መሀመድ አሊ ቤት ተባለ፡፡ ሰሌን ብሩቅ የሰሌን ማጌጫ ማለት ነው፡፡ አዱረኢን የድመት አይን ማለትነው፡፡ መቅናቱን ማጣመሪያ ማለት ሲሆን ቀዲም ጋር የመጀመሪያ (አዲስ ጀማሪ የሚለማመድበት) ማለት ነው፡፡ ገብረመርፌ መርፌው ሰለጠነ በስራው በስፌቱ የተካነ (ማስተር) ያደረገ ሰው የሚሰራው ማለት ነው፡፡መርፌው የማይሰፋው የለም ማለት ነው፡፡ ሰጋሪ ብሩቅ ጥንቸል ማለት ነው፡፡... መለያ ካንዱ ቅርፅ (ዲዛይን) ሌላውን መለያያ (boundary) ነው፡፡ ሐናጭሀበ ቀስት ማለት ነው፡፡ ዘቢዳ ብሩቅ የዘቢዳ ስጋጃ፣ የዘቢዳ ማጌጫ ማለት ነው (አብዱ መሀይመን፣የካቲት፣ 2004፣ 46)፡፡*

የተገለፁት የዲዛይን አይነቶች አንዲት ስፌት መስፋት መለማመድ የምትፈልግ ልጃገረድ እንደየቅለታቸው ቅደም ተከተል የምትለማመዳቸው የዲዛይን አይነቶች


ናቸው፡፡ ቀዲምጋር አዲስ እና ገና ሰፍተው የማያውቁ ልጃገረዶች እንዲሰፉት የሚደረግ የእጅ ማለማመጃ ዲዛይን ነው፡፡ለማጅቹ እጃቸውን ቶሀቶሀ (ረጋሰራሽ) በሆነው በቀዲም ብዙም ሳይጠቀጥቁት አለፍ አለፍ እያሉ በመውጋት የሚሰፉት የስፌት አይነት ነው፡፡ በቀዲም የተጀመረው የዲዛይን ስራ እያደር እየተሻሻለ ከቀን ወደ ቀን ረቀቅ ወዳለ ጥበብ እያደገ ይሄዳል፡፡

የዲዛይን አይነቶቹ በለመዳ ሂደት ውስጥ ያሉ የዲዛይን (ጥበባት) ስያሜ እንጂ እያንዳንዳቸው ትእምርት የላቸውም፡፡ ለምሳለ በመቅናቲን ወይም በአዱረኢን ዲዛይን የሚሰፋው የመለማመጃ ስፌት ቅርፁ ከሀማትሞት ጋር አንድ አይነት ነው፡፡ ነገር ግን ሀማትሞት ተብሎ አይጠራም፡፡ መቅናቲን ወይም አድረኢንም አይባልም፡፡ ሀማትሞትን እና ሌሎቹን የተተነተኑትን ስፌቶች ለየት ያደረጋቸው የተናጥል ዲዛይን ሳይሆን የዲዛይኖች ህብር ነው፡፡ ትርጉምም ያለው ይህ ህብረ ዲዛይን ነው፡፡ከላይ እንደጠቀምኩት ሀማትሞት በቅርፁ ከመለማመጃ ስፌቶቹ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ነገር ግን ሀማትሞት አሰኝቶ ማህበራዊ ፋይዳ እንዲሸከም ያደረገው የዲዛይኖች ህብር የአለላስራው ላይ በመዋሉ እንጂ በቅርፁ አይደለም፡፡

በመሆኑም በሀረሪ ማህበረሰብ ተምሳሌቶችን የተሸከሙ ቁሶችን መስፋት የሚቻለሙ ለየብቻ የተዘጋጁትን የዲዛይን አይነቶች ጠንቅቆ በማወቅና ክህሎትን በማዳበር ነው፡፡ የእነዚህን ዲዛይንኖች ክህሎት አለመካን አንዲት ልጃገረድን ትዳር ሊያሳጣት ይችላል፡፡ ምናልባት ሞያ እንደሌላት ሳይታወቅ ብታገባ እንኳ ባህሉ እንድትሰፋ የሚያስገድዳትን ሐማትሞትን ሰፍታ ለማቷ ካልሰጠች በባሏ፣ በባሏ ቤተሰቦች፣ በጓደኞቿ እና በአጠቃላይ በማህበረሰቡ የተናቀች እና ከበሬታ የሌላት ትሆናለች፡፡ይህጉዳይ ቀደም ባሉት ጊዜያት በማህበረሰቡ አባላት ዘንድ በተግባር ይውል ነበር፡፡ባሁኑ ጊዜ አብዛኛው የማህበሩ አባል በመግዛት ለሚፈልገው ማህበራዊ ፋይዳ ይገለገልባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ልጅቷን ባለሙያ የሚያሰኛት የምትሰፋው ቁስ ቅርፅ ብቻ ሳይሆን በቁሱ ላይ የሚያርፉት ህብረ ዲዛይኖች ናቸው፡፡ በመሆኑም ያለ ዲዛይን ችሎታ ቁሶቹ አይሰሩም፡፡ ለቁሶቹ ህልው መሆን ዲዛይኖቹ ወሳኝ ነገሮች በመሆናቸው በማህበረሰቡ የተለያዩ ተምሳሌቶችን የያዙ የስፌት ቁሶችን ለማግኘት በዲዛይን ሞያ መካን የግድ ነው፡፡

ይህጉዳይ ቀደም ባሉት ጊዜያት በማህበረሰቡ አባላት ዘንድ በተግባር ይውል ነበር፡፡ባሁኑ ጊዜ አብዛኛው የማህበሩ አባል የአለላ ስራዎቹን በመግዛት ለሚፈልገው ማህበራዊ ፋይዳ ይገለገልባቸዋል፡፡



ዲዛይናቹን መለማመጃ ሰፌቶች

የስፌት ቁሶች በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ የተለመዱ እና ጥንታዊ ቁሶች ናቸው፡፡ ሀረሪዎችም እነዚህን ቁሶች በተለያየ ቅርፅ በመስፋት ለዘመናት በቤት ውስጥ ሲገለገሉባቸው ቆይተዋል፡፡ በችግርም ጊዜ እነዚህ ቁሶች ለችግራቸው መውጫ ውለታ ውለውላቸዋል፡፡ አቶ አብዱ መሀይመን የስፌት ቁሶች ለሀረሪዎች የዋሉትን ውለታና ማህበረሰቡም ለተዋለለት ውለታ የሰጠውን ምላሽ እንዲህ በማለት ይገልፃሉ፡፡

> *"በኦሮሞ ማይገሬሽን ጊዜ ሀረሪዎች ዘጠኝ ወር ከጀጎል ሳይወጡ ጦርነት ነበር፡፡ አልተራቡም፣ አልተጠሙም፡፡ እንጨት ሲጠፋ ሰፌቱን እያቃጠሉ (እያነደዱ) እያበሰሉ ይበሉ ነበር፡፡ ጦርነቱ ሲያልቅ ሲረጋጉ ንጉሱ በሉ ለችግር ጊዜም ይሆነናል ሀረሪ ቤት በመሉ ይሰቀል! በማለት ትእዛዝ ሠጡ፡፡ አሁን እያደገ እያደገ ያችግር ስላልፈተጠረ ቤታቸውን አደረጁበት፡፡ ከተሜነት ነገር እየታየበት ቀስበቀስ እንደ ባህል አደረጉት" (የካቲት፣ 2004፣ አብዱ መሀይመን፣ 43)፡፡*

ቁሳዊ ባህሎቹ ለሀረሪዎች ከቤት ውስጥ መገልገያነት ባለፈ የማህበረሰቡን ህይወት እስከመታደግ ድረስ የዘለቀ ሚና ተጫውተዋል፡፡ በዚህም በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ

ግምት በማግኘት በያንዳንዱ ሀረሪ ቤት ተሰፍተው እንዲሰቀሉ በሀረሪዎች አሚር[4] አዋጅተጠናክሮ ዛሬ ላለው ደረጃ በቅቷል፡፡ በመሆኑም ሀረሪዎች በነዚህ ስፌቶች ቤታቸውን በሚከተለው ፎቶ ላይ በምናየው መልኩ ያስጌጣሉ፡፡



(የሀረሪን መደብ ቤት የሚያሣይ ፎቶ)

በፎቶ ግራፉ ላይ እንደሚታየው የቁሶቹ አሰቃቀል በረድፍ በረድፍ ሲሆን እያንዳንዱ ቁስ በተፈቀደለት ቦታ የአሰቃቀል ባህሉን በሚያውቁ ሰዎች እንዲሰቀል ይደረጋል፡፡ እነዚህ ቁሶች በቤት ውስጥ ከተነጠፈው ስጋጃ ምንጣፍና ተመሳሳይ ትራስ ጨርቅ ለብሰው ከተደረደሩት ትራሶች ጋር በመሆን ለቤቱ ልዩ ድምቀትና ውበት ይሰጡታል፡፡ አቶ አብዱ መሀይመን ስለቁሶቹ የአሰቃቀል ቅደም ተከተል እንዲህ ይገልፃሉ፡፡ "ሀቻላ፣ ኩቻላ፣ ሾሽቲቻላ ምን ማለት ነው ይሄ አንደኛ ረድፍ፣ ሁለተኛ ረድፍ፣ ሶስተኛ ረድፍ ይባላል፡፡ መጀመሪያ ከእንጨት የተሰሩት ይደረጋሉ፤ ከዛ በኋላ የሣር ሥራዎች እያሉ ይደረደራሉ" (አብዱመሀይመን፣የካቲት፣ 2004፣ 39)፡፡

---

[4]በሀረሪዎች 72 አሚሮች ነግሰዋል የመጨረሻው አሚር አብዱላሂ ሲባሉ ከሚኒሊክ ጋር በተደረገው ጦርነት በ1887 ነው ከስልጣን የወረዱት፡፡ አሚር ማለት ንጉስ ማለት ነው፡፡

[3]አዋጅ በዘመኑ በቃል ስለሚነገር የተጻፈ መረጃ አላገኘሁም ፡፡አሚሮቹ ህግ እና ደንቦችን ጥምር ያስተላልፉ የነበረው በቃል እንደነበር አረጋግጫለሁ፡፡

ቁሳዊ ባህሎች በየረድፋቸው ሲሰቀሉ የአሰቃቀል ስርአት አላቸው፡፡ የስፌት ተርታ ነው ተብሎ በዘፈቀደ እያመሳቀሉ መስቀል አይቻልም፡፡ ስለዚህ ጉዳይ አቶ አብዱ መሀይመን እንዲህ ይላሉ "ደግሞ እይ እያንዳንዷ ስፌት ቦታ ቦታ አላት ወንዶች እንኳን ማነው እዚ ይሄን የሰቀለው? ይህ ቦታው እዚህ ነው ይላሉ፡፡ አንድ ስፌት አንድ ቦታ ነው ሁል ጊዜ የሚሰቀለው..." (አብዱመሀይመን፣የካቲት፣ 2004፣ 40)፡፡

ስለ ሀረሪዎች ቤትና የተለያዩ ስፌቶቻቸው (Ahmed Zekaria,1999,8) ከላይ ከቀረቡት ምዕራፎች ጋር በሚስማማ አገላለፅ እንዲህ ብለዋል፡፡ concerning the beauty of interior walls of a living room. We see baskets with different pattens and shapes hanged on the walls. Baskets are essentially pieces of art for Harari".

በሀረሪዎች የሚሰሩት የአለላ ስራዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ለቱሪስት፣ ለሀረሪዎች፣ ለሰርግ ወዘተ. ናቸው፡፡ ለሰርግ ወይም የስጦታ የአለላ ስራዎች መካከል ሳህናሰጋሪ፣ ሻልደጋር፣ ፊጃንጋር፣ ቢሸሙዳይ፣ ራዝሙዳይ፣ ሚሀክናወስክምባይ ወዘተ. ተጠቃሾች ናቸው፡፡

### 5.1.1 ሐማትሞት



ሐማትሞትምራት ሰፋታ ለአማቷ የምትሰጠው የስፌት አይነት በመሆኑ(የአማትስፌት) ተባለ፡፡ዝርግና ክብ ሆኖ በመጠኑ ጎርጎድ ያለ የስፌት ቁስ ሲሆን ከስር በኩል ትንሽ መቀመጫ የሚሆን እግር አለው፡፡ ሁለት ሐማትሞት በማካደን በበሩ ፊትለፊት ባለው ግድግዳ መሐል ላይ ፊት ለፊት ይሰቀላሉ፡፡

አሰራር ፤- የሐማትሞት አሰራር ከተለያዩ የሳር ዘሮች እና ከገብስ ቀርማ(ብር) ነው፡፡ እነዚህ ቁሱን መስሪያ የሆኑ ቁሳቁሶች ከተሟሉ በኋላ ሀማትሞትን የምትሰፋዋ ሴት ቀለም የሌለውን ነጭ አክርማ ውሃ ውስጥ ትነክራለች፡፡ መራሱን ስታረጋግጥ አንድ በአንድ እያነሳች ትሰነጥቃለች፡፡ በምትሰነጥቅበት ጊዜ ወጥ ሆኖ ሳይሰበር መሰንጠቅ አለበት፡፡ ይህ የስንጠቃ ሂደት የሴትየዋ ችሎታ የሚለካበት በመሆኑ እያንዳንዱ ስፌት ሰፊ ተጠንቅቃ ነው የምትሰነጥቀው፡፡ ለእለቱ መስፊያ የሚሆናትን ከሰነጠቀች በኋላ እና ሁሉም ነገር መዘጋጀቱን ስታረጋግጥ ቢስሚላሂ በማለት ውጥኑን በትንሹ ክብ (ቀለበት) አስመስላ ማጠናከሪያ ሳሮች ትከብና በክቡ ቀዳዳ እያሾለከች መሀሉንትሰፋለች፡፡ ክቡ ከተጠናከረ በኋላ በረጅሙ ያሉትን ሳሮች ወደ መጀመሪያው ክብ በማስጠጋት በወስፌ እየተወጋ በተወጋው ቀዳዳ አክርማውን እያሾለኩ የመስፋቱ ሂደት በፍጥነት ይቀጥላል፡፡ ይህ ሁሉ ሲደረግ ዙሩበክብ መሄዱ እየተረጋገጠ በጥንቃቄ ስፌቱ ዝርግ ሆኖ መሄድ አለበት፡፡ቢስሚላሂ በማለት የምትጀምረው ስራዋንፈጣሪዋ እንዲያከናውንላት እናውጤታማ እንድትሆን መማጸኗ ነው፡፡

የስፌት ጅምር የተወሰኑ ዙሮች ተሰፍተውበት ካልጠበቁ በሁለት እና በሦስት ዙር አይተውም፡፡ ጅምሩ በወጉ ካልጠበቀ ሊበታተን (ሊፈርስ) ይችላል፡፡ የተጀመረው ውጥን ስፌት እያደገ እያደገ ወደ አስራ አምስት ዙር እንደ ተሰፋ ለሀማትሞቱ መቀመጫ ከስር ስለሚያስፈልገው ሰበዙን ሁለት ቦታ በመክፈል አንዱን ወደታች በመስበር ቁልቁል እንዲወርድ በማድረግ ከስር ያለው የ "በ" ቅርፅ በማስያዝ ይሰፋል፡፡ ሁለት ቦታ የተከፈለውና ከላይ ያለው ዙሩ የሚሰፋበት ሳር መጠነኛ የሆነ መጎድጎድ እንዲይዝ ተደርጎ ቀስበቀስ ስላች ቅርፅ ይዞ እንዲወጣ በማድረግ ይሰፋል፡፡ በዚህ የመስፋት ሂደት ጅምሩ ለዓይን ሞላ ማለት ከጀመረ በኋላ በተለያዩ ቀለማት የቀለሙ አለላዎችንና ቀርማዎችን በመጠቀም እያፈራረቁ የቀለማት ስብጥር በማድረግ ዲዛይኖች በስፌቱ ላይ በጥንቃቄ ይነደፋሉ፡፡ ወደታች የተሰበረው የሀማትሞት መቀመጫ የሚበቃውን ያህል በግምት ከተሰፋ በኋላ ይቆረጣል (ይደመደማል)፡፡ ከላይም ከስርም ያለው ሲቆረጥ ድምድማቱ በአንድ አይነት አክርማ ይሰፋል፡፡ በመጨረሻም በቀይ ቆዳ ይለጎማል፡፡ ለማስጌጫና ለመስቀያ የሚያገለግሉ ከቀይ ቆዳ የተሰሩ ቀጫጭን ማንጠልጠያዎች አራት ቦታ ይደረግበታል፡፡ ቆዳዎቹ በሚሰፉበት ቦታ ላይ ከስፌቱ ጋር በማያያዝ ሦስት ሐቀን (ዶቃ) በጌጥነት በአራቱም ቆዳዎች ማያያዥ ላይ ይሰፋል፡፡ ከዚህ በኋላ ለተፈለገው አገልግሎት ይውላል፡፡

ስለውጥኑ አጀማመር ወ/ሮ ቢፍቱ እንዲህ ብለዋል፡፡ "ጅምሩ ወይም ውጥኑ በልሙጥ በአረጓዴ ብቻ ይጀመራል፡፡ ከዚያም አረንጓዴውን ቀርጬ ነጬን እጨምራለሁ፡፡ ከዚያም እያለ እያለ እያደገ ይሄዳል" (ቢፍቱ፣ጥር 2004፣29)፡፡

ማህበራዊ ፋይዳ፡-በሀረሪዎች ዘንድ ሐማትሞት የሚባለው ይህ ቁስ ትልቅ ባህላዊ ፋይዳ አለው፡፡ ሃማት ሞትን ማንኛዋም የሀረሪ ሴት አትሰፋውም፡፡ አግብታ በመጀመሪያው የሙሽርነት አመት ላይ ያለች ሙሽራ ነች የምትሰፋው፡፡ ሙሽራዋ ካገባችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አንድ አመት ድረስ ለሷም ሆነ ለባሏ ምግብ አታበስልም፡፡ በባህሉ መሰረት ከባሏ ወላጆች ቤት ቁርስ፣ ምሳ፣ እራት ይመጣላቸዋል፡፡ በመሆኑም ሙሽራዋ በቤቷ ውስጥ ስራ ስለሌለባት ሐማትሞት ሰፍታ ለአማቷ እንድትሰጥ ባህሉ ያስገድዳታል፡፡

ወ/ሮ አሚና እና ወ/ሮ ዘቢዳ ስለመጀመሪያው የሙሽርነት አመት ሙሽሪት ምን እንደምታደርግ እንዲህ በማለት ይገልፃሉ፡፡

> *"ከአገባች በኋላ እስከ አመትዋ ድረስ ቁጭ ትላለች ምንም አትሰራም፡፡ ምግብ ደግሞ ከአማቷ ቤት ነው የሚያመጡት እስከዚያ ከቤት ምንም ስራ ስለሌላት ስራዋ ይህ ስፌት ነው፡፡"*

> *"እኛ አመት ሙሉ እንጀራ እናበላት ነበር እየሰራን እሷ አመት ሙሉ አትሰራም፡፡ እሷ ትወልድና ቤት እስክትመለስ ድረስ እኛ እናበላታለን፡፡... ወንድ ልጄን ስድር ሚስቱ ሰፍታ ትሰጠኛለች፡፡ ደንባችን ነው እንደ ደንቡ መሠረት ነው፡፡ እኛም እንሰጥ ነበር፡፡ ይሄም አንድ ልጄ የሰጠኝ፣ ይሄም አንድ ልጄ የሰጠኝ ነው፡፡ ወንዶቹ ልጆቹ ያገቧቸው ሚስቶቻቸው ይሰጡኛል" (አሚና፣ጥር፣ 2004፣ 11፣ ዘቢዳ፣ 11-12)፡፡*

ለአዲሷ ሙሽራ ሐማትሞት ትልቅ ጉዳይ የሚሸከም ቁስ ነው፡፡ በመሆኑም ሙሽራዋ ለአማቷ የምትሰጥበት የጊዜ ፍጥነት፣ እላዩ ላይ የሚያርፈው ዲዛይን ወዘተ. እያንዳንዳቸው ትርጉም አላቸው፡፡ ሙሽራዋ ለአማቷ በጥቂት ወራት ውስጥ ሰፍታ ሆነ ገዝታ ከሰጠቻት አማትዋ በልጇ ሚስት ከፍ ያለ ቦታ ተሰጥቷት በቶሎ ስለሰጠቻት ትወዳታለች፣ ታከብራታለች፣ ትኮራባታለች፡፡ ለጎረቤቶቿም ቁሱን

በማሳየት ልጇ ያገባት ወጣት ባለሞያ፣ ጠንቃቃና ሀላፊነትን መሸከም የምትችል መሆኗን በኩራት ትገልፃለች፡፡ ወጣቷም በሰጠችው ሐማትሞት ክብሯን ታገኛለች፡፡ ወልደው ያሳደጉኝ ቤተሰቦቹ ባለሞያዎች ናቸው፡፡ እኔም ሞያ አለኝየሚል መልእክት ትገልፅበታለች፡፡ በተጨማሪም ግዳጇን በመወጣቱ ማህበረሰቡ በጎ አመለካከት በኔ ላይ ይኑረው፣ ልከበር የሚል መልዕክት አለው፡፡ ለዚህም ነው ሙሽራዋ ጉዳዩን አስባበት በቶሎ ሰፍታ የምትሰጠው፡፡ ይህን እንድታደርግም ከቤተሰቦቿ ምክር ይሰጣታል፡፡ ምክንያቱም ይሄ ቁስ ነገ በማህበረሰቡ ውስጥ ለሚኖራት ቦታ ወሳኝ ሚና ስለሚጫወት እና ከባሏ ዘመዶች ጋር ለሚኖራት ቀጣይ የዕድሜ ልክ ቁርኝት ከፍተኛ ጠቀሜታ ስላለው ችላ ብላ እንዳታየው ለማድረግ ነው፡፡ አቶ አብዱ መሀይመን ስለ ሐማትሞት ትዕምርት እንዲህ ሲሉ ገልፀዋል፡፡

> *ሐማትሞት ትንሽናት፣ ውድናት፡፡ ከመውለድሽ በፊት ሰርተሽ ስትሰጪ ፊጥነሽ እንደሰጠሽ ነው፡፡ ፊጥነሽ ከሰጠሻት (ለአማትሽ) ልትኮራበት ነው፡፡ ለቅሶ ቤትም እንጀራ ይዛበት ትሔዳለች፡፡ እና እዛም ጎረቤቶቿ እዩ ይቺኮ ጥሩ ምራት አላት በማለት ያደንቋታል፡፡ ሐማትሞት መስጠት ከአማት ጋር ዲፕሎማቲክ ሪሌሽን ፈጠርሽ ማለት ነው፡፡ ጫጉላ ቤት ሆና ምግብ አትሰራም፡፡... እንዲሁ ቁጭ እንዳትል ጥበቡንም ለማሳየት ለአማቷ ሐማትሞት መስፋት ትጀምራለች፡፡ ሠርታ ትሰጣታለች፡፡ በወር በሁለት ወር ከተሰጣት ትኮራባታለች የልጁ እናት፡፡ ከመቼው ሰጠቻት ይባላል፡፡ እሷም ባለሙያ መሆኗ ይታወቃል፡፡ እና ሐማትሞት አንቺንና አማትሽን የሚያስተሳስር ነው፡፡ ከወለድሽ በኋላ ብትሰጪት ትራራቃላችሁ፡፡ ስለዚህ የልጁ ሚስት ፊጥና ሰፍታ መስጠቷ አማቷን በቁጥጥሯ ለማድረግ ይረዳታል፡፡አምስት ወንድ ልጅ ያላት አምስት ሐማትሞት አላት(ይመጣላታል)፡፡ ትኮራበታለች፣ እኔኮ የልጆቼ ሚስቶች ባለሙያዎች ናቸው ትላለች፡፡ እያቀያየረች ትይዛለች ያውቀዋል ሰው ሁሉ፡፡ ይቺ ደግሞ አዲሷ ናት በማለት ወይ ይቺ የታደለች እያሉ ይቀኑባታል (አብዱ መሀይመን፣የካቲት፣ 2004፣ 41)፡፡*

የሐማትሞት ተግባር ፈርጀ ብዙ ነው፡፡ ከቤት ውስጥ ጌጥነት እና ለቅሶ ቤት እንጀራ ከመውሰጃነት በዘለለ ማንነትን መገንቢያ ነው፡፡ በልጅቷም በኩል በልጁ ቤተሰቦችም

በኩል ራሳቸውን በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍ የሚያደርጉበት ነው፡፡ ያዲሱን ቤተሰብ ህልውና ማረጋገጫ ነው፤ ተከባብሮና ተፋቅሮ የሚኖር ቤተሰብ መገንቢያ ነው፤ ለባህሉ ያላቸውን ከበሬታ ማሳያ ነው፡፡ በመሆኑም ይሄ ትንሽ ቁስ በርካታ ትእምርቶችን የተሸከመ ባህላዊ ቁስ ነው፡፡ ወ/ሮ ዘቢዳ ይህ ቁስ ምን ያህል ተፅእኖ አሳዳሪ መሆኑን እንዲህ ሲሉ ገልፀዋል፡፡ "የልጄ ሚስት ስትሰጠኝ በጣም ደስ ይለኛል፡፡ እደስትበታለሁ... አሜሪካ እንኳን ቢጋቡ እናቷ ለኔ ትሰጠኛለች፡፡ ካልሰጠች አማቷ ትቀየማለች፡፡ ትልቅ ቁም ነገር ያለው ነው፡፡ የሷ ልጅም አሜሪካ ትሁን የኔም ልጅም አሜሪካ ይሁን እሷ እዚህ ለኔ ትሰጠኛለች-" (ዘቢዳ፣ጥር፣ 2004፣ 24)፡፡

ቁሱ ከመስጠት እና ከመቀበል ባለፈ የሚያመላክተው ጉዳይ አለ፡፡ የተሰጣት አማት በልጇ ሚስት ባለሙያ መሆን ደስታዋ ወሰን የለውም፡፡ ይሄ ደስታ ተራ ደስታ አይደለም፡፡ በልጇ የሚቀጥለው የትውልድ ሐረግ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው፣ ለራሱ ኩርቶ የእነሱንም ስም የሚያስጠራ፣ የነእገሌ ዘር በመባል ኩራት የሚሆን ስለሆነ ነው የምትደሰተው፡፡ በመሆኑም ሐማትሞት ከቤት ውስጥ መገልገያ ቁስነት ባሻገር በርካታ ትዕምርቶችን የተሸከመ ነው፡፡በቁሱና በማህበረሰቡ መካከል ያለው ቁርኝትምከፍተኛ ነው፡፡

አቶ አህመድ ዘከሪያ ይህን ሃሳብ በማጠናከር “baskets are essneital pieces of art for Harari. They have multivariuis seravices; ultilitarina aesthetic and symbolic” በማለት ገልፀዋል (አህመድ ዘከሪያ ውስተ siverman 1999)፡፡

ሐማትሞት የስፌዶች ሁሉ ቁንጮ የሆነ ከፍተኛ ሙያን የሚጠይቅ የስፌድ አይነት በመሆኑ በተለያዩ የስፌት ሞያዎች ውስጥ ተፈትና ያለፈች ሴት የምትሰፋው ነው፡፡ ከሚወስደው ጊዜ፣ እውቀትና ክህሎት አንፃር ሲታይ ለተሸከማቸው ትእምርቶች የሚመጥን ቁስ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ምራትየዋም ይህንን ቁስ ሰፍቶ የመስጠት ግዴታ ከነ ትዕምርቱ የተጣለባት አስተዳደጓ ባህሉን አውቃ፣ ለምዳ እና አክብራ ያደገች መሆኗን ለማረጋገጥ ጭምር ነው፡፡(schlerteh) በሞዴሎቹ ላይ የጠቀሰውን ማህበራዊነትን ልብ ስንል እዚህ ቁስ ላይ በማህበረሰቡ እና በቁሱ መካከል ያለው ተራክቦ ተግባራዊ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

### 5.1.2 ሌማትሞት



ሌማትሞት ከሌሎቹ የሐረሪ ስፌቶች አንፃር ሲታይ በጣም ትልቁ የስፌት ቁስ ነው፡፡ መሐሉ (ሜዳው) ዝርግ ሆኖ ግለቂያው አካባቢ ወደላይ ቀና ተደርጐ የሚሰፋ ቁስ ሲሆን ለመቀመጫነት የሚያገለግለው አነስተኛ እግር ከስር በኩል ያለው ቁስ ነው፡፡

አሰራር፡-ሌማት ከአክርማ፣ አለላ እና የገብስ ቀርማ የሚዘጋጅ ቁስ ነው፡፡ ለመስሪያነት የሚያገለግሉትም ወስፌ፣ መቀስ፣ ቀይቆዳ እና ሳሮቹን ለማራስ የሚያገለግል ሠፋ ያለ እቃ ያስፈልጋል፡፡

ሌማትሞት በቅርፅና በመጠን ከሌሎቹ ቁሶች ጋር ልዩነት ይኑረው እንጂ የአሰፋፍ ሂደቱ የሌሎቹን የአሰፋፍ ጥበብ የተከተለ ነው፡፡ ጅምሩ በቀለበት ቅርፅ ጠበብ ተደርጎ በርከት ያሉ ሳሮች በሌባ ጣት ላይ ይጠቀለላሉ፡፡ የተጠቀለለው ጥቅልል ከሀማትሞት ጅምር በመጠኑ ወፈር ያለ ነው፡፡ ቀለበት መሰሉን የአክርማ ጥቅል ጥቅጥቅ በማድረግ ይሰፋል፡፡ፋዙእንዳይሳሳ ሳፉ በደንበ እየተሳገ (እየተጨመረ) ይሰፋል፡፡ ተመሳሳይ የሆኑ የስጋጃ አይነቶች ይሰፉበታል፡፡ ዲዛይኖቹ እንደ ሀማትሞት አይበዙም፡፡መለስተኛ ዝርግ ሳህን የሚያክል ዝርግ ሆኖ ከተሰፋ በኋላ ለሌማቱ መቀመጫ የሚሆን እስከ ሰባትና ስምንት ዙር የሚሰፋ እግር ስለሚያስፈልገው በየዙሩ በአለላ ሚሸፈኑት ሳሮች ሁለት ቦታ በመክፈል የላይኛው

ቀድሞ እንደነበረው ዝርግ ሆኖ ይሰፋል፡፡ የታችኛው ቁልቁል ወደታች የ"በ"ን ቅርፅ በማስያዝ እየተሰፋ ቀስበቀስ በመጠኑ ዘርጠጥ በማድረግ አንድ የእጅ ጋት የሚያህል ከተሰፋ በኋላ ይቆረጣል፡፡ ሲቆረጥ ከአለላው ስራ የሚውለው ሳር ቀስበቀስ እያነሰ እያነሰ ይሰፋና በመጨረሻም ደጋግሞ በመስፋት እንዲጠብቅ ይደረጋል፡፡ የስፌት ስራው ሲያልቅ ከስርም ከላይም ያሉት ዙሮች በቆዳ ይለጐማሉ፡፡ የቆዳ ማንጠልጠያ ከሦስት ዶቃ ጋር በመስፋት አራት ቦታ ይደረግበታል፡፡

**አገልግሎቱ፡-** በሰርግ ጊዜ የተለያዩ የምግብ አይነቶች ለምሳሌ ሙጠበቅ[5]፣ ጁልጁል፣[6] ሙቃሊም[7]፣ ኢናይገበታ ተዘጋጅቶ በሌማቱ ይሞላና ሁለት ሰው ተሸክሞት ከሴቷ ቤት ወደወንዱ ቤት ይወሰዳል፡፡ በወንዱ ቤት የተገኙ ዘመድ አዝማድ እና እድምተኞች እንዲበሉም ይደረጋል፡፡ በመሆኑም ሌማት በርከት ላሉ ታዳሚዎች ለምግብ ማቅረቢያነት የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡

**ማህበራዊ ፋይዳ፡-**"እናይገበታ" ተብሎ ከሴቷ ቤት ወደ ወንዱ ቤት የሚመጣ የምግብ ዝግጅት አለ፡፡ በዚህ ስነ ስርአት ላይ ሙቃሊም፣ ጡፍጡፍ፣ ጁልጁልና ሙጠበቅ ተዘጋጅቶ በሌማት ሞት ተሞልተው ወደ ወንዱ ቤት ይላካል፡፡ ሰርጉ እሁድ ከሆነ እናይ ገበታ ማክሰኞ ይላካል፡፡

ኢናይገበታ የሚዘጋጅበት ዋናው ሰበብ ከሙሽራዋ ድንግልና ጋር በተያያዘ ሲሆን የድንግልና ሰርግ በመባልም ይታወቃል፡፡ በድሮ ጊዜ ሴት ልጅ ብልቷን ትሰፋለች፡፡ የተሰፋው አካሏ የሰርጓ እለት ስለሚላቀቅ ስቃይ አለው፡፡ በመሆኑም ይህንን ስቃይ እንድትረሳ በማለት እናይገበታ ለልጅቷ ክብር ተብሎ የሚዘጋጅ ስነ ስርአት ነው፡፡ ይህ ስነ ስርአት በሀረሪዎች በየዘመኑ እየተከበረ የመጣ ቢሆንም ጉዳዩ ከነብዩ መሐመድ ልጅ ከፋጡማ ጀምሮ የመጣ ነው፡፡ "በመጀመሪያ ኢናይገበታ የተዘጋጀላት

---

[5]በዳቦ ዱቄት የሚዘጋጅ የምግብ አይነት ሲሆን፤ የተቦካው ዱቄት በደንብ ሲቦካ በፈላ ዘይት ውስጥ ይጠበስና ቀላ ሲል በማውጣት ለምግብነት ይውላል፡፡

[6]የተፈተገ ሰሊጥ በእሳት ላይ ሞቅ ተደርጐ ቀለጥ ካለ ስኳር ጋር በመቀላቀል ድቡልቡል እየተደረገ የሚዘጋጅ የምግብ አይነት ነው፡፡

[7]ከፍየልና ከበግ አንጀት የሚዘጋጅ የምግብ አይነት ነው፡፡ አንጀቱ ፈርሱ ወጥቶ ከፀዳ በኂላ የተከተፈ ስጋ ውስጡ ተሞልቶ በደረቁ ይጠበሳል፡፡ የተከበረ የሐረሪዎች ተወዳጅ ምግብ ነው፡፡

ለፋጡማ ነው፡፡ እኛም እሱን ይዘን እስከ ዛሬ ድረስ እንከውነዋለን" (አቶ አህመድ ዘከሪያ ፣ሚ.ያዚ.ያ፣ 2004፣ አ.አ.ዩ)በማለት ገልፀውልኛል፡፡

ፀዳለ ካሣ በበኩሏ ስለ ኢ.ናይገበታ የሚከተለውን ገልፃለች፡፡ ኢ.ናይ ገበታ የሚባለው ልጃገረድ ክብረንፅህናዋን ጠብቃ የመገኘቷ የደስታ ዜና ወደ ወላጆቿ ሲላክ፣ ወላጆቿ ለሙሽሮቹ አዘጋጅተው የሚልኩት የምስራች ማዕድ ነው፡፡… በብሔረሰቡ ለዚህ መብቃትን ትልቅ ግምት ስለሚሰጠው ልጃገረድ በወላጆቿ ቤት ሳለች ለምትፈፅማቸው ቅን ተግባራት ሁሉ ቤተሰቧ የሚመርቋት ትልቁና ዋና ምርቃት ከኢ.ናይ ገበታ ጋር የተያያዘ ነው (ፀዳለ፣ 1983፣ 30)፡፡

| ሐረሪኛ | አማርኛ |
| --- | --- |
| ኢ.ናይገበታኘ ጭንስራ | የምስራች ማዕድሽን ለመሥራት ያብ ብቃኝ |
| ኢ.ናይገበታኘሸሌ ጭን ጨሪቅ ቤነሻወርለሽ | የምስራች ገበታሽን ስሰራ ወገቤ ቁርጥ ይበልልሽ |

ይህ ምርቃት ቤተሰብ የሴት ልጃቸውን ኢ.ናይገበታ አዘጋጅተው ወደ ወንዱ ቤት የሚልኩበት ቀን ታላቅ ደስታን የሚሰጣቸውና የሚረኩበት ቀን መሆኑን ይገልፃል፡፡ ምንም እንኳ የኢ.ናይገበታ ዝግጅት አድካሚ ቢሆንም እናት እሱን ስታዘጋጅ አደጋ እንኳ ቢደርስባት እንደማይከፋት የሚገልፅ ምርቃት ነው፡፡ በመሆኑም የኢ.ናይገበታ ሥነ ሥርዓት እጅግ ከፍተኛ ክብር ያለው አስደሳች እና ተናፋቂ መሆኑን ከዚህ ምርቃት መገንዘብ እንችላለን፡፡

ሌማትሞት እራሱን የቻለ ትርጉም ያዘለ ቁስ ነው፡፡ አንድ የሀረሪ ቤት ውስጥ ሲገባ ሌማት ካለ የዛቤት ባለቤት ሰዎች እድሜያቸው ከ60 አመት በላይ የሆኑ አዛውንቶች መሆናቸውን ማንም የብሔረሰቡ አባል ሰው ሳይነግረው ያውቃል፡፡ አቶ አብዱ መሀይመን ስለ ሌማት እንዲህ በማለት ይገልፃሉ፡፡ "ሀረሪዎች ቤት ያሉ ስፌቶች symbolic (ተምሳሌታዊ) [8]ናቸው፡፡ ለምሳሌ ሌማትን ካየሽ አንድ የሀረሪ ቤት ስትገቢ እነዛ ሰዎች እድሜያቸው ከ60 በላይ የሆኑ ሽማግሌዎች ቤት ነው፡፡ ሌማት ቤቱ

[8] ተምሳሌት እና ትምርት የተባሉትን ቃላቶች (symbol ) የሚለውን ቃል ተክተው የገቡ ናቸው፡፡

ያለው ሰው የእድሜ ባለፀጋ ነው" (አብዱ መሀይመን፣የካቲት 2004፣40)፡፡ከአቶ አብዱ መሀይመን ገለጻ የምንገነዘበው Schelereth የጠቀሰውን ሞዴል ማህበረሰብ ጠቃሽነትን ልብእንድንል ያደርጋል፡፡

ሌማት በማህበረሰቡ ውሰጥ ያለውን ትዕምርት አቶ አብዱ መሀይመን እንዲህ በማለት ይገልፁታል፡-

> *ሌማትሞት… ከጫጉላ ቤት ሲሄዱ ገበሬ በነበሩበት ወቅት ማሽላ፣ ሰሊጥ፣ በቆሎ ምናምን እርሻ ውስጥ ሊበቅል የሚችል ፅገረዳ አስቀምጠው ሙሽሪትን ይጠይቋታል፡፡ ይሄ ምንድ ነው? መቼ ነው የሚዘራው? በዚህ ጊዜ እያለች ትመልሳለች፡፡ ምንድነው ከቤት ትምህርት ወስዳለች ወይ? ቤተሰቦቿ ገበሬ ናቸው ወይ? የሚለውን እያንዳንዱን ይጠይቋታል፡፡ እና እሱን መልሳ ከጨረሰች ይቺ ደንበኛ ሀረሪ ናት ይሏትና ትዳሩ ይፀድቃል፡፡ ይሄንን ግን ባትችል ልትፈታም ትችላለች፡፡ የልጁ አባት ልጂ ናት እኮ ብሎ ይኮራባታል፡፡ ደጅ ደግሞ የሚበቅሉ ባህላዊ መድሃኒቶች አሉ፡፡ ይህ እንዲነው፣ ይህ እንዲህ ነው፣ ልጆች ከታመሙ ምግብ አልበላ ካሉ ይሄን ቆርጬ እስጠዋለሁ ካለች በቃ ይቺ የልጅ ልጄንም ታክማለች ብሎ የልጁ አባት ይመካባታል (አብዱ መሀይመን፣የካቲት፣ 2004፣ 41-43)፡፡*

ባሁኑ ሰአት በግብርና ሞያ የሚተዳደሩ ሀረሪዎች ቁጥር አናሳ ቢሆንም ቀደም ባሉት ጊዜያት በግብርና ይተዳደሩ ስለነበር የወንዱ ቤተሰቦች የልጃቸው ሚስት የተለያዩ እህሎችን ምንነትና መቼ መቼ እንደሚዘሩ የማወቅ ግዴታ ነበረባት፡፡ ያንፈተና በምትፈተንበት ወቅት ሌማትሞት የተባለውን ቁስ የእህሎቹን እና የመድሃኒቶቹን አይነት ተደርድሮበት ለፈተና የሚቀርብ የተከበረ ቁስ ነበር፡፡

እያንዳንዱ ቤተሰብ የራሱን መገልገያና የቤት ማጌጫ የሆነውን ስፌት መስፋት ግዴታው ስለሆነ በሀረሪዎች ዘንድ ስፌት መዋስ በጣም ነውር ነው፡፡ ስፌቶችን መዋስ ነውር መሆኑን አቶ አብዱ መሀይመን እንዲህ በማለት ይገልፃሉ፡፡ "በሀረሪ አንድም ቤተሰብ ከጎረቤት ስፌት ለመጠቀሚያ አያመጣም (አይዋስም) ነውር ነው፡፡ ከተዋሰ እንዴት አይኖረውም ይባላል" (አብዱ መሀይመን፣የካቲት፣2004፣43)፡፡ ነገር ግን

ሌማትን መዋዋስ ይፈቀዳል፡፡ ሌማት በጣም ትልቅ በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት ዋጋው 5000 (አምስት ሺህ ብር) ስለሆነ በማንኛውም ሀረሪ ቤት ሊገኝ ስለማይችል በሰርግና በድግስ ወቅት ሌማትን ተዋውሶ መጠቀም እንደ ነውር አይቆጠርም፡፡

ወ/ሮ አሚና በበኩላቸው ሌማትን ስለመዋዋስ እንዲህ ይላሉ "... ድሮ ሁሉም ቤት ነበር፡፡ አሁን የተወሰነ ቤት ነው ያለው፡፡... እየተዋዋስን እንጠቀማለን" በማለት ሌማትን መዋዋስ እንደሌሎቹ የስፌት ቁሶች ነውር አለመሆኑን ተናግረዋል፡፡

### 5.1.3 ጉፍተሙዳይ



ጉፍተሙዳይ ስያሜውን ያገኘው ከጠቀሜታው አንፃር ነው፡፡ ጉፍታ የተባለ ያገቡ የሀረሪ ሴቶች ለፀጉራቸው መሸፈኛ የሚጠቀሙበት ሻሽ አለ፡፡ ይህንን ሻሽ ከተገለገሉበት በኋላ የሚያስቀምጡት በዚህ ቁስ ውስጥ በመሆኑ የቁሱ መጠሪያ ጉፍተሙዳይ ተብሎ ተሰየመ፡፡የጉፍታ (ሻሽ) ማስቀመጫ ሙዳይ ማለት ነው፡፡

አሰራሩ፡ ጉፍተሙዳይ መክደኛና ተከዳኝ አለው፡፡ በመጀመሪያ ከስር ያለው ይሰፋል፡፡ ሂደቱ ሲጀመር በቅድሚያ ጅምር በጣት ላይ ክብ ሆኖ በመጠቅለል በአክርማ ይዘጋጃል፡፡ ከአክርማው የተወሰኑት ከጥቅሉ ይወጡና በተጠቀለለው ውስጥ እያስገቡ በማውጣት ክቡ ይደፈናል፡፡ ስፌቱ ዝርግ ሆኖ የተወሰነ ደረጃ ድረስ

ይሰፋል፡፡ዝርጉክፍል ከስር ያለና የማይታይ በመሆኑ ዲዛይን አይደረግበትም፡፡ እንዳመጣላቸው በተገኘ አለላ ይሰፉታል፡፡ አንድ ስንዝር ያህል ዝርግ የሆኑ ዙሮች ከተሰፉ በኋላ አክርማው ሁለት ቦታ ይከፈላል፡፡ አንዱ የተከፈለው አክርማ ወደታች ይሰበርና ወደታች ቀጥአድርጎ በማውረድ እስከ ሰባት ዙር የሚደርስ በቀጫጭኑተሰፍቶ ይቆረጣል፡፡ ከላይ የታችኛው ሲሰበር የቀረው አክርማ እስከ ሶስትና አራት ዙር በዝርጉ ይሰፋል፡፡ በመቀጠል ወደ ላይ በመስበር የጎርጓዳ ሳህን ቅርፅ እንዲኖረው በማድረግ (ከ12-14) ዙር ይሰፋል፡፡ በመጨረሻም መደምደሚያ በቀይ አለላ ዙሪያውን ይሰፋና ይቆረጣል፡፡

**የጉፍተሙዳይ ክዳን አሰራር፡-** ክዳኑ ወደ ላይ ረጅም ነው፡፡ መጨረሻው ጫፉ ላይ ያለችው (ቆጥ) ትባላለች፡፡ ቅርጿ አንድ ጣት በመሆኑ ለጅምርም ሰብሮ ለመስፋትም ታስቸግራለች፡፡ በትንሽ ክብ ጅምሩ ይወጠናል፡፡ከአለላው ስር የሚገባው አክርማ በጣም ቀጭን መሆን አለበት፡፡ ሁለት ዙር ከተሰፋ በኋላ ወደታች "በ" ቅርፅ ይሰፋል፡፡ የአንድ መሃል ጣት ርዝመት እስከሚኖረው በቀጭን ሰበዝ በቀይ አለላ እና በነጭ ቀርማ ይሰፋል፡፡ ርዝመቱ በቂ ሲሆን ዘርጠጥ ማድረግ ይጀመራል፡፡ የተዘረጠጠውም ትንሽ ወርዶ ያቆማል፡፡ አሁንም በማስከተል ወደታች ቀይ አለላ እና ነጭ የገብስ ቀርማ በመጠቀም ቀይና ነጭ ከለር እንዲይዝ ይደረጋል፡፡ አንድስንዝር ከተሰፋ በሁዋላ ቀስበቀስ ዘርጠጥ እየተደረገ ይሰፋል፡፡ ከዚያም ለስረኛው ግጣም መሆን የሚያስችል ስፋት ሲይዝ እንደስረኛው የመጨረሻው ዙር በቀይ አለላ ተደምድሞ ይቆረጥና ተካድኖ ይቀመጣል፡፡ ጉፍተሙዳይ እንደ ሌማትጥሞት እና ሐማትጥሞት በቆዳ አይለጐምም ተጨማሪ ጌጥም አይደረግበትም፡፡ ስለ ጉፍታ ሙዳይ አሰራር ወ/ሮ ከዲጃ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> *መጀመሪያ ከስር እንመጣና እዚህጋ እንሰብረዋለን ከዛ ከዚህ እንጀምራለን፡፡ እስከ ታች ሂደን እንቆርጣለን፡፡ የሚሰራው አገገሩ፣ ቀርማ፣ ነጭ ቀይ ቀርማ በተለያየ ቀርማና አገገሩ አድርገን እንሰራዋለን፡፡ በተለያየ ቀለም አክርማውን ነክረን እንደምንፈልገው ከለር እንጠቀማለን፡፡ አምስት ስድስት ከለር ከፋፍለን በድስት በድስት ቀለሙን እየቀቀልን እንጠቀማለን (ከዲጃ፣ጥር፣ 2004፣ 35)፡፡*

ጉፍተሙዳይን ሰፍቶ ለማጠናቀቅ በተከታታይ ቁጭ ብለው ከሰፉ አንድ ወር እንደሚፈጅባቸው ወ/ሮ ከዲጃ ገለፀውልኛል፡፡ ይህ ሁሉ ልፋት የወጣበት (የፈሰሰበት) ቁስ ሲሸጥ ምን ያህል ያወጣል ብዬ ላቀረብኩት ጥያቄ 800 ብር እንደሚሸጥ ነግረውኛል፡፡ አልፎ አልፎም ገበያ ሲሞቅ እስከ 1000 (አንድ ሺ) ብር እንደሚሸጡት ተረድቻለሁ፡፡

ስለ ጉፍተሙዳይ አገልግሎት ወ/ሮ ከዲጃ እንዲህ በማለት ይገልፁታል፡፡ "ይህኛው በኛ ጊዜ(ከ60 ዓመት በፊት) ከውስጡ ሳህን ይጨመርና ብስኩት ይጨመርና ወደ ሙሽራ ቤት እንወስድበታለን፡፡ አሁን ግን ናዚ[9]፣ ጉፍታ (ሻሽ)፣ ጌጣጌጥ እዚህ ውስጥ እንጨምርበታለን" በማለት የጉፍተሙዳይ የቀድሞውን እና የአሁኑን አገልግሎት ምን እንደሚመስል አስረድተዋል (ከዲጃ፣ጥር፣ 2004፣35)፡፡ከወ/ሮ ከዲጃ ገለጻ በምራፍ ሁለት ከተገለገልኩባቸው ሞዴሎች ውስጥ አገልግሎት ሰጪነትየሚለው ሞዴል ተግባራዊ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ምክንያቱም የቁሱ አገልግሎት ተቀይሯል ወይስ ያው ነው ሚለውን ለመመልከት ስለተገለገልንበትነው፤፤

ማህበራዊ ፋይዳ፡- ጉፍተሙዳይ አንዲት የሀረሪ ሙሽራ የሰርጓ እለት ይዛ ወደ ባሏ ቤት ከምትሄዳቸው ቁሶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ወ/ሮ ዘቢዳ ጉፍተሙዳይ በሙሽራዋ እንደሚሰፉና ማህበራዊ ፋይዳውን እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> *በፊት እኛ ለመዳሪያችን ሠርተን እናስቀምጥ ነበር፡፡ እንግስ (አለበለዚያ) ይገዛል፡፡ የአሁን ልጆች አይሰፉም ድሮ ግን ልጅቷ ነች የምትሰፋው፡፡ ይሄ ደግሞ የልጅቷን ባለሙያነት፣ ቤተሰቦቿ ሞያ እያስተማሩ እንዳሳደጓት ይገልፃል፡፡ ጉፍታ ሙዳይ ዛሬም አልቀረም ውጭ ላሉት ጭምር እንልካለን፡፡...ለአንድ ቀን ጉፍታ ታደርግና ያገባች እለት ከዛ ትተወዋለች፡፡ እከሊት ጉፍታ ተሰራች ይባላል፡፡ በሀረሪ ጉፍታ ያደረገቺ ሴት ያገባች ነች፡፡... አንድ ቀን ማድረጓም መልዕክት አለው ማግባቷን ይገልፃል፡፡ ሰርግ ቤት ስትሄድም ጉፍታ አድርጋ ትሄዳለች (ዘቢዳ፣ጥር፣ 2004፣ 28)፡፡*

[9]በግንባር ላይ የሚታሰር ጌጥ ሲሆን በጥቁር ቀጭን ጨርቅ ላይ ትንንሽ፣ ክብና ብልጭልጭ ጌጦች ተደርገውበት የሚዘጋጅ ነው፡፡

ጉፍተሙዳይ በጥንት ጊዜ ይሰሩ የነበረው በሙሽራዋ ነበር፡፡ አሁን ግን ይገዛል፡፡ ሙሽራዋ ጉፍተሙዳዩን ራሷ ከሰሩች የቤተሰቦቿን እና የሷን ማንነት ይገልፃል፡፡ ቤተሰባቸው ባለሙያ መሆኑን እና ልጅቷ ይህንን ጥያ ተምራ ማደጓን ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ሙሽራዋን በባሏና በባሏ ዘመዶች ፊት ልበ ሙሉ እንድትሆን፣ በራሷና በቤተሰቦቿ እንድትኮራ ያደርጋታል፡፡ ከስፌቶቹ ጋር በተያያዘ ሙሽሪት በሰርጓ እለት በሚዜዎቿ የሚዜሙላትን ዜማዎች ወ/ሮ አሚና እንዲህ በማለት ያብራራሉ፡፡ "ቤቷን ለማሳመር ትሰሩለች የዛኔ በሰርጓ ቀን ልትወጣ ስትል ማለት ነው፡፡ አጃቢዎቿ እሁድ ቀን እሷን እያጀቡ እያሞገሷት እስከ ቤቷ ድረስ ይሸኟታል፡፡ ሙገሳው ከሰራቻቸው ስፌቶች ጋር የተያየዘ ነው፡፡"

ዚሠፍታ ኢዝካም ዋለዳው ...............የሰፋሽውን ሰው ተሸከሞ አይችለውም፡፡

ማያጦርሴ ኢበታሉ ዜይበርካው .............................በፈረስ ተጭና ይሄዳል፡፡

በማለት ያሞግሷታል (አሚና፣ጥር፣ 2004፣ 11 እና 12)፡፡

ከሚገዛው ጉፍተሙዳይ ይልቅ በሙሽሪት የሚዘጋጀው የበለጠ ክበሬታን እንደሚያስገኝላት እና በሰርጉ እለትም የማሞገሻ ርእስ በመሆን አድናቆት እንድትቸር የሚያደርጋት ቁስ ነው፡፡ይህ ሁኔታ ደግሞ ለሙሽሪት ጠንካራ ስነልቦና እንድትጎናፀፍ ያደርጋታል፡፡

### 5.1.4 ሰጋሪወስክምባይ



ሠጋሪወስክምባይ

ሰጋሪ እና ወስክምባየ ተካድነው የሚቀመጡ ቁሶች ናቸው፡፡በመሆኑም ሲጠሩም በአንድ ላይ ሰጋሪወስክምባይ በመባል ነው፡፡ ሰጋሪ በዝርግ ሳህን መልክ የተሰራ የእጅ ስራ ስፌት ነው፡፡ከስርበኩል ለመቀመጫነት የሚያገለግል መቀመጫ አለው፡፡ወስክባይ ከላ□ በኩል ሾጣጣ የሆነ ስፌት ነው፡፡ ሰጋሪ በመጠን አነስተኛ በመሆኑ ለዚህ ተስማሚ የሆነ የወስክምባይ ክዳን ይሠራለታል፡፡ ሰጋሪወስክምባይ የሚሰቀለው በበሩ ፊት ለፊት ለመጽሐፍት መደርደሪያነት ከተዘጋጁት ሁለት መስኮቶች መካከል ነው፡፡

**አሰራር፡-** ስራው ከመጀመሩ አስቀድሞ ቢጫ የገብስ ቀርማ፣አረንጓዴ አለላ፣ ቀይ አለላ፣ ሰማያዊ አለላና ያልቀለሙ አክርማዎችይዘጋጃሉ፡፡ እነዚህ ጥሬ ቁሶች አንዱ እንኳን ቢጓደል ስራው ይቆማል፡፡ ዲዛይኑን እውን የሚያደርገው የአለላዎቹ አጣጣል በመሆኑ ተፈላጊው አለላ ከሌለ ስራው ይቋረጣል እንጂ በተገኘው የአለላ ቀለም አይሰፉም፡፡

ሰጋሪ በመጠኑ አነስ ከማለቱ ውጪ በቅርፁ ከሀማትሞት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ሠጋሪ ከሀማትሞት የሚለየው በቁሱ ላይ የሚሰፉት ዲዛይኖች አቀማመጥ እና በአላላ ቀለም ነው፡፡ ለሠጋሪ መስሪያነት የሚውሉት አለላዎች አረንጓዴ፣ ቢጫና ሰማያዊ ናቸው፡፡ ቢጫ የገብስ ቃርሚያ ስለሚበዛበት በጣም ያብለጨልጫል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከድምድማቱ በኋላ እንደ ሀማትሞት ዶቀና ቆዳ አይደረግበትም፡፡

የሰጋሪ ማጌጫ በሰበዝ ላይ ቢጫ፣ ቀይ፣ ሰማያዊ፣ አረንጓዴ አለላዎችን በመጠምጠም በየቀለማቱ ይዘጋጃል፡፡ በየቀለማቱ እጥፍእጥፍ እየተደረገ ከሠጋሪው ጋር ተያይዞ ይሰፋል፡፡ ይህ መደረጉ ለሰጋሪው ልዩ ውበት ይሰጠዋል፡፡

የሰጋሪ ክዳን የሆነው ወስክምባይ በቅርፅ ከጉፍተሙዳይ ክዳን ጋር ይመሳሰላል፡፡ የወስከምባይ አሰራር ከቆጥ (እናቱ ላይ ያለችው ቀጭኗ) ነው የሚጀምረው፡፡ የወስከምባይ ቆጥ እንደ ጎፍተሙዳይ በጣም ቀጭን አይደለም፡፡ በመሆኑም ለመስፋት በጣም አስቸጋሪ አይደለም፡፡ አክርማ በጠባብ በቀለበት ቅርፅ ተጠቅልሎ ወፈር በማድረግ ይጀመርና ሦስት ዙር እንደተሠፋ ወደታች ይሰበራል፡፡ "በ" ቅርፅ እንዲይዝ ተደርጎ ቁልቁል ይወርዳል፡፡ ይህ ቦታ ሲሰፋ መደቡ ቢጫ ቀርማ ይበዛበትና ነጭ አክርማ በቢጫው ላይ በሰላች እየተጋደሙ እንዲጠማዘዙ ይደረጋል፡፡ በነጩ አክርማ ውስጥ አለፍ አለፍ እያለ በአረንጓዴ አለላ ዳይመንድ ቅርፅ ያለው

ትንሽ የቢሳጥ ዲዛይን ይሰፋበታል፡፡ በመቀጠለም ስፌቱ እየተዘረጠጠ ይሄድና ሌላ ከቆጡ ሰፋ ያለ "በ" ቅርፅ እንዲይዝ ይደረጋል፡፡ ይህ ቦታ እንደ ላይኛው ቢጫ ቀርማ የበዛበት ቦታ ነው፡፡ በቢጫው ላይ አለፍ አለፍ ብሎ በነጭ አክርማ ላይ በሰማያዊ አለላ ስጋጃ ይሰራበታል፡፡ አራት ተመሳሳይ የሆኑ ስጋጃዎች በቅደም ተከተል ቁልቁል ከተሰፉበት በኋላ ስፌቱ የ"በ"ን ቅርፅ በመልቀቅ በጣም ዘርጠጥ እየተደረገ ይወርዳል፡፡ አሁንም መደቡ ላይ ቢጫ የገብስ ቃርሚያ እና ነጭ አክርማ ጎንለጎን በማደባለቅ ይሰፋል፡፡ በነጩም በቢጫውም ቀርማ ላይ በሰማያዊ አለላ ትንንሽ የቢሳጥ ዲዛይን ይሰፋበታል፡፡ የመቅናቱን ዲዛይን በአራት ረድፍ ከተደረደረ በኋላ የዲዛይን ለውጥ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ስድስትና ሰባት ዙር እንዳስፈላጊነቱ ዲዛይኖቹ ተሰባጥረው ይሰፋሉ፡፡በመጨረሻም አንድ ዙር በቀይ አለላ ሙሉውን ይሰፋና ይቆረጣል፡፡ በሰጋሪው ላይ የተደረገው ማስጌጫ ለወስከምባዩም ይደረጋል፡፡ ስራው ሲጠናቀቅ ሠጋሪው ከስር በአፉ በኩል ተደፍቶ ወስከምባዩ ከላይ ተደርቦበት በግርግዳ ለይ ይሰቀላል፡፡

ሰጋሪ ወስከምባይ ለግርግዳ ጌጥነት በመዋል ለቤቱ ውበት ይሰጣል፡፡ በፎቶው ላይ እንደሚታየው በጣም ደስ የሚል እና አይንን ማርኮ ለረጅም ደቂቃዎች መያዝ የሚችል ቁስ ነው፡፡ የዲዛይኖቹ አጣጣል፣ የቀለማቱ ስብጥር ውስብስብ በመሆናቸው ቀልብን ማርኮ በመያዝ የሰፊዎቹን የጥበብ ሚስጥር እንድናደንቅ የሚያስገድድ ማራኪ ቁስ ነው፡፡እዚህጋ በምራፍ ሁለት የተገለጸውን ጥበብን አመላካችነት የሚለውን ሞዴል ልብ እንድንል ያደርጋል፡፡

ሀረሪዎች እንግዳ መቀበያ ቤታቸው ዘወትር አምሮና ደምቆ እንዲታይ ስለሚፈልጉ ይህንን ክፍል ደሀውም ሀብታሙም ባለው አቅሙ ተጨንቆና ተጠቦ ያሳምራል፡፡ በመሆኑም ለስፌት ስራና ለስፌት ያላቸው አክብሮት ለየት ያለ ነው፡፡

ሰጋሪወስከምባይ በማን እንደሚሰፋ፣ መቼ ግርግዳ ላይ እንደሚሰቀልወ/ሮ አሚና እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ "... ልጅቷ ታገባና ከአመት በኋላ ሰፍታ ትሰቅላለች፡፡ ስትወልድ ቤቷን በዚህ ታሳምራለች፡፡ ከአመት በፊት አታደርግም፡፡ ድሮ ተለምዷል እንደዚህ ማድረግ" (አሚና፣ጥር፣ 2004፣10)፡፡

ከወ/ሮ አሚና ገለፃ እንደምንረዳው ሰጋሪ ወስከምባይ የሚሰፋው በተጋቢዋ ሙሽራ ሲሆን ይህ ቁስ የሚሰቀለው ልጅ ከተወለደ በኋላ ነበር፡፡ በመሆኑም ይህ ቁስ መውለድን፣ መክበድን፣ ሀላፊነትን መቀበልን ያመላክታል፡፡ የሀረሪ ብሔረሰብ አባል የሆነ አንድ ሰው በእንግድነት ሌላ ሀረሪ ቤት ቢሄድ እና ሰጋሪ ወስከምባይ በጌጥነት ተሰቅሎ በቤት ውስጥ ቢያይ እነዛን ሰዎች ልጆች አሏችሁ ወይ ብሎ አይጠይቅም፡፡ ምክንያቱም ቁሱ ከተራ ቁስነት እና ከጌጥነት የዘለለ ትዕምርት ስለተሸከመ፡፡ ቁሱ እራሱ ልጅ ወልደዋል የሚል መልእክት ነጋሪ ነው፡፡ ከዚህ እንደምንረዳው ቁሶች ለሰው ልጆች መረጃ ይሰጣሉ፡፡ አፍ አላቸው ይናገራሉ፡፡

ወስከምባይ በፎቶው ላይ እንደሚታየው ወደላይ የሾለ ክፍል አለው፡፡ ከስር ሰፊ ሆኖ ጀምሮ ቀስ በቀስ ወደ ላይ እየጠበበና ከፍ እያለ የመሄዱን ሚስጢር ቁሱ በሂደት ከፍ እያለ መሄዱ የሚያመላክተው ቀስ በቀስ የሚመጣ እድገትን፣ ቀድሞ ከነበረው ህይወት የተሻለ መመኘትን፣ ባለራዕይ መሆንን፣ ከዛሬ ይልቅ ነገ የተሻለ ህይወት እንደሚመጣ በመጠቆም የነገን ብሩህነት እና እድገት ይሰብካል፡፡ በመሆኑም ቁሶች በቀለማቸውና በዲዛይናቸው ብቻ ሳይሆን በቅርፃቸው ጭምር መልዕክት ነጋሪነታቸውን ከመረጃአቀባዮቼ መገንዘብ ችያለሁ፡፡

ማህበራዊ ፋይዳ፡- ሰጋሪወስከምባይ ለሁለት ተቃራኒ ማህበራዊ ስነ ስርአቶች ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ይኸውም ለሠረግና ለሀዘን ጊዜያት የሚያገለግል የባህል እቃ ነው፡፡ በሠርግ ጊዜ የተቆላ ቡና ይጨመርበትና ሰጋሪውወስከምባይ ተከድኖ ለሙሽራው ቤተስ በስጦታ መልክ ይሰጣል፡፡ በሀዘን ጊዜ በዚሁ ሰጋሪ ያልተቆላ ቡና ይጨመርና በወስከምባይ ሳይከደን በሟቹ የመጀመሪያ ሐዘን እለት ይቀርባል፡፡ ይህ ያልተቆላ ቡና በአሮቻ አባላት ተቆልቶ ተዘጋጅቶ ለሀዘንተኛ ይቀርባል፡፡

### 5.1.5 ሳንቡሳ



ሳንቡሳ የተባለው ቁስ ሦስት መአዘን ቅርፅ ያለው ቁስ ሲሆን ስሙን ያገኘው ሳንቡሳ ከተባለው የምግብ አይነት ነው፡፡ ቁሱና የተጠቀሰው የምግብ አይነት በቅርፅ አንድ ናቸው፡፡

የሳንቡሳ አሰራር አክርማውን ስንደዶውና የገብስ ቃርሚያ ከገበያ ይገዛል፡፡ እነዚህ ጥሬ ቁሶች በቤት ውስጥ ሙያው ያለው ሰው በብረት ድስት በቤት ውስጥ ያቀልሟቸዋል፡፡ አንዳንድ ሰዎች የተቀለመውን አለላ የሚገዙም አሉ፡፡ የጥሬ እቃ ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ማንኛውም ስፌት የምትሰፋ ሀረሪ ቤት ወስፌ፣ መቀስ እና ለአክርማውና ለቃርሚያው ውሀ ማራሻ የሚያገለግሉ ቁሶች ይኖሯታል፡፡ እነዚህ ጥሬ እቃዎች ዝግጁ መሆናቸው ሲረጋገጥ የስፌት ስራው ይጀመራል፡፡

አሰራር፡- የሳንቡሳ አሰራር ከሌሎቹ የስፌት አይነቶች ሁሉ የተለየ ነው፡፡ እየተወጋ አክርማና አለላ ቃርሚያ በቀዳዳው በማሾለክና በክቡ ሰበዙን እንዲሸፍን የሚደረግ አይደለም፡፡ ልጥፍ እና ሰፋፊ በመሆኑ በመጀመሪያ ውጥን (ጅምሩ) ሦስት ማእዘን ቅርፅ ያለው አክርማጠፍጠፍ ተደርጎ ሦስት ይዘጋጃል፡፡ አክርማው በቀይ አለላ ይሸፈናል፡፡ ሦስቱ ከተዘጋጀ በኋላ በደንብ እንዲጠብቁ ሦስቱንም በየማእዘኑ እያያዩ ይሰፋል፡፡ ይህ የጅምሩ ስራ ሲጠናቀቅ በመቀጠል ያለው ዙር በቢጫ፣ በአረንጓዴ፣ በቀይ አለላዎች እና በቀርማ እየተሰባጠረ በሰፋፊው ይሰፋል፡፡ ከጅምሩ ጭምር

አራቱም ዙሮች በዲዛይናቸው የተለያዩ ተደርገው ይሰፋሉ፡፡ በመጨረሻም ሰበዙ ሙሉ በሙሉ ሳይሸፈን አለፍ አለፍ በማለት በቢጫ የገብስ ቀርማ በቀጭኑ ይደመደማል፡፡ በማስከተልም በሰበዝ ላይ የተጠቀለሉ የተለያዩ አለላዎች ወጣ ገባ (ዝግዛግ) እየሰሩ ይሠፋበታል፡፡


የሳንቡሳ አገልግሎት እንደ ሌሎች የሀረሪ ቁሶች ሁለት አይደለም፡፡ በግርግዳ ላይ በመሰቀል ለጌጥነት በመዋል የቤቱን ውበት ማድመቅ ብቻ ነው አገልግሎቱ፡፡ መጠኑም ቢሆን ከሌሎቹ ዝርግ ቁሶች አንፃር ሲታይ አነስተኛ ነው፡፡

ማህበራዊ ፋይዳ፡-አቶ አብዱ መሀይመን እንዲህ በማለት ይገልፁታል፡፡"ሳንቡሳ የተባለውን የስፌት አይነት የሚሰቅሉት የመጀመሪያ ያገቡ ሰዎች ናቸው፡፡ አዲስ ተጋቢዎች በረኖ[10] ያሉ ተጋቢዎች ናቸው የሚሰቅሉት (አብዱ መሀይመን፤የካቲት፤ 2004፤40)፡፡ በማለት እነማን ናቸው ሳቡሳን የሚሰቅሉት የሚለውን ገልፀውልኛል፡፡ ከዚህ ገለፃ የምንረዳው ሳንቡሳ ግርግዳቸው ላይ የተሰቀለ የሀረሪዎች ቤት ካለ እነዛ ሰዎች አዲስ ተጋቢዎች ናቸው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የሀረሪዎች እያንዳንዷ ቁስ መልዕክት አላት፡፡ ይሄንንም አቶ አብዱ መሀይመን እንዲህ ሲሉ ገልፀውታል፡፡ "ሀረሪዎች ቤት ያሉ ስፌቶች (symbolic) ናቸው፡፡ ለምሳሌ ሌማት ካየሽ አንድ የሀረሪ ቤት ስትገቢ እነዛ ሰዎች እድሜያቸው ከ60 በላይ የሆኑ የሽማግሌዎች ቤት ነው" (አብዱ መሀይመን፤የካቲት፤ 2004፤ 40)፡፡ በመሆኑም እነዚህ አስገራሚ የሆኑ ትዕምርቶች የተሸከሙት የሀረሪ ስፌቶች ከማራኪ ዲዛይናቸውና ቀለማቸው ባሻገር በርካታ የማህበረሰቡን ሚስጢር የተሸከሙ ናቸው፡፡

ሳንቡሳ አንዲት ልጃገረድ በእናት አባቷ ቤት እያለች ለጋብቻ ከምታዘጋጃቸው ቁሶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ሴት ልጅ ትዳር መስርታ ከባሏ ጋር ጎጆ ቀልሳ ስትኖር በአዲሱ ጎጆዋ ውስጥ እንድትሰቅላቸው ከሚደረጉት ቁሶች ውስጥ ቀዳሚው ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ቁስ የሁለቱን ተጋቢዎች ደረጃ ይጠቁማል፡፡ ከልጅነት እና በቤተሰብ ሀሳብ ከማደር ወደ እማወራነት እና አባወራነት መሸጋገራቸውን ሀላፊነትን መሸከማቸውን የሚያሳይ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

[10]በረኖ የኦሮምኛ ቃል ሲሆን አዲስ ተጋቢ ሙሽሮችን የሚገልፅ ቃል ነው፡፡ ገና ያልወለዱ ባልና ሚስቶችን ይወክላል፡፡

## 5.1.6 ሚህካክናወስከምባይ





ወስከምባ

ሚህካክ

ሚህካክናወስከምባይ

ሚህካክና ወስከምባይ ተካዳኝ እና መከደኛ ናቸው፡፡ ሚህካክ የሚከደነው ሲሆን ወስከምባይ ከዳኑ ነው፡፡ ሚህካክ ማለት ምን ማለት እንደሆነ የአማርኛ ትርጉም የለውም፡፡ ወስከምባይ በአማርኛ ወስከንባ ተብሎ ከሚጠራው ቁስ ጋር በቅርፅ ይመሳሰላል፡፡ ስለዚህ መከደኛ ከዳን ማለት ነው፡፡

ሚህካክ በዛጉል ያጌጠ ከጠፍር የተሰሩ አራት ለመያዣነት የሚጠቅሙ ጆሮዎች እና ለመቀመጫነት ከስር በኩል ክብ የሆነ ጠርዝ ያለው ሰፌት ነው፡፡ ሚህካክናወስከምባይ በተለያየ ቀለሞች የተሰራ የሀረሪ ብሔረሰብን የእጅ ሥራ (ኢጂሲነት) ውበት የሚያንፀባርቅ ስፌት ነው፡፡

ሚህካክ በፎቶው ላይ እንደሚታየው ከሐማትሞት ጋር በቅርፅ ይመሳሰላል፡፡ ነገር ግን ሐማትሞት ማካደኛ ወስከምባይ የለውም፡፡ የሐማትሞት ማካደኛ እንደራሱ አይነት ነው፡፡ በዲዛይን ላይም መጠነኛ ልዩነት አላቸው፡፡ ያለላ ቀለም አጠቃቀም ልዩነታቸው በአሠራሩ ላይ ተብራርቶ ቀርቧል፡፡

የሚህካክናወስከምባይ አሰራር፡- ለሌሎቹ የስፌት ቁሶች የተገለፁት ጥሬ እቃዎች እና መስሪያ መሣሪያዎች ይዘጋጃሉ፡፡ ከዚያም ተሰንጥቆ ቀለም የተነከረው አክርማ፣ ቀርማ፣ በውሃ እንዲርስ ይደረጋል፡፡ በማስከተልም ያልተቀለመውን አክርማ በትንሽ

ጣት ጫፍ ላይ ይጠመጠማል፡፡ በመቀጠል የተጠቀለለው ትንሽ ክብ አክርማ እስኪደፈን ድረስ የራሰውን አክርማ ቀለም ሳይመረጥ በቀዳዳው በማሾለክ ይደፈናል፡፡ ከዚያም መጥበቁና መደፈኑ ሲረጋገጥ በወስፌው ጫፍ እንዳይበተን በጥንቃቄ እየተወጋ እክርማው ላይ አለላ እንዲጠመጠም ይደረጋል፡፡ ሦስት አራት ዙር ከተሰፋ በኋላ ጅምሩ (ውጥኑ) በደንብ ስለሚጠብቅ ከዚህ በኋላ በወስፌ እንደልብ ሳይቸገሩ ለመስፋት ዝግጁ ይሆናል፡፡ ይህን የመሰለው የውጥን ስራ ከተከናወነ በኋላ አስፈላጊ የሆኑ ቀለማትን በመምረጥ ዲዛይኑ ይጀመራል፡፡ አንዱ ዲዛይን ከሌላው እንዳይደባለቅ "መለያ" የምትባል የዲዛይን አይነት በየዲዛይኑ መካከል እንድትገባ ይደረጋል፡፡

ሚህካክና ሐማትሞት በቅርፅም በዲዛይንም ተመሳሳይ ቁሶች ናቸው፡፡ የሚህካክ ዲዛይኖች በብዛት ቀይ አለላን ሲጠቀሙ፤ የሐማትሞት ዲዛይኖች ቢጫ ቀርማ በብዛት ይጠቀማሉ፡፡ የዲዛይን አሰፋፉም ለምሳሌ ሐማትሞት በቀይ አለላ ከቦ ከላይ ወደታች አንድ አንድ ስጋጃ ሲደረድር፤ ሚህካክ በመጠነኛ ቀይ አለላ ይከብና ዲዛይኑን አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት እያደረገ የዲዛይኖቹን ቁጥር ቁልቁል እያበዛ (እየጨመረ) ይሄዳል፡፡

የሚህካክ "ወስከማባይ" አሰራር፡-የሚህካክወስከምባይ ከሰጋሪ ወስከምባይ ጋር ከማጌጫቸው ውጭ በቅርፅ አንድ አይነት ናቸው፡፡ በመሆኑም ከጅምሩ አንስቶ ቁልቁል የመውረድ፣ የመዘርጠጥ ሂደታቸው ተመሳሳይ ነው፡፡ ነገር ግን በዲዛይን አጣጣል ላይ ከፍተኛ ልዩነት አላቸው፡፡ "የሚህካክወስከምባይ" ሚህካኩ ላይ ያሉት ዲዛይኖች በሙሉ ይሰፉበታል፡፡ የሰጋሪ ወስከምባይ (የሰጋሪ ክዳን) ሰጋሪው ላይ ከተሰፉት ዲዛይኖች የተለየ ዲዛይን አለው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሁለቱ ወስከምባዮች ላይ ያለውን ዲዛይን ስናነፃፅር፣ "የሰጋሪ ወስከምባይ" በጣም የሚያብለጨልጭ ነው፡፡ይህም የሆነው በስፌቱ ላይ ቢጫ የገብስ ቀርማ በብዛት ጥቅም ላይ ስለሚውልና ሌሎቹ ዲዛይኖች በትንንሹ በአረንዴ አለላ ጣልጣል በመደረጋቸው ነው፡፡ "የሚህካክወስከምባይ" ግን ብዙዎቹን የዲዛይን አይነቶች የያዘ ሲሆን ቀይ አለላ በብዛት ይሰፋበታል፡፡

በመሆኑም እነዚህ ሁለት ወስከምባዮች በቅርፅ አንድ ናቸው፡፡ ነገር ግን የተለያየ ስም እንዲኖራቸው ያደረገው በቁሶቹ ላይ የተሰፋው ዲዛይን ነው፡፡ ዲዛይኖች ለቁሶች

የሚሰጣቸውን ስም እንዲይዙ ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ቁሱን ቁስያሰኘው ቅርፁ ብቻ ሳይሆን ዲዛይኑ ነው ማለት የምንችል ይመስለኛል፡፡ "Schelereth" ካቀረባቸው ሞዴሎች መካከል ጥበብን አመለካችነት በአስረጂነት ሊቀርብ ይችላል፡፡ ምክንያቱም ቁሶቹ በዲዛይኖቹ ተገልፀዋልና፡፡

ወ/ሮ አሚና የሚህካክን አገልግሎት መቼና ከየትኞቹ ቁሶች ጋር እንደሚሠሩ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡ "ያው ለቤት ጌጥነት ነው የሚውለው... ለአማቷ ሐማትሞት ከሰፉች በኋላ ይሄንን ሚህካክ እና ሰጋሪወስከምባይ ትሰፋለች፡፡ ሙሽሪት ከገባች በኋላ ባሏ ቤት የምትሰፋው እነዚህን እቃዎች መስፋት ግዴታዋ ነው፡፡ ስለዚህ ትሰፋለች" (አሚና፣ጥር፣ 2004፣ 11)፡፡

ማህበራዊ ፋይዳ፡-የሚህካክናወስክምባይ ማህበራዊ ፋይዳ የሠርገኞቹ የሴት ዘመዶች ወይም የሴት ጓደኞች "ጌሎች" እንዲሁም የአፎቻ (እድር) አባላት ለሙሽሮቹ በስጦታ መልክ ከሚያቀርቡት ቁሶች መካከል አንዱ ነው፡፡  ከዚህ በተጨማሪምአስቀድሞ ሐማትሞት ላይ እንደተገለፀው በሀረሪዎች ባህል አዲት ሙሽራ አመት እስኪሆናት በቤቷ ውስጥ ምንም አይነት ስራ አትሰራም፡፡ ነገር ግን በዚህ ከስራ ነፃ በሆነችባቸው ወራት እጇን አጣጥፋ ቁጭ አትልም፡፡ ቤቷን የምታሳምርባቸው ልዩ ልዩ ስፌቶችን መስፋት ይጠበቅባታል፡፡ ይህንንም እንድታደርግ ባህሉ ያስገድዳታል፡፡ መስፋት የማትችል እንኳን ብትሆን እናቷና ዘመዶቿ እንዲሰፉላት ታደርጋለች፡፡ እነሱም ካልሰፉላት ገዝታም ቢሆን እራሷ የሰፋችው አስመስላ ትሰቅላለች፡፡ ስፌት መስፋት ለአንዲት ሙሽራ ግዴታ መሆኑን ወ/ሮ አሚና እንዲህ በማለት ይገልፃሉ፡፡ "... ቁጭ ብላ መስፋት አለባት፡፡ ትሰፋለች፡፡ ከአማትዋ ቤት የሚመጣላትን ምግብ እየበላች ቤቷን ታሳምራለች፡፡... እያንዳንዱ ሙሽራ ቤት ይሄ መገኘት አለበት፡፡... ይሄ ሁለቱ (ሚህካክ እና ወስከምባይ) እንደተጣበቁ ነው የሚሰቀለው ግድግዳ ላይ" (አሚና፣ጥር፣ 2004፣12)፡፡

ማህበረሰቡ በስፌት ቤትን ማስጌጥን ከፍተኛ ግምት ስለሚሰጠው አንድ አመት ሙሉ ሙሽራዋን ከቤት ውስጥ ስራ ነፃ በማድረግ የስፌት ስራዎቹን እንድትሰፋ ያስገድዳል፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ሀረሪ ቤት እንዲኖሩ የግድ የተባሉ ስፌቶችን ከቻለች ሰፍታ ካልቻለች አሰፍታ ሁለቱም ካልተሳካላት ገዝታም ቢሆን ቤቷን የሀረሪ ቤት የማስመሰል ግዴታ አለባት፡፡

## 5.2 ከሸክላ የሚሰሩ ቁሶች

የሸክላ ቁስ በሀረሪ ማህበረሰቦች ዘንድ ረጅም እድሜ ያስቆጠረ ቁስ ነው፡፡ ለበርካታ አመታትም በቤት ውስጥ ለተለያዩ አገልግሎት ሲጠቀሙበት ቆይተዋል፡፡ በአሁኑ ሰአት በዘመናዊ እቃዎች በመተካት ምርቱም ሆነ ተጠቃሚነቱ በጣም እየቀነሰ የመጣ ቁስ ነው፡፡

በሀረር ከተማና በአካባቢው ባሉት የገጠር ቀበሌ ገበሬ ማህበራት የሚገኘው አፈር ለሸክላ ስራ ተመራጭ ነው፡፡ በመሆኑም በሸክላ ስራ ተግባር ላይ የተሰማሩ ሰዎች በጥሬ እቃነት የሚጠቀሙትን አፈር እንደልብና በቅርባቸው ያገኙታል፡፡ የሀረር አፈር ለቤት መምረጊያነት በሚውልበት ጊዜ ተቦክቶ እስከ ሶስት ቀን ድረስ ለምርጊት ይደርሳል፡፡ አንዳንድ የቾኩሉ ሰዎችም በሁለት ቀን ይመርጉበታል፡፡ ምርጊቱ ያለጭድ ተመርጎ ለበርካታ አመታት ጥንካሬውን እንደያዘ መቆየት ይችላል፡፡ በመሆኑም የአካባቢው የአፈር አይነት ለሸክላ ስራ ተስማሚ ነው፡፡ ፀሐፊ ትእዛዝ ገ/ስላሴ ስለ ሀረር አፈር ጠንካራነት "መሬቱ ግን አሸዋ ነው የግንቡም ጭቃ እንደ ኖራ የጠነከረ ነው፡፡ ስለዚህ አይፈረካከስም" (ገ/ስላሴ፣ 1959፣ 47) በማለት ገልፀዋል፡፡

በሀረሪ ማህበረሰቦች ዘንድ የሸክላ ስራ እንደ ስፌት ስራ ከቀን ወደ ቀን በአሰራር ጥበቡ እያደገና እየተሻሻለ ከዘመናዊ የፋብሪካ ስሪት ቁሶች ተፅእኖ ለመውጣት የሚያስችል እድገት ያሳየ ዘርፍ አይደለም፡፡ በነባር የአሰራር ሂደት ውስጥ እያዘገመ ስለሚገኝ የሙያው አድካሚነት ከሚገኘው ኢኮኖሚያው ጠቀሜታ አንፃር ሲታይ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

**የሸክላ አሰራር፡-** የእቃው አይነት ቅርፁና መጠኑ ይለያይ እንጂ የአሰራሩ ሂደት ተመሳሳይ ነው፡፡ አፈሩ ካለበት ቦታ የሸክላ ስራው ወደሚከናወንበት አካባቢ እንዲመጣ ይደረጋል፡፡ ከአፈሩ ውስጥ ቆሻሻ የሆኑ ባእድ ነገሮች ይወገዳሉ፡፡ አንኳሩን ለማስቀረት ይነፋል፡፡ በመቀጠልም ይቦካል፡፡ የቦካው ጭቃ በተፈላጊው ቁስ ቅርፅና መጠን በባለሙያዎቹ ይሰራል፡፡ አስፈላጊ ቅርፆች ሲጠናቀቁ በፀሀይ ሙቀት እንዲደርቅ ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም በእሳት ይቃጠልና በውስጡ ያለ እርጥበት ተሟጦ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ በሚቃጠልበት ወቅት አልፎ አልፎ ቁሶቹ ሊሰነጠቁ

ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ቁሱ ዋጋ እንዳያጣ የድግጣ ቅጠል ይቀባል፡፡ ስንጥቁ በጣም የጎላና የማይሸጥ ከሆነ ተሰባብሮ በድጋሚ ይቦካል፡፡

### 5.2.1 አፍላላኡፉ





አፍላላኡፉ ኡፉ

አፍላላ አንገቱ በጣም ረጅም ሆኖ መጠነኛ ሆድ ያለው የሸክላ ቁስ ሲሆን ክዳኑ (ኡፉ) ከላይ ረጅም ቀጭን ሆኖ አፍላሉ አፍ ላይ የሚገጠመው ክፍል ሰፋ ያለ የሳር ስፌት ነው፡፡

አፍላልኡፉ የሁለት እቃ ስም ነው፡፡ አፍላላየሚባሉት ከሸክላ የሚሰሩት እና ጥቁር ባህላዊ ቀለም ተቀብተው በዋናው ቤትከመደቡ በስተቀኝ ተደርድረው የሚቀመጡት አራት ቁሶች ሲሆኑ፤ ኡፉ ደግሞ የአፍላላ ክዳን ነው፡፡ ከአክርማ ስንደዶና ቀርማ የሚዘጋጅ ነው፡፡ ሁለቱ ባንድ ላይ ተካድነው ስለሚቀመጡ አጠራሩም አንድ ላይ አፍላላ ኡፉ ተብሎ ነው፡፡

አፍላላ በፎቶው ላይ እንደሚታየው ከቅርፁ አንፃር ራሱን ችሎ ቀጥ ብሎ መቆም ስለማይችል ለመቀመጫነት እንዲያገለግለው ከቃጫና ከኮባ የሚሠራ መቀመጫ ይዘጋጅለታል፡፡

የአፍላል አሰራር፡ ከሸክላ አፈር ሲሆን አዘገጃጀቱን ወ/ሮ ፈቲሀ እንደማከተለው ይገልፁታል፡፡

> *በመጀመሪያ ለሸክላ መስሪያ የሚሆን የሚጣበቅ አፈር ሌላ አሸዋማ ከሆን ፍርክስክስ ይላል፡፡ ሲያገኙ ቆፍረው ያወጣሉ ከዚያ ይነፉታል፡፡ ድንጋይና ኮረቱን በማውጣት ከዚያም ደቃቅ የሆነውን አፈር ያቦኩታል፡፡ ሲቦካ መቆየት አለበት፡፡ እየተመላለሰ እንዲብላላ፡፡ ከተብላላ በኋላ ነው ሰርተው ቅርፅ የሚያስይዙት፡፡ ቅርፅ ከያዘላቸው በኋላ ይደርቃል ፀሐይ ላይ፡፡ ከደረቀ በኋላ በእሳት ያቃጥሉት እና ያበስሉታል፡፡ እንዳይሰበር ማለት ነው፡፡ እሳት ያላገኘው ነገር ይሰበራል፡፡ ውሃም ሲያገኘው ይሟሟል (ፈቲሀ፣ጥር፣ 2004፣ ፣22)፡፡*

**የኡፉ (ክዳን) አሰራር፡-**ኡፉ የሚሰራው ከሣር ነው፡፡ አክርማ (ያልተቀለመ ሣር)፣ ቀይ አለላ እና ቢጫ የገብስ ቃርሚያ በዋናነት ለመሥሪያነት የሚውሉ ጥሬ ቁሶች ናቸው፡፡ ለቁሱ መሥሪያነት የሚያስፈልጉ ነገሮች ከተሟሉ በኋላ ውጥኑ ይጀመራል፡፡ አክርማ በትንሽ ክብ ተደርጐ በቀለበት ቅርፅ ይጠቀለልና በአክርማውና በአለላው ይሰፋል፡፡ ጅምሩ ሦስት ዙር ከተሰፋ በኋላ ወደታች ይሰበራል፡፡ የ"በ" ቅርፅ አስይዞ ቁልቁል ይወርዳል፡፡ የሚፈለገው ርዝመት ላይ ሲደርስ ዘርጠጥ ማለት ይጀምራል፡፡ በመጨረሻም በቀይ አለላ ተደምድሞ ይቆረጣል፡፡ አክርማ ላይ የተጠቀለሉ የተለያየ ቀለም ያላቸው አለላዎች ወጣ ገባ በማድረግ ፎቶው ላይ እንደሚታየው ጌጥ ይደረግበታል፡፡ ስራው ሲጠናቀቅ አፍላሉ ላይ ተከድኖ ለሚፈለገው አገልግሎት ይውላል፡፡ የኡፉ ቅርጽ የወንድ ብልት ይመስላል ፡፡በመሆኑም ባልየው ሲሞት ተዘቅዝቆ አፍላሉ ላይ እንዲከደን ይደረጋል፡፡ምክንያቱም ኡፉው የሚወክለው የማህበረሰብ ክፍል የቤቱን አባወራ በመሆኑ የኡፉው አቀማመጥ አባወራው ምንአይነት ሁኔታ ላይ እንዳለ ገላጭ ነው፡፡

የአፍላላ ጥቁር መሆን ሆን ተብሎ ለማሳመር ተጨንቀውና ተጠበው የሰጡት የቀለም አይነት ነው፡፡ በቀድሞ ጊዜ ሀረሪዎች ቤታቸውን የሚያሳምሩት በነጭ የኖራ ቀለም ነው፡፡ በመሆኑም የአፍላሉ ቀለም ጥቁር ሲሆን ከነጩ የቤት ውስጥ ቀለም ጋር ተቀናጅቶ ድምቀት ስለሚሰጥ ታስቦበት የሚደረግ ተግባር ነው፡፡ ስለ ጥቁርነቱ ወ/ሮ

ከዲጃ እንዲህ ይላሉ፡፡ "ድሮ ቀለም ሳይኖር ቀለም ከመኖሩ በፊት ቅርጣን የሚባል አለ እሡን እና ዘይት እንቀባዋለን እንዲያምርልን" (ከዲጃ፣ጥር፣ 2004፣ ፣37)፡፡

በአንድ እማወራና አባወራ ቤት ተደርድረው የሚቀመጡት አፍላላ ኡፋዎች አራቱም አራት አገልግሎት አላቸው፡፡ ወ/ሮ ከዲጃ እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡

"አራቱ አፍላላ ከነ ክዳኑ አፍላላ ኡፋ ይባላል፡፡ ደርድረን ለተለያየ አገልግሎት እናስቀምጠዋልን፡፡... ጫት በአመት የተወሰነ ጊዜ ስለሆነ የሚሸጠው ባልየው የሚሸጠውን የጫት ገንዘብ እዚህ አፍላል ውስጥ ያስቀምጥላታል፡፡ ሁለተኛው እስኪደርስ ድረስ እዚህ ውስጥ ያለውን ገንዘብ ትጠቀምበታለች፡፡ ሁለተኛው አፍላል ኡፋ ባህላዊ መድሃኒት ማስቀመጫ ነው፡፡ ዲገሎ[11]፣ የምች መድሃኒት፣ የመሳሰሉትን ባህላዊ መድሃኒቶች አድርቀን እዚህ ውስጥ እንጨምርና ልጆቻችንና እኛ ስንታመም ከህመሙ ለመፈወስ እንጠቀመበታለን፡፡... ሦስተኛው አፍላል ኡፋ ጌጣጌጥ ማስቀመጫ ነው፡፡ አራተኛው አፍላላ ኡፋ ዘር የሚቀመጥበት ነው (ከዲጃ፣ጥር፣ 2004፣ 36-37)፡፡

ከላይ ወ/ሮ ከዲጃ እንደገለፁት አፍላሎቹ ለጌጥነት ብቻ ሳይሆኝ የሚቀመጡት የየራሳቸውን አገልግሎት ለመስጠት ጭምር ነው፡፡ በሀረሪዎች አንዲት ሴት ባሏን መሸሩፍ[12] አትጠይቀውም፡፡ እራሱ አውቆ የመሸሩፍ ማስቀመጫ በሆነው አፍላል ውስጥ አስቀምጦላት ይሄዳል፡፡ እማወራዋም የተቀመጣላትን መሸሩፍ በመውሰድ የቀን ወጪዋን ትሸፍናለች፡፡ አባወራው መሸሩፉን ከመክተት ውጭ ከአፍላል ውስጥ ገንዘብ መውሰድ አይችልም፡፡ በባህሉ ነውር ነው፡፡ በአፍላል ውስጥ ያለውን ገንዘብ ወስዳ የምትረጠቀመው እማወራዋ ብቻ ነች፡፡ Dubois ስለ አፍላላ የተለያየ አገልግሎት የሚከተለውን ብለዋል፡፡ “Containers with Basket work upper Lid and under lid (no visible)for medicine, sweets, coins etc called “AFLALA” (Dubois, 2000,77).

---

[11]ለመድሃኒትነት የሚያገለግል የዛፍ ተቀጥላ ነው፡፡ ህፃናትና እርጉዝ ሴቶች ሲያማቸው ከፍየል ወተት ጋር በማፍላት የሚሰጥ ባህላዊ መድሃኒት ነው፡፡

[12]በየእለቱ፣ በየሳምንቱ ወይም በየወራቱ ለቤት መተዳደሪያ የሚውል ገንዘብ መሸሩፍ ይባላል፡፡

ማህበራዊ ፋይዳ፡-በሀረሪ ማህበረሰብ ዘንድ አፍላላ የሚወጣላት ሴት አግብታ የወለደች ሴት ናት፡፡ አፍላላውንም ባሏ ከቤተሰቦቹ በስጦታ መልክ ይሰጠዋል፡፡ የሚሰጡት አፍላላዎች ብዛት አራት ናቸው፡፡ ቤተሰቦቹ የሰጡትን አፍላላ በማምጣት ለትዳር አጋሩ ይሰጣታል፡፡ እማ ወራዋም አራቱንም አፍላል ኡፋ ጉንለጉን የሚታይ ቦታ ደርድራ ታስቀምጣቸዋለች፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ወ/ሮ ከዲጃ እንደ ቀጣዩ አብራርተዋል፡፡ "አፍላል የሚወጣለት ያገባ ወንድ ነው፡፡ ከቤተሰቦቹ ቤት ይሰጠውና ይዞ ወደ አዲሱ ቤቱ ይሄዳል፡፡... አፍላላ የሚወጣላት አንዲት ሴት ካገባች እና ከወለደተ በኋላ ነው፡፡ ከወለደች በኋላ ባሏ ያመጣውን አፍላል ደርድራ የሚታይ ቦታ ታስቀምጣለች" (ከዲጃ፣ጥር፣ 2004፣37)፡፡

አፍላላ በክብር ተደርድሮ የሚገኝበት ቤት ባልና ሚስት ተጋብተው ቢያንስ አንድ ልጅ የተወለደበት ቤት ነው፡፡ ይህ ባህላዊ ቁስ ያለበት ቤት ተጋቢዎቹ የሙሽርነት ጊዜ ጨርሰው እናት ወይም አባት መሆናቸውን ወልደው መሳማቸውን የሚገልፅ ቁስ ነው፡፡

የአፍላላ አንገት በፎቶ ግራፉ ላይ እንደሚታየው ረጅም ነው፡፡ ይሄ የሆነበትን ምክንያት አቶ አብዱ መሀይመን እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ "... አንዱ ዘር፣ አንዱ ጌጥ፣ አንዱ መዳኒት፣ አንዱ መሽሩፍ ይቀመጥበታል፡፡ አፍላል ለምን አንገቱ ረዘመ ካልን ልጆች እጃቸውን ከተው አፍላል ውስጥ የተከተተውን ነገር እንዳይወስዱ ለመከላከል ነው፡፡ አፍላል የሴቷ እቃ ነው አባወራውም ልጆቹም አይነኩም፡፡ ልጆቹም ስርቆት እንዳይምዱ ለመከላከል ነው" (አብዱ መሀይመን፣ የካቲት፣ 2004፣ 42)፡፡


ልጆች በመልካም ስነ ምግባር ታንፀው እንዲያድጉ ለቁሳዊ ባህሎቹ የተሰጠው ከበሬታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው እንገነዘባለን፡፡ በአፍላል ውስጥ ገንዘብና ውድ የሆኑ ጌጦች ይቀመጡበታል፡፡ ልጆች ይህ ቁስ እነሱ እንዲነኩት ስለማይፈቀድላቸው አይነኩም፡፡ አማወራዋም ይህን የማይሰበር ጠንካራ ባህል በመተማመን እነዚህ ቁልፍ የሌላቸው ቁሶች ውስጥ ውድ የሆኑ ጌጦቿን እና ገንዘብ ታስቀምጣለች፡፡ ባህሉ ለግሏ ያበረከተላት የተከበሩ ልዩ ቁሶች በመሆናቸው የሚያሰጋት ነገር አይኖርም፡፡

ቱሳዊ ባህሎች ከመደበኛው አገልግሎታቸው ውጭ በርካታ ትእምርት ተሸክመው የሚገኙበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ በመሆኑም አፍላል እና ኡፋ ከመከደኛ እና ተከዳኝነት ባለፈ በጌጥነት ለተቀመጡበት ቤተሰብ የሚናገሩት መልዕክት አላቸው፡፡ “ኡፋ” ቤተሰቡ ሰላም ፍቅር በነበረበትና አባወራው ከቤተሰቦቹ ባልተነጠለበት ወቅት ወደ ላይ መለል ብሎ የወጣ ውብ አንገቱን አሳምሮ አፍላሉ ላይ ይከደናል፡፡ የቤቱ አባወራ ቤተሰቡን በሞት ከተለየ ግን አፍላሉ ወደታች ተዘቅዝቆ ይከደናል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ወ/ሮ ከዲጃ እንዲህ በማለት ይገልፃሉ፡፡ "... እሱ ሲሞት ክዳኑ ይዘቀዘቃል፡፡ በዚህ ጊዜ ያቺ ሴት ባሏ ሞቶባታል የሚል መልዕክት ያስተላልፉል፡፡ ካልተዘቀዘቀ ግን ባልየው አልሞተም ማለት ነው፡፡ መሽሩፍም አላት ማለት ነው፡፡ ከተዘቀዘቀ ባልየው ሞቷል፡፡ መሽሩፍም የሚሰጣት የለም ማለት ነው" (ከዲጃ፣ጥር፣ 2004፤36)፡፡

የኡፋው ተዘቅዝቆ መከደን በዛ ቤተሰብ ውስጥ ያባወራውን በሞት መለየት ይናገራል፡፡ በተጨማሪም እማወራዋ ለቤተሰቦቿ ማስተዳደሪያ የሚሆናት የገንዘብ ወጪ የሚሰጣት ሰው አለመኖሩንና የቤተሰቡ ሀላፊነት ሙሉ በሙሉ እማወራዋ ላይ መውደቁን የአፍላል ኡፋው አቀማመጥ (position) ገላጭ ነው፡፡ በመሆኑም የኡፋው ተዘቅዝቆ መከደን የባልየውን መሞት ላልሰማሰው መርዶ ያረዳል፣ እማወራዋ ወጣ ገባ ሰትል ስታየው የሚያግዝሽ አጋርሽ የለምና በርቺ ጠንክሪ የሚል መልዕክት ይሰጣታል፡፡

ስለ አፍላላ ኡፋ በቀረበው ትንታኔ የ”Schlerth”ን ተምሳሌታዊነትና ማህበራዊነት የተባሉትን ሞዴሎች ለማጤን ባስረጅነት ሊቀርብ ይችላል፡፡ ምክንያቱም አፍላላ የማህበረሰቡን ተምሳሌታዊ ውክልና እና የዕርስ በዕርስ መስታጋብር አጉልቶ ያሳያል፡፡

### 5.2.2 ጊርጊራ



ጊርጊራ

ጊርጊራ በአብዛኛው ሀረሪዎች ዘንድ በቤት ውስጥ አገልግሎት በመስጠት ዛሬ ድረስ የዘለቀ ቁስ ነው፡፡ አገልግሎቱም እሳት እላዩ ላይ በማድረግ እጣን ለማጨሻነት ይጠቀሙበታል፡፡

የጊርጊራ አሰራር፡- ወይዘሮ ፈቲሀ እንደገለፁልኝ እንደሌሎቹ የሸክላ ቁሶች አሰራራቸው በመጀመሪያ ለሸክላ ስራ የሚሆን አፈር ተፈልጎ ይቆፈራል፡፡ ከአፈሩ ውስጥ ባእድ የሆኑ እንደ ድንጋይ፣ ሳር፣ እንጨት ወዘተ. የመሳሰሉት አላስፈላጊ ነገሮች እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡ ከዚያም አፈሩ በወንፊት ይነፋል፡፡ ለሸክላ ስራው ንፁህ አፈር ከተዘጋጀ በኋላ ይቦካል፡፡ በደንብ እንዲዋሀድ መልሰው መላልሰው ያቦኩታል፡፡ ለሦስት ቀንም እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ መቡካቱና በመብላላቱ ከተረጋገጠ በኋላ የሚፈለገው ቅርፅ (form) እየተሰጠው ይዘጋጃል፡፡ በማስከተልም በፀሃይ ላይ እንዲደርቅ ይደረጋል፡፡ በውሃ የመራስ እና የመፍረስ አደጋ እንይደርስበት በእሳት እርጥቡቱ እስኪወጣ ድረስ ይቃጠላል፡፡ ከዚያም ለሚፈለገው አገልግሎት ይውላል፡፡

አገልግሎት፡- ወ/ሮ ዘቢዳ ስለ አሰራሩ አጠር አድርገው ሲገልፁ “እኛ ገዝተን እሳት እናነድበታለን፡፡ እሳቱ ላይ እጣን አድርገን ጭስ እናጨስበታለን” (ዘቢዳ፣ጥር፣ 2004፣ 25)፡፡

ማህበራዊ ፋይዳ፡-ጊርጊራው ላይ ጭስ የሚጨሰው መቼ መቼ ነው የሚለውን ወ/ሮ ዘቢዳ እንዲህ በማለት ያስረዳሉ፡፡ "ሁል ጊዜ እናጨሳለን፡፡ እጃቸውን ወደ ዋናው በር መግቢያ መሀል ላይ እየጠቀሙኝ ጠዋት እዛ እናጨሳለን ወደ ማታ መከሪብ ጊዜ (ወደ በሩ እያሳዩኝ) በሩን አስጠግተን እናጨሳለን" (እንደላይኛው) በማለት አስረድተዋል፡፡

ጊርጊራ የተከበረ እቃና ልዩ ለሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚውል ቁስ ነው፡፡ በመሆኑም እጣኑ የሚጨስበት ሰአት ተለይቶ በቀን ሦስት ጊዜ የመንፈሳዊ ተግባር ክንውን ይካሄድበታል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ አቶ ጃሚ የተባሉ መረጃ አቀባይ እንዲህ በማለት ይገልፁታል፡፡

"ይህ ጊርጊራ በሀረሪ ብሔረሰብ ትልቅ ትርጉም አለው፡፡ ለእጣን ማጨሻነት ሀረሪዎች ይጠቀሙበታል፡፡የሚጠቀሙበት የተለየ ጊዜ እና ሰአት አላቸው፡፡…ጠዋት አብዱልቃዲር[13]፣ ቀን በርጫ[14] ላይ፣ መክሪብ እና ሚስቲያብ (ኢጃባ)[15] ላይ ይጨሳል፡፡ በቀን ሦስት ጊዜ ባልየውም ከእርሻ መጥቶ ጨስጨስ አድርገው ቅመው ተመልሰው ወደ እርሻ ይሄዳል (ጃሚ፣የካቲት፣ 2004፣33)፡፡

ጊርጊራው እጣን የሚጨስበት የቤቱን ጠረን መልካም መአዛ እንዲኖረው ለማድረግ አይደለም፡፡ ጠዋት፣ ቀትር ላይ እና አመሻሻ ላይ ጊዜው ሳይዛነፍ የሚያምኑበትን አምላክ የሚለማመኑበት እና መንፈሳዊ ስራን በሚሰሩበት ጊዜ ጊርጊራው አጋዥ ቁስ ነው፡፡ እንደተገለፀው ገበሬው ከእርሻ መጥቶ ተለማምኖ የሀገሩ ባህል የሆነውን ጫት ቅሞ ተመልሶ ወደ መደበኛ ስራው ይሄዳል፡፡ በመሆኑም በጊርጊራው ላይ የሚከናወነው መንፈሳዊ ተግባር በብሔረሰቡ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ለወ/ሮ ዘቢዳ ለምን እንደሚጨስ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ የሚከተለውን መልስ

---

[13]ከጀጎል ወጣ ብሎ ሱፌ ወረዳ ውስጥ ያለ ወልይ ነበር፡፡ የሱን ስም በመጥራት ሰዎች ይለምናሉ፣ ይማፀናሉ፣አማልደን ይላሉ፡፡

[14]ቀን ከስድስት ሰዓት ጀምሮ ያለው ሰዓት የበርጫ ሰዓት ይባላል፡፡ በርጫ ማለት ጫት መቃም የሚጀመርበት ሰዓት ነው፡፡ አንድም በርጫ የጫት መቃምን ስርአት በርጫ በማለት ይጠሩታል፡፡

[15]አመሻሽ ላይ ፀሐይ ስትጠልቅ ያለው ሰዓት ኢጃባ ይባላል፡፡ መላእክቶች የሚቀያየሩበት ሰዓት ነው ተብሎ ስለሚታመን ፀሎት የሚቀርብበትና ሰው ከራሱ ጋር የሚታረቅበትና ለፈጣሪው ፀሎት የሚያቀርብበት ሰዓት ነው (ግንቦት፣ 2004፣ አህመድ፣ አአዩ)፡፡

ሰጥተውኛል፡፡ "በቃ አላህ መሪም ብለን የሞተውን አስታውሰን እንመርቅና የድሮ እናቶች ፋታ[16] ያደርጉበታል"... (ዘቢዳ፣ጥር፣ 2004፣ 26)፡፡

እጣኑ በጊርጊራ የሚጨሰው የሞቱ ዘመዶቻቸውን የሚያመልኩት አምላክ የሰሩትን በደል ይቅር ብሎ በእምነታቸው መሠረት መልካም የተባለውን ስፍራ እንዲሰጥላቸው ለመማፀኛ ነው፡፡ በህይወት ላሉትም ምድራዊ ኑሮአቸው እንዲሰምር መለመኛና ተስፋን መቀበያ ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የእጣን ማጨስ ተግባር ተመላኪውን አምላኪዎቹ የሚፈልጉትን ነገር እንዲሰጣቸው ድምፃቸውን በማውጣት እና ከፍ በማድረግየሚለምኑበትና ታዳሚዎቹ የቀረበው ልመና እና ተማፅኖ እንደሚሰምር ተስፋ በማድረግ ደጋግመው አሜን በማለት የሚያረጋግጡበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማህበረሰቡ ይህን በጊርጊራ ላይ የሚከናወነውን የእጣን ማጨስ ተግባር ሲያከናውን ስነልቦናዊ እርካታ ስለሚያገኝ በስጋዊ ህይወቱ መረጋጋት፣ ተስፋ መሞላት እና ያለመፍራት ስሜቶች ይኖሩታል፡፡ እንዲህ መሆኑ ደግሞ ኑሮውን ለመምራት የተረጋጋ ስሜት እንዲኖረው ያስችለዋል፡፡

ጊርጊራ ቁስ ነው፡፡ እንደሌሎቹ ቁሶችም ተራ ቁስ አይደለም፡፡ ልዩ አክብሮትና ቦታ የሚሰጠው ቁስ ሲሆን ተግባሩንም ለማከናወን  የሚጠቀሙበት በእድሜ ገፋ ያሉ ትልልቅ ሰዎች ናቸው፡፡

በዙ የጊርጊራ ስርአትን ማን እንደሚያከናውን ሲገልፅ፡-

> *አው አባድር ዋነኛው የአባድር በአል የሚከበርበት ሲሆን የአባድር መካነ መቃብር በሚገኝበት እና በግንብ በተከለለው ግቢ ውስጥ ነው፡፡ በዚህ ቤት ውስጥ በቀይ ጃኖ ተሸፍኖ የሚኖረው የአባድር መቃብር አለ፡፡ ከቤቱ መግቢያ ግራና ቀኝ በጣም ትላልቅ የሆኑ ከሸክላ የተሰሩ ጊርጊራዎች አሉ፡፡ ጊርጊራዎቹ በሁለት ሽማግሌዎች አገልጋዮች ጠዋት ቀን እና አመሻሽ ላይ እጣን ይጨስባቸዋል፡፡ በግቢው ውስጥ በጣም ግዙፍ የሆኑ ወርካዎች አሉ በየወርካዎቹ ልዩ መአዛ ያላቸው እጣን እና*

[16]የፀሎት መክፈቻ ለማለት ነው፡፡ ጠዋት በር ሲከፈቱ አስቀድመው የሚፀልዩት ቀዳሚ የፀሎት ክፍል ነው፡፡

*ሰንደል በተቀበሩ ጊርጊራዎች ያለማቋረጠ ይጨሳሉ ዱአ[17] ይደረጋል እየተጨሰ (በዙ፤1980፤ 16-17)፡፡*

ጊርጊራ በተባለው ቁስ ሌላ የምናስተውለው ጉዳይ ቁሳዊ ባህል እና መንፈሳዊ ባህል እንዴት አንዱ አንደኛውን እንደሚያጎላ እና እንደሚገልፅ ነው፡፡ ጊርጊራው ቁሳዊ ባህል ነው፡፡ እጣን ተጨሶ የሚከናወነው የፀሎት ክንውን መንፈሳዊ ባህል ነው፡፡ በመሆኑም ለመንፈሳዊ ጉዳይ መሳካት ጊርጊራው ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከተ ነው፡፡ ለጊርጊራው ተፈላጊነት እና ህልውና ደግሞ መንፈሳዊ ክንውን መኖሩ የግድ ነው፡፡

ቁሳዊ ባህል ለመንፈሳዊ ባህል ምንጭ ነው፡፡ መንፈሳዊ ባህል ከቁሳዊ ባህል ቢመነጭም ቁሳዊ ባህልን እንዲያድግ ያደርገዋል፡፡ የነዚህ ሁለት መደጋገፍ የባህሉን ባለቤት የሆነውን ማህበረሰብ ማንነት በመግለፅ የበኩላቸውን እንዲወጡ ያደርጋቸዋል፡፡ ማህበረሰቡም ለመንፈሳዊ ባህሉ ከፍተኛ ከበሬታና ግምት ስላለው መንፈሳዊ ተግባራት ለሚከናወኑባቸው ቁሶችም ያለው አክብሮት ከመንፈሳዊው ያነሳ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም አንዱ የአንደኛው መገለጫ በመሆናቸው ነው፡፡

### 5.2.3 መስሎቶች



[17]ልመና ወይም ፀሎት ማለት ነው፡፡

መስሎላቲ ጀበና የሚመስል ቅርፅ ሲኖረው፣ ለያዘው ፈሳሽ ማውረጃነት እንደ ጀበና ሆዱ አካባቢ ጡት (ቀዳዳ) የለውም፡፡ በመጠኑም ከጀበና ከፍ ያለ ነው፡፡ ቅርፁም ከታች ሞለል ያለ ሰፊ ሆድ ሲኖረው አንገቱ ረዘም መለል ያለ ነው፡፡በአንገቱና በሆዱ መካከል ለመያዣነት የሚያገለግል አንድ ጆሮ አለው፡፡ በውስጡ ያለው ፈሳሽም የሚቀዳው በአፉ ነው፡፡

የመስሎላቲ አሰራር ቁሱን የሚሰሩ ሰዎች ለሸክላ ስራ የሚሆን አፈር ካለት ቦታ ቆፍረው ወደ ቤት ያመጣሉ፡፡ ከዚያም ከአፈሩ ውስጥ ባእድ የሆኑ እንደ ድንጋይ፣ እንጨት ሳር ወዘተ. ለቅመው ያወጣሉ፡፡ በማስከተልም አፈሩን ይነፉታል፡፡ የአፈሩ ንፁህ መሆን ከተረጋገጠ በኋላ ይቦካል እንዲብላላም መልሦመላልሶ ይቦካል መቡካቱ ከተረጋገጠ በኋላ የሸክላ ቁስ ስራ ይከናወናል፡፡ በመጀመሪያ የቡና ወይም የሻሂ መያገር□ው ክፍል ይሰራል፡፡ እሱ ንፋስ አግኝቶ መጠጥ ሲል አሁንም ይቀጠልበታል፡፡ ይህኛውም ንፋስ ወስዶ መጠጥ እንዲል ይደረግና አንገት ይገጠምበታል እያለ እያለ በሂደት ከስር ያለው ሲመጥ ተከታዩ እየተሰራ በቅደም ተከተል ሥራው ይከናወናል፡፡ ከዚያም አንገቱ አካባቢ የምትሰጠዋ ቅርፅ ትሰጥና ጆሮ ይቀጠላል፡፡ መጨረሻው ላይም የማለስለስ ተግባር ይከናወናል፡፡ መስሎላቲ ፈሳሹን ለማውረጃ የሚሆን ጡት የለውም፡፡ ቡናው ወይም ሻዩ የሚቀዳው በአፉ ነው፡፡ አቶ ኢድሪስ አብዲ ስለመስሎላቲ አገልግሎትና አሰራር ጠቅለል በማድረግ እንዲህ ብለዋል፡፡ "መስሎላቲ የቡና ሀሻራ ማፊያነት የምታገለግል ነች፡፡ የሚሰራውም ከሸክላ አፈር ነው፡፡ ሂደቱም እንደሌሎቹ ሸክላዎች ነው፡፡ አሁንም በሀረሪዎች ቤት አለ ቡና ማፍያና ማቅረቢያ ያደርጉታል" (የካቲት፣ 2004፣ እድሪስ፣ 49)፡፡

ይህ ቁስ በሀረሪዎች በተለይም በቀድሞ ጊዜ ቡና ለማፍያነት የሚያገለግል ቁስ ሲሆን አልፎ አልፎም ሀሻራ የተባለ ከቡና ፍሬ ገላባ የሚፈላ ሻይም ያፈሉበታል፡፡ ወ/ሮ ፈቲሀ ስለመስሎላቲ አገልግሎት እንዲህ በማለት ይገልፃሉ፡፡ "መስሎላቲ ቡናም ሻሂም ይፈላበታል፡፡... ሀረሪዎች በሰርግና በሀዘን ጊዜ ጥንት ይገለገሉበት ነበር፡፡ የብረት ጀበና ሳይኖር ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ትልልቅ እናቶች ናቸው የሚጠቀሙበት (ፈቲሀ፣ጥር፣ 2004፣ 20)፡፡

መስሎላቲ በብዙዎቹ ቤት የማይገኝ ጥንታዊ የቡናና ሀሻራ ማፍያ ሲሆን ከሸክላ አፈር የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ ሀረሪዎች ለሀዘንና ለሠርግ ይጠቀሙበታል፡፡ ዘመን እየሰለጠነ

ሲሄድ በፋብሪካ ውጤቶች እየተተካ በመሄዱ መስሎቱቲ በአሁኑ ሰአት የእድሜ ባለፀጋ የሆኑ ሀረሪዎች ቤት እና አደጋር በሚባለው ሀረር ባለው ሙዚየም ውስጥ እንደሚገኝ አጥኚዋ አረጋግጣለች፡፡ የቁሱ ከብዙዎች ሀረሪዎች ቤት መጥፋት ሰበቡ በፋብሪካ ውጤቶች መተካቱ ብቻ ሳይሆን ከገበያ ላይ መጥፋቱ እና ተሰባሪ በመሆኑ የፈላጊው ቁጥር እየቀነሰ በመምጣቱ መሆኑን ወ/ሮ ፈቲሀ እንዲህ በማለት ይገልፁታል፡፡ "ቴክኖሎጂ ያፈራቸውን ነገሮች ሁሉም መጠቀም ስለጀመረ፣ ሸክላም ስለሆኑ እድሜ ስለሌላቸው በገበያው ውስጥም ስለማይገኙ አሁን እየቀሩ ነው (ፈቲሀ፣ጥር፣ 2004፣22)፡፡ በማለት የተጠቃሚው ቁጥር ያነሰበትን ምክንያት ገልፀዋል፡፡

### 5.2.4 ማሰሮ



ማሰሮ ድብልብ ክብና ሆዱ ሰፊ ሲሆን አጠር ያለ አንገት አለው፡፡ በግራና በቀኝ ለመያዣነት የሚያገለግሉ ጆሮዎችም አሉት፡፡ አፉ ሰፊ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ገንፎ ለማገንፋት እንዲመች ታስቦ ነው፡፡

ማሰሮው ከሸክላ አፈር የሚዘጋጅ በመሆኑ በጥናቱ ውስጥ እንደተጠቀሰው እንደሌሎቹ ከሸክላ አፈር እንደሚዘጋጁት ቁሶች ተመሳሳይ ሂደት ስላለው ስለ አዘገጃጀቱ ደግሞ ማቅረቡ አስፈላጊ ባለመሆኑ አልቀረበም፡፡

ማሰሮ ገንፎ ለማገንፋት እና የተቆላ ድፍን ቡና በቅቤ ለመጥበስ የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡ የተቆላ ድፍን ቡና በቅቤ የሚጠበሰው በኦሮምኛ ቡነቀላ ይባላል፡፡ የባህል መወራረስ ስለሚኖር አንደኛው ማህበረሰብ ከአንደኛው ሊወርስ ይችላል፡፡ የትኛው ማህበረሰበ የጉዳዩ ባለቤት እንደሆነ የማረጋገጥ ሂደት የጥናቱ ትኩረት ባለመሆኑ አልተከናወነም፡፡

**ማህበራዊ ፋይዳ፡-**ይህ ቁስ እሳት ላይ ተጥዶ በውስጡ የሚጠበሰው ድፍን ቡና ለአምልኮ ተግባር የሚውል ነው፡፡ በአመት አንድ ጊዜ የሚከበር በየቤቱ የሚከናወን የአድባር ሥርአት አለ፡፡ በዚህ የአድባር ሥርአት ላይ ከሌሎች ቁሶች ጋር አንድ ላይ በመሆን የአምልኮ ስርአቱን ለመፈፀም ከሚያገለግሉ ቁሶች መካከል ማሰሮም አንዱ ነው፡፡ ወይዘሮ ዘቢዳ ስለ አድባር እንዲህ ይላሉ፡-

> *… የድሮ ሰው ሳናጤስ አንውልም አናድርም፡፡ አሁን እኛ እናደርጋለን ደጃችንም አድባር አለ፡፡ ሁል ጊዜ እናጨሳለን፡፡ በአመት አንድ ጊዜ ንፍሮ እንቀቅላለን፣ ቂጣ እንጋግራለን፣ ቡና እንቆላለን፡፡ ቡናው ተወቅጦ የሚፈላ አይደለም፡፡ ከቅቤ ጋር የሚቆላው ድፍን ቡና ነው፡፡ ኦሮሞዎቹ ቡነቀላ እንደሚሉት አይነት፡፡ በቅቤ ይከደናል፡፡ ከዚያ ጥሬ ቅቤ አምስት እናደረጋለን በመቁጠር ላዩ ላይ ቡናውን እናደርገዋለን ይበስላል፡፡ ከበሰለ በኋላ ሦስት ጊዜ ብቻ አሁንም ጥሬ ቅቤ እናደርጋለን፡፡ (ጥር፣ 2004፣ ዘቢዳ፣ 26)፡፡*

በአመት አንድ ቀን ለሚከበረውና ለሚከናወነው የአምልኮ ስርአት ድፍኑን ቡና ከቅቤ ጋር በማድረግ ለመቀቀል ማሰሮው አስፈላጊ ቁስ ነው፡፡ በመሆኑም ይሄ ቁስ ይሁነኝ ተብሎ ለዚህ አገልግሎት የሚዘጋጅ ቁስ በመሆኑ በአመት አንድ ጊዜ ብቻ በመውጣት ይሄ ተግባር እንዲከናወንበት ይደረጋል፡፡ አሁን አሁን ግን ቁሱ ቅቤ ስለሚፈላበት እና ቅቤውን በደንብ ስለጠጣው ለገንፎ ማገንፊያ ቆንጆ ነው በማለት አንዳንድ ሰዎች ቤት ገንፎም ይገነፋበታል፡፡

ቁሶች ከተራ ቁስነት ባለፈ ለአምልኮ መፈፀሚያነት በመዋል የሚገለገልባቸው በማህበረሰብ መንፈሳዊ እርካታ እንዲያገኝ የበኩላቸውን ያደርጋሉ፡፡ ቡናውን በብረት ድስት መጥበስ ይቻላል ነገር ግን በፍፁም አያደርጉትም፡፡ ምክንያቱም ቡናው

ለሚጠበስበት ቋስጭምር አክብሮትና ቅቡልነት በውስጣቸው ስላለ ቡናው በማሰሮው ሲጠበስ ትክክለኛ ነገር አደረግን ብለው ስለሚያስቡ ቅር የሚላቸው ነገር ስለማይኖር ይረካሉ፡፡ አምልኮ የፈፀሙበትም ነገር እንደሚሰምር አድርገው በተስፋ ይሞላሉ፡፡ በመሆኑም ቁሳዊ ባህሎች እንደየ አገልግሎት አውዳቸው ለፈጠራቸውና ለሚገለገልባቸው ማህበረሰብ የሚፈልግባቸውን ግዴታ ስለሚወጡ ማህበረሰቡም ለነሱ ያለው የእኔነት ስሜት እና አክብሮት ከፍተኛ ነው፡፡

## 5.3 ከቅል የሚሰሩ ቁሶች

በዚህ ርዕስ ከቅል የሚሰሩ ቁሶች እንዴት እንደሚዘጋጁ ፣ አገልግሎታቸው እና ማህበራዊ ፋይዳቸው ምን እንደሆነ ቀርቧል፡፡

የቅል ተክል በተፈጥሮ የሚገኝ ሲሆን አበቃቀሉም እንደ ሀረግ እያሳገ በአካባቢው በሚገኝ ማንኛውም ነገር ላይ እየተጠመጠመ በመውጣት ቅጠሎቹን እና ቅሉን ከመበስበስ አደጋ በተፈጥሮ ይከላከላል፡፡ቅል በሀገራችን በተለይም በገጠሩ ክፍል በጣም በርካታ አገልግሎቶች ስለሚሰጥ በእርሻው ውስጥ ቅል የበቀለለት ገበሬ እየተንከባከበ ያሳድገዋል፡፡ አልፎ አልፎም ይሁነኝ ተብሉ ቅል የሚዘራት ጊዜም አለ፡፡


ቅል በቤት ውስጥ መገልገያነት ሲውል ለወተት መያዣ፣ ለቅቤ፣ ለድልህ፣ ለሽሮ እቃነት፣ ለቡና መያዣ፣ ለሻይ መጠጫነት ወዘተ. በርካታ አገልግሎቶች ይውላል፡፡ በመሆኑም ህይወት የሰመረ ይሆን ዘንድ ቀደም ባሉት አመታት ቅል ያበረከተው አስተዋፅኦ ቀላል የማይባል ነው፡፡ ይህንን የቅል ቁሶች አገልግሎት በመገንዘብ ይመስላል ሲልቨር ማን "ሰዎች በእለት እለት ህይወታቸው የሚያስፈልጓቸውን መያዣዎች እና ልዩ ልዩ እቃዎች ከቅል ፍሬ የሚገኘውን ቅል በመጠቀም ያዘጋጃሉ በማለት የገለፀው" (Silverman፣ 1993፣ 39)፡፡

ከቅል የሚዘጋጁ ቁሶች እንደ ሸክላ ቁሶችና ስፌት ቁሶች የአሰራር ሂደት የላቸውም፡፡ በመጠናቸውና በቅርፃቸው ላይ መሠረታዊ ለውጥ ማድረግም አይቻልም፡፡ ቅሎቹ ደርቀው ለአገልግሎት ሲደርሱ ቅርፅና መጠናቸውን በማየት አገልግሎት ሊሰጡበት ለሚችሉት ጉዳይ መምረጥ እንጂ ቅሎቹን ሳያዩ አገልግሎቱን መወሰን አይቻልም፡፡ ለምሳሌ ለድልህ መያዣ የሚሆን ቅርፅና መጠን ያለው ቅል ለወተት መያዣነት

አያገለግልም፡፡ በመሆኑም አገልግሎቱን የሚወስነው ቅሎቹ በተፈጥሮ ያላቸው ቅርፅና መጠን ነው፡፡ ነገር ግን በጣም የረዘመን ቅል በስለት ከርክሞ አንገቱን ማሳጠር ይቻላል፡፡ አጠር ያለውንም በስንደዶና አክርማ የተወሰኑ ዙሮችን በአንገቱ ላይ በመስፋት መጠነኛ ርዝመት መጨመር ይቻላል፡፡

በቀጣዩ ክፍል ሀይቀዳድ (የወትቅል) እና ኢጃይ (የብርዝ ቅል) የተባሉትን ከቅል የሚዘጋጁ ቁሶች እንመለከታለን፡፡

### 5.3.1 ሀይቀዳድ



ሀይቀዳድ

ሀይቀዳድ የተባለው ቁስ ስያሜውን ያገኘው ከሚሰጠው አገልግሎት አንፃር ነው፡፡ ቅሉ ለወተት መያዣነት ስለሚያገለግል ሀይቀዳድ ወይም የወተት ቅል የሚል ስያሜ ተሰጠው፡፡

ለሀይቀዳድነት የሚያገለግሉ ቅሎች በመጠንና በቅርፅ አንድ አይነቶች ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ በተፈጥሮ የሚገኙ ቁሶች በመሆናቸው ከፍተኛ ባይሆንም መጠነኛ ልዩነት አላቸው፡፡ በመሆኑም አንዱ ከአንዱ ፍፁም ተመሳሳይ አይደለም፡፡

የቅል ቁሶች ከቆዳ፣ ከሸክላ፣ ከእንጨት ወዘተ. ቁሶች ጋር የሚያመሳስል የአሰራር ሂደት የላቸውም ቢባልም የያዙት ቅርፅና መጠን ሳይለወጥ የተወሰነ የአዘገጃጀት

ሂደት ይደረግባቸዋል፡፡ የቅል ቁሶች ለቤት ውስጥ መገልገያነት ሲታሰቡ እንዴት እንደሚዘጋጁ ወ/ሮ ፊቲሃ እንደሚከተለው አስረድተዋል፡፡

> *"ቅሉ በቅሎ ሲበስል ወይም ሲደርቅ ይቆረጣል፡፡ አፉ በሚፈለገው ስፋት በቢላዋ ተቆርጦ ይስተካከልና በቆዳ ይሸፈናል (ይለጎማል)፡፡ ከዚያም የሚመር ጣዕም ቅሉ ስላለው እሱ እንዲለቅ ለበርካታ ቀናት በውሃ ይዘፈዘፋል፡፡ ሲርስ ወደ ውስጥ በሚገባ ነገር የቅሉ ውስጠኛው አካል ላይ ያሉ መልቀቅ የሚችሉ ነገሮች በሙሉ እንዲለቁ ይደረጋል፡፡ ከዚያም ቅሉ በደንብ ከፀዳ በኋላ ወይራ በተባለ የማጥንት እንጨት በተደጋጋሚ ይታጠናል፡፡ ከዚህ በኋላ ምሬቱ ስለሚለቅ እና የወይራውን መልካም መአዛ ስለሚይዝ ለተፈለገው አገልግሎት ይውላል (ጥር፣ 2004፣ ፊቲሀ፣ 18)፡፡*

የቅል ቁሶች በተፈጥሮ የሚገኙ ቢሆንም ከተክሉ ላይ ቆርጠ በመውሰድ ቀጥታ ለአገልግሎት አይውሉም፡፡ በባለሙያ አስፈላጊውን የክንውን ሂደት ካለፉ በኋላና ለአገልግሎት ዝግጁ መሆናቸው ሲረጋገጥ ለተፈለጉበት አላማ ማዋል ይቻላል፡፡

ሀይቀዳድ እንደሌሎቹ የቅል ቁሶች የዝግጅት ሂደቱ ሲጠናቀቅ ለወተት መያዣነት አገልግሎት መዋል ይጀምራል፡፡ በእድሜ የገፉ ሰዎች እንደ ሚናገሩት ቅሉ ከታጠበ በኋላ ወይራ በተባለ የእንጨት ጭስ ሁል ጊዜ ስለሚታጠን በቅል ውስጥ የሚቀመጥ ወተት በጣም ደስ የሚል መአዛ አለው በማለት የፋብሪካ ስሪት ከሆኑት እቃዎች ይልቅ የቅል ቁሶች ለወተተ መያዣነት ተመራጭ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡ ለዚህም ይመስላል ቀደም ባሉት ጊዜያት አራስ ለመጠየቅ፣ በሽተኛን ለመጎብኘት እና የቅርብ ዘመድ ለመጐብኘት ሲታሰብ ወተት በቅል ጠልጠል ተደርጎ የሚኬደው፡፡

በሀገራችን የቅል ቁሶችን ለወተት መያዣነት የሚጠቀሙበት ሀረሪዎች ብቻ አይደሉም ሌሎች ማህበረሰቦችም ይጠቀሙበታል፡፡ በበርካታ አካባቢዎች በዘመናዊ እቃዎች ሳይተካ እስከ ዛሬ ድረስ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

### 5.3.2 ኢጃይ



ኢጃይ ማለት የብርዝቅል ማለት ነው፡፡ ኢጃይ ከሌሎች ቅሎች ቅርፁና መጠኑም ለየት ያለ ነው፡፡ አንገቱ በጣም ረጅምና ቀጭን ሲሆን ከስር የሚገኘው ሰፊ ክፍል የእንቁላል ቅርፅ ያለው ነው፡፡ የቅሉ አንገት እና የመያዣው ክፍል እንዲህ አይነት ቅርፅ መያዛቸው ቅሉን ገና ሲያዩት አይን ገቡ ያደርጉታል፡፡ በፎቶው ላይ የሚታየው ኢጃይ ምንም አይነት መጊያጊያጫ ሳይደረግበት የቀረበ ኢጃይ ነው፡፡ በመሆኑም የቅሉን ውበት ልብ ይሏል፡፡

ስለ ኢጃይ አዘገጃጀት ስንመለከት በተፈጥሮ የሚገኝ ቅል በመሆኑ ወ/ሮ ፈቲሀ ስለ ሀይቀዳድ (የወተት ቅል) አዘገጃጀት የሰጡት ማብራሪያ ለኢጃይም እንጠቀምበታለን፡፡ ኢጃይ ምንም አይነት ዶቃና ማስጌጫ አይደረግበትም፡፡

አገልግሎት፡- ኢጃይ ማር ለመያዣነት የሚያገለግል ቁስ ሲሆን ወ/ሮ ፈቲሃ የገለፁትን ሂደት ተግባራዊ ተደርጎ ከተዘጋጀ ማሩ ለረዥም ጊዜ ሳይበላሽ ይዞ ማቆየት ይችላል፡፡

ማህበራዊ አገልግሎት፡-እጮኛ ላላት ልጃገረድ ማር ተበጥብጦ ወደ ልጅቱ እጮኛ ዘንድ ይላክበታል፡፡ የተበጠበጠው ማር ለምን ወደ ለጁ ቤት ይላካል ለሚለው ጥያቄ ወ/ሮ ፈቲሀ ምክንያቱን እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

“ማሩ የሚላክበት ምክንያት አለ፡፡ እጮኛ ላይ እያሉ ሳይጋቡ እህል ሲቆረጥና እህሉ እቤት ሲገባ የሷ ድርሻ ተብሎ ለሷ የሚሆን አንድ ኩንታል እህል ሲልኩ የወንዱ ቤተሰቦች የሴቷ ቤተሰቦች በዚህ ማር በጥብጠው ወንድየው ቤት ይልካሉ፡፡… እርሻው ላይ ደክመው ስለሚገቡ ይሄ ማሩ ብርታት ስለሚሰጣቸው ነው” (ፈቲህ፣ጥር፣ 2004፣18)፡፡ ወ/ሮ ፈቲህ ከሰጡት ገለፃ በተጨማሪ በዙ፣ 1980 ስለ ኢጃይ የሚከተለውን በመግለጽ ቁሱ ከማህበረሰቡ ጋር ያለውን ትስስር ያስረዳል፡፡

> *የሰርጋቸው ጊዜ ሲቃረብ ከወንዱ ቤተሰቦች በልዩ ልዩ ቀለማት ያጌጡ ልብሶች ከአንድ መቶ ብር ጋር ለልጅቷ ወላጆች ጥሎሽ ይሰጣል፡፡ የጋብቻው ጊዜ አስር ቀን ሲቀረው አስራ ሁለት ሸክም እንጨት ልጅቷ ወላጆች ቤት በራፍ ላይ በመጣል የማስጠንቀቂያ ምልክት ይሰጣል፡፡ የልጅቷ ወላጆችም በሁለት ቅሎች የተሞላ የማር ብርዝና አንድ እስር ነጭ ሽንኩርት ለወንዱ ወላጆች በመላክ መዘጋጀታቸውን ያረጋግጣሉ (በዙ፣ 1980፣16-17)፡፡*


ኢጃይ የተባለው የቅል ቁስ በባህሉ ለተከበረው ለጋብቻ ትስስር ከሴቷ ቤተሰቦች ለወንዱ ቤተሰቦች አይዟችሁ አታስቡ ተዘጋጅተናል የሚል መልዕክት ተሸክሞ ወደ ወንዱ ቤተሰብ ለመላክ የተመረጠ ምርጥ እቃ መሆኑን እንረዳለን፡፡ የማሩ ብጥብጥ (ብርዙ) የሚላከው በጠርሙስ ወይም በጀሪካን በአይደለም በኢጃይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ቁስ ማህበረሰቡ ለተከበረ አገልግሎት ለመልዕክት አድራሽነት እምነቱን ጥሎበት መርጦታል፡፡ ይህንንም ከላይ የጠቀስናቸው ሁለት መረጃ አቀባዮች በተለያዩ አገላለፆች አስረድተዋል፡፡

## 5.4 ከእንጨት የሚሰሩ ቁሶች

እንዲህ እንደዛሬው ፋብሪካ ሰራሽ ቁሳቁሶች ሳያጥለቀልቁን የሰው ልጅ ህይወቱን ቀላል እንዲሆንለት ካስቻሉት ነገሮች መካከል እንጨት እና ከእንጨት የሚገኙ ቁሶች መሆናቸውን እንገነዘባለን፡፡ አሁን ባለንበት ዘመን ጭምር ከእንጨት የሚሰሩ ቁሳቁሶች በጣም ተፈላጊእና ተመራጮች ናቸው፡፡ ሆኖም ግን የደኖች መመናመን እና የእንጨት እንደልብ አለመገኘት የቁሳቁሶቹ ዋጋ እንዲንር አድርጎታል፡፡

ቢሆንም ዘመናዊ የተባሉት እቃዎችችን ለምሳሌ ጠረጴዛ፣ወንበር፣ ቡፌ፣ መፅሐፍ መደርደሪያ፣ የደረጃ መወጣጫ ወዘተ ገዝቶ ቤቱን ማሳመር እና ማደራጀት የማይፈልግ ማንም የለም። በመሆኑም ከእንጨት የሚሰሩ ቁሶች ተፈላጊነታቸው ጥንት ብቻ ሳይሆን ዛሬም ድረስ የዘለቀ ነው። በዚህ ክፍል ገበታ፣ ጭልፋና ወንበር ተተንትነው ቀርበዋል።

### 5.4.1 ቆሪ (ገበታ)



ገበታ

በሀረሪ ማህበረሰቦች ዘንድ በእንጨት ከሚሰሩት ቁሶች መካከል ገበታ ዋነኛውና ትልቁ ሲሆን ጉድጓዳና አፉ ዘርጠጥ ብሎ በጣም ሰፊ የሆነ ክብ ቁስ ነው።

የገበታ አሰራር የዋንዛ እንጨት ይፈለግና ይቆረጣል። ሙያው ያላቸው ወንዶች የተቆረጠረውን የዋንዛ እንጨት በተፈላጊው መጠን ይቆርጡታል። ከዚያም በአነስተኛ መጥረቢያ እያስተካከሉ የውጭውን ክፍል ቅርፅ ይሰጡታል። ይህን ከጨረሱ በኋላ የውስጠኛውንና መጎድጎድ ያለበትን ክፍል እየቦረቦረ ያጎደጉዱታል። አልፎ አልፎም የፍም እሳት መሀሉ ላይ በማስቀመጥ መሀሉ እንዲቃጠልላቸው በማድረግም ያጎደጉዱታል። የተፈለገው ደረጃ ላይ ሲደርስ ይለሰልሳል። በመጨረሻም ውስጡም ውጭውም ጥቁር ቀለም እንዲኖረው ይደረጋል። የገበታ ቀለም ጥቁር እንዲሆን ለምን እንደተፈለገ ወ/ሮ ፈቲህ እንዲህ በማለት ይገልፃሉ


“ጥቁር ቀለም መቀባቱ ድሮ ቤታቸው ቀለሙ ነጭ ስለሆነ ይህ ጥቁር ሲሆን ቤቱን ውበት እንዲሰጥ ነው” (ፈቲህ፣ጥር፣ 2004፣ 19)፡፡ በማለት ቀለሙ ይሁንኝ ተብሎ ለውበት ሲባል መቀባቱን ያስረዳሉ፡፡ ይሄ ደግሞ የሀረሪ ማህበረሰቦች ተደም ባሉት ጊዜያት ጭምር ስለ ቀለማት ያላቸውን እውቀት ይገልፃል፡፡

ገበታ በአሁኑ ሰአት በትርስትት በሙዚየም እና አንዳንድ ትልልቅ ሰዎች ቤት ብቻ የሚገኝ ቁስ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም የገበታውን አገልግሎት በርካሽ እና በስፋት የፋብሪካ እቃዎች ስለተኩት መሆኑን ወ/ሮ ፈቲህ ገልፀውልኛል፡፡

ገበታ ለመመገቢያነት እና ለጌጥነት የሚያገለግል ቁስ ሲሆን መጠኑም የተለያየ ነው፡፡ በርከት ያለ የሰው ቁጥር ባለበት ቦታ ትልቁ ገበታ ላይ ምግቡ ተዘጋጅቶ ይቀርባል፡፡ አንድ ወይም ሁለት ሰው ብቻ ከሆኑ ደግሞ አነስ አነስ ተደርገው የተዘጋጁ ገበታዎች ስላሉ በነሱ እንዲመገቡ ይደረጋል፡፡

ማህበራዊ ፋይዳ፡- ገበታ በሀረሪዎች ዘንድ ለሠርግና ለሀዘን ጊዜ ለመመገቢያነት ከሚውሉት ቁሶች ውስጥ ተጠቃሽ ቁስ ነው፡፡ ወ/ሮ ፈቲህ ስለ ገበታ አገልግሎት የሚከተለውን ገልፀዋል፡፡ “አገልግሎቱ መብያ ነው፡፡...ትንንሹን አንድና ሁለት ሰው ይመገቡበታል፡፡ በሰርግና በሀዘን ላይ ትልልቁን ይጠቀማሉ፡፡ ለማቡኪያም ስለሚጠቀሙበት ያው እንደየ ሁኔታው ነው (ፈቲህ፣ 2004፣ ጥር፣19) በማለት ተናግረዋል፡፡

### 5.4.2 ጭልፋ



አንድ ቄስ ስያሜ ሲወጣለት ካለው ባህሪይ ጋር በማያያዝ አሊያም ከሚሰጠው አገልግሎት አንፃር ይሰየማል፡፡ ጭልፋ የተባለው ቄስ ስያሜውን ያገኘው ከሚሰጠው አገልግሎት በመነሳት ነው፡፡ አንዳንዶቹ በሀረሪ ቋንቋ የሚነገሩ ቃላት ከአማርኛ ቃላት ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ይህ ደግሞ በቀዳሚው ክፍል ላይ እንደገለፅኩት ሁለቱ ቋንቋዎች አንድየቋንቋ ቤተሰብ ውጥ የሚገኙ በመሆናቸው ግርሊለን አይገባም፡፡በመሆኑም ጭልፋ የሚለውንቃል ሁለቱም (አማርኛ እና ሀረሪ) ቋንቋዎች ተመሳሳይ አገልግሎት ለሚሰጥ ቄስ የሰጡት ስያሜ ነው፡፡

ስለዚህ ጉዳይ ወይዘሮ ፈቲሀ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡ "የትልልቅ ድስት መጨለፊያ ስለሆነ የድስቱ ሙቀት ሰውን እንዳያቃጥል ነው (ረጅም የሆነው) አጠር ካለ ትልቅ ድስት ውስጥ ሲገባ ሙቀቱ ስለሚያቃጥል ለዛ ነው እንደዛ ያደረጉት" (ፈቲሀ፣ ጥር፣ 2004፣21)፡፡

የጭልፋ አሰራር ከእንጨት እንደሚሰሩት ሌሎች ቁሶች ከዋንዛ እንጨት ይዘጋጃል፡፡ ዋንዛ የተመረጠበት ምክንያት በዝግጅት ወቅት ተፈላጊውን ቅርፅ ለማስያዝ በሚጠረብበት ጊዜ እየተሰባበረ ስለማያስቸግር እና ቁሱ ተሰናድቶ ካለቀ በኋላ በጣም ረጅም ለሚባሉ አመታት ሳይሰነጠቅ መቆየት ስለሚችል ነው፡፡ ለጭልፋ አሰራር ዝርዝር ሂደት ገበታ በተባለው ቁስ ትንተና ላይ ስለቀረበ ከዛ መመልከት ይቻላል፡፡

የጭልፋ አገልግሎት የተለያዩ ነገሮችን ከአንድ እቃ ውስጥ ወደ ሌላ እቃ ማሸጋገር ሲፈለግ ለመጨለፊያነት ነው፡፡የሚጨለፉት ነገሮች ወጥ፣ ንፍሮ፣ ቂንጬ፣ሾርባ ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ የተጠቀሱት ተጨላፊ ነገሮች እንደየ ዝግጅቱ መጠን አንዳንዴ በርከት ተደርገው ይዘጋጃሉ፤ አንዳንዴ ደግሞ አንስተኛ ሆነው ይዘጋጃሉ፡፡ የተጨላፊዎቹ ነገሮች ማነስና መብዛት የጭልፋውን መጠን ይወስነዋል፡፡ ለምሳሌ በሰርግ እና በሀዘን ላይ የሚዘጋጁ ወጦች በጣም ትልልቅ በሆኑ ድስቶች ይሰራሉ፡፡ በነዚህ ድስቶች ውስጥ ያለውን ወጥ ለመጨለፊያነት የሚያስፈልገው ትልቅና መያዣው ረዘም ያለ ጭልፋ ነው፡፡ በመሆኑም ሀረሪዎች ጭልፋዎችን ሲያዘጋጁ ይህንን ጉዳይ በማጤን የተለያየ መጠን ያላቸው ጭልፋዎችን ያዘጋጃሉ፡፡

### 5.4.3. ሺብሪያ (ወንበር)



የወንበር አሰራርከዋንዛ እንጨት የቀድሞ አባቶች ዛፍን በመቁረጥና በመጥረብ የሚያዘጋጁት ብዙ ጥበብ የማይፈልግ ቁስ ነው፡፡ ስለወንበር አሰራር አቶ ኢድሪስ እንዲህ በለማት ይገልፃሉ፡፡ "እርሻ ዋንዛ አለ፡፡ እንዲህ እንደአሁኑ ምድረ በዳ ሳይሆን፡፡ በዛ በመጥረቢያ ይጠረባል፡፡ ይህው እስካሁን አለ ይሄ ወንበር 200 (ሁለት መቶ) አመት ያስቆጠረ ጥንታዊ ወንበር ነው (ኢድሪስ፤የካቲት፣ 2004፤49)፡፡

ወንበር በሀረሪዎች ዘንድ በቀድሞ ጊዜ ለእናቶች መቀመጫነት የሚያገለግል ቁስ ነበር፡፡ የወንበር አገልግሎት በቤት ውስጥ እናቶች ለሚያከናውኑት ተደራራቢ ስራ ወገባቸውን አረፍ በማድረግ ጉልበታቸውን ሰብስብ አድረገው የእለት ተግባራቸውን እንዲወጡ ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ ኢድሪስ የሚከተለውን ገለፃ ሰጥተዋል፡፡ "እናቶቻችን በማድቤት ውስጥ ቁጭ ብለው ወጥ ሲሰሩ እንጀራ ሲጋገሩ የሚጠቀሙበት ነው፡፡ የሚሰራውም ከዋንዛ እንጨት ነው፡፡ ብል አይበላውም፣ ጠንካራ ነው፣ ለአደጋ አይጋለጥም፡፡ በቤት ውስጥ እንኳን ቢቀበር ምስጥ አይበላውም (ኢድሪስ፤የካቲት፣ 2004፣ 49)፡፡ በማለት የወንበርን ጥንካሬ እና የሚዘጋጅበትም ጥሬ ነገር ዛሬ ለያዘው እድሜ ያለውን ጉልህ ሚና አስረድተዋል፡፡

ይህ በፎቶ ላይ የምናየው ወንበር በቀደሙ አባቶች የተዘጋጀ መሆኑንና የአሁኑም ትውልድ ይህንን ቁስበከብር መዝገቦ በመያዝ በቅርስነት እየተንከባከበው መገኘቱን ነው፡፡ ቁሱ ተራ እቃ ቢሆን ኖሮ እንክብካቤ ተደርጎለት ይህን ሁሉ ዘመን ማስቆጠር ባልቻለ ነበር፡፡የወንበር ማህበራዊ ፋይዳ እናቶች በቤታቸው ውስጥና በትልልቅ ድግሶች ላይ ምግብ ሲያዘጋጁ በማዕድ ቤት ውስጥ ለመቀመጫነት የሚያገለግላቸው ቁስ ነው፡፡

## 6. በመገልገያ ቁሶቹ ላይ ያለ ለውጥ

ይህ ክፍል በቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶቹ ላይ ለውጥ አለወይ? ካለ ምን አይነት ለውጥ ነው? ለውጥ እንዲከሰት ያደረጉ ምክንያቶች ምንድ ናቸው?

በምዕራፉ ቀዳማይ ክፍሎች አንዳንድ ቁሶች በስልጣኔ እና በሌሎች ችግሮች ምክንያት እየጠፉ መሆናቸውን እና ሙዚየም ውስጥ ብቻ የተገኙ ቁሶችም እንዳሉ፣ መጠነኛ ለውጥ

የተደረገባቸው ቁሶች መኖራቸውን እና ሙሉበሙሉ የተቀየሩ ቁሶች መኖራቸው ተጠቁሟል፡፡

የተጠቀሱት ቁሶች አገልግሎት ላይ እንዳይውሉ ያገዳቸው ነገር ቴክኖሎጂ ያፈራቸው የሆኑ ቁሳቁሶች በገበያ ላይ ከባህላዊ ቁሶቹ በርካሽ ዋጋ መገኘታቸው፣ ባህላዊ ቁሶቹን ገበያ ላይ እንደልብ አለማግኘት፣ የባህላዊ ቁሶቹ ዋጋ ውድ መሆናቸውተደማምሮ ተገልጋዩ ማህበረሰብ ሌላ አማራጭ እንዲፈልግ ያስገደዱ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

እነዚህ ሀገረሰባዊ ቁሶች ለዘመናት የሀረሪ ማህበረሰቦች የአእምሮና የእጅ የፈጠራ ውጤት አርፎባቸዋል፡፡ ነገር ግን ዛሬ ላይ ሆነን ስናስተውል ቀድሞ በነበራቸው ሚና በማህበረሰቡ ውስጥ ሊዘልቁ አልቻሉም፡፡ ምንም እንኳን የማህበረሰቡ መገለጫዎች ቢሆኑም ቀድሞም ማህበረሰቡ ሲፈጥራቸው ህይወትን ቀላልና ምቹ እንዲያደርጉለት በማሰብ መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ ዛሬ ላይ ከነዚህ ቁሶች በተሻለ ዋጋ እና ግልጋሎት ሊጠቀምባቸው የሚያስችሉት ቁሳቁሶችን ሲያገኝ ባህል ናቸውና መተው የለባቸውም በማለት ሙጥኝ ሊል አይችልም፡፡ ማድረግ የሚቻለው ወ/ሮ ፈቲሀ እንዳሉት ቀርሶ ማስቀመጥ ነው፡፡

### 6.1 መጠነኛ ለውጥ የተደረገባቸው ቁሶች

የስፌት ስራዎች በትንታኔው እንደተገለፀው ከአክርማ፣ ቀርማ እና አለላ የሚሰፉ ስፌቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን በተጠቀሱት ጥሬ ቁሶች ስፌቶቹ በሚሰፉበት ሂደት የሚወስደው ጊዜ ጉልበት እና ወጪ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ለመከላከል ሲባል አለላዎቹን እና ቀርማውን በክር እየተኩ የሚሰፉ አንዳንድ ሰዎች እና ማህበራት አሉ፡፡ ወ/ሮ ከዲጃ የተባሉ መረጃ አቀባይ በክር፣ በአለላና ቀርማ


የተሰሩ ብዙ ስፌቶችን አይቼ  ስለክሩ ስፌት ማብራሪያ በጠየቅኋቸው ወቅት የሰጡኝ ገለፃ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

*በፈትል ነው የሚሰራው ክር ከመጣ ወዲህ በአክርማ የሚሰራውን በክር አደረግነው፡፡ ክሩን መርፌ ውስጥ ከተን በሰበዝ አድርገን እንሰፋዋለን፡፡ ዘመኑ ያንን ተወና የሳሩን ክር በመርፌ እየተጨመረ በቀላሉ መስፋት ተጀመረ፡፡ የበፊቱን (የአለላና ቀርማውን) በማየት ከለሩንና ጥበቡን አንድ አይነት አድርገን እንሰራዋለን (ከዲጃ፣ ጥር 2004፣37)፡፡*

ከወ/ሮ ከዲጃ ገለፃ የምንረዳው ስፌቱ በክር ሲሆን አክርማ መሰንጠቅ ፣ አለላ መንከር ወዘተ. አይኖርም ይሄ ጊዜን ይቆጥባል፡፡ ሲሰፋም በየቀለማቱ እንደየ አስፈላጊነቱ ክሩን በመርፌ እየጨመሩ መስፋት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ስራው በጣም ቀላል ነው፤ ጊዜን ይቆጥባል፡፡ በመሆኑም ስሪዎቹ ከአክርማው ይልቅ የክሩን ስፌት መስፋት ይቀላቸዋል፡፡

በሽያጭ ላይ ከክር የተሰራው ስፌት እና በአለላ የተሰራው ስፌት ከፍተኛ ልዩነት አላቸው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሚህካክ እና ወስከምባይ የአለላው ሰባት ሺህ ብር ሲሆን የክሩ አምስት ሺህ ብር ነው፡፡ በንጥረ ቁሱ መለያየት ምክንያት በቁሱ የሁለት ሺህ ብር የዋጋ ልዩነት ተፈጥሯል፡፡ በዚህም ምክንያት ተጠቃሚው ህብረተሰብም ዋጋው ወደሚቀንሰው ቁስ ማዘንበሉ የማይቀር ቢሆንም በመስክ ቆይታዬ እንዳረጋገጥኩት በሁሉቱም ጥሬ እቃዎች የሚሰሩት ቁሶች እኩል ፈላጊ እንዳላቸው አረጋግጫለሁ፡፡ ይሄም የሆነበት ምክንያት ለጥሎሽ የሚውሉት

ስፌቶች በሙሉ በአለላና በቀርማ የተሰፉ መሆን ስላለባቸው የክሩን ለጥሎሽ የሚገዛ ሰው ባለመኖሩ የአለላው ውድ ቢሆንም ፈላጊ አለው፡፡



በከፊል ለውጥ የተደረገበት ሚህካከና ወስከምባይ

## 6.2 ሙሉ በሙሉ ለውጥ የተደረገባቸው ቁሶች

በሀረሪ ማህበረሰብ የሚሰፉት ስፌቶች ቀልብን የመግዛት አቅማቸው የመነጨው ከቁሶቹ ላይ ያረፉት ዲዛይኖች እና ቀለማት ስብጥር መሆኑ የተረጋገጠ ነው፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ወጣት ወንዶች ቅርፁን ብቻ በመውሰድ ዲዛይንና ቀለማቱን በሙተው የከፋይ ወርቆች፣ ካርቶን እና ወሌዎች በመጠቀም ቁሶቹን ባዲስ ማምረት ጀምረዋል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ አቶ ጃሚ የተባሉ ወጣት የገለፁልኝ ሀሳብ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

> *... ድሮ ያረጁ ስፌቶች ጎፍተ ሙዳዮች/በከፋዩ (ጥቁር ከፋይ) እና ወሊ ገዝተን እናሳምረዋለን፡፡ አሁን እሱ (ያረጀው ስፌት) ሲጠፋ በካርቶን ለራሳችን ፈጥረን በማስቲሽ በሆር ከፋይ በጥቁር፣ በቀይ፣ በቢጫ እየሰራን በወሊ አሸብርቀነው ለገበያ እንሸጠዋለን... በስፌት ብቻ የሚሰፋው ሴቶች ሚያጊያጌጡበትን ጉፍታ የሚባል አለ እሱ ይቀመጥበት ነበር፡፡ ይህ እኛ የምንሰራው ግን ስለማይከፈት ለጌጥ ብቻ ያገለግላል፡፡ ውስጡ ካርቶን ነው፡፡ ስለዚህ አያይዘን እንሰፋዋለን፡፡ ውስጡ ስለማይከፈት እንደ ጉፍታ ሙዳይ አያገለግልም፡፡ ለጌጥ ግን ያገለግላል፡፡ ቅርፁን ያገኘው ከጉፍታ ሙዳይ ነው (የካቲት፣ 2004፣ ጃሚ፣ ጥር 2004፣32)፡፡*

አዲሶቹ ቁሶቹ ከቀድሞዎቹ ቁሶቹ ቅርፅ ብቻ ነው የሚጋሩት፡፡ አገልግሎታቸውም ከአክርማና አለላ እንደሚሰሩት ቁሶች ሁለት አይደለም፡፡ ቁሶቹ ለጌጥነት ብቻ የሚውሉ ናቸው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት አዲሶቹን ቁሶች ለመስራት በግብአትነር የሚጠቀሙት ጥሬ ቁስ ካርቶኒና ጨርቅ በመሆኑ ተፈላጊውን የቤት ውስጥ አገልግሎት ሊሰጡ አይችሉም፡፡

እነዚህ ቁሶች ጥሬ እቃዎቻቸው በጣም በርካሽ የሚገኙ፣ ባጭር ጊዜ ውስጥ የሚሰሩና ሞያውንም ለመልመድ ከባድ ሂደት የሌላቸው በመሆናቸው ገበያ ላይ በሚወጡበት ጊዜ ርካሽ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንድ ጉፍታ ሙዳይ በ80 ብር ከገበያ ላይ መግዛት እንደሚቻል መረጃ አቀባዬ ገልፀውልኛል፡፡ ይሄ መሆኑ ደግሞ ቤታቸውን ማስጌጥ ፈልገው የአቅም ውሱንነት ለገደባቸው የማህበረሰቡ አባላት ጥሩ አማራጭ ስለሚፈጥርላቸው በአዲስ መልክ የተሰሩትን ቁሶች በመግዛት ለቤታቸው ማጌጫነት ይገለገሉባቸዋል፡፡


## ለውጥ የተደረገባቸውን ቁሶችን የሚያሳ ፎቶ



ጉፍተሙዳይ



ኡፋ



ሳህናሲጋሪ



ሳንቡሳ

# 7.ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳቦች

በጥናቱ ውስጥ በቀዳሚዎቹ ምእራፎች የተነሱ ቁም ነገሮች በዚህ ምዕራፍ ማጠቃለያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

## 7.1 ማጠቃለያ

አስቀድሞ በመግቢያው እንደተገለፀው የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋና አላማ የሀረሪ ማህበረሰብ ባህላዊ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ላይ ገለፃዊ ትንተና ማድረግ ነው፡፡ ይህንንም ለማሳካት ቁሶቹን፣ የቁሶቹን ተግባር፣ የቁሶቹን አሰራር፣ ባለሙያዎቹን፣ በቁሱና በባለቤት ማህበረሰብ መካከል ያለውን ቁርኝት፣ በቁሶቹ ላይ የተደረገ ለውጥ ማሳየት የሚያስችሉ ንኡሳን አላማዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

የተነደፈውን አላማ ከግብ ለማድረስ በተለያዩ መንገዶች መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ እነሱም ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት ናቸው፡፡ መረጃ መሰብሰቢያ መንገዶቹን በማዛነቅ የመረጃ ክፍተት እንዳይከሰት ጥረት ተደርጓል፡፡ መረጃዎቹ በምዕራፍ ሁለት በቀረቡት ትውሮች መሰረትነት ተተንትነዋል፡፡ የትንተናው ውጤት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

የተሰበሰቡት መረጃዎች በሙሉ ትንተና አልተደረገባቸውም፡፡ትንተና የተደረገባቸው በናሙናነት የተመረጡት ቁሶች ናቸው፡፡ ቁሶቹ በአራት ወገን ከተሰሩበት ንጥረ ቁስ አንፃር ተወግነዋል፡፡ እነርሱም የሰፌት ቁሶች፣ የሸክላቁሶች፣ ከእንጨት የተሰሩ ቁሶች እና ከቅል የተሰሩ ቁሶች ናቸው፡፡ ትንተና የተደረገባቸው ቁሶች ከሰፌት የተሰሩ 6፣ ከሸክላ የተሰሩ 4፣ ከእንጨት የተሰሩ 3 እና ከቅል የተሰሩ 2 ናቸው፡፡

እነዚህ ትንተና የተደረገባቸው ቁሶች ከቤት ውስጥ መገልገያና ማጌጫነት ባሻገር ተምሳሌታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እናማህበረ ባህላዊ ፋይዳ አላቸው፡፡ አብዛኞቹ ቁሶች ባለቤት ማህበረሰቡን የሚገልፁበት ትዕምርት ተሸክመዋል፡፡ በመሆኑም ቁሶቹ ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸው ቁርኝት ከፍተኛ ነው፡፡

የሀረሪ ማህበረሰብ በጥናቱ የተተነተኑትን ናሙና ቁሶች በቤት ውስጥ ሲገለገሉባቸው ቁሶቹ በዋናነት ከተሰሩበት ተግባር ባለፈ ለቤት ውስጥ ማጌጫነት በግርግዳ ላይ በመስቀል

የቤቱን ውበት እያደመቁ የሚያስተላልፉት በርካታ ትርጉም እንዲይዙ የተደረጉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውሉ፣ ማንነትን የሚገልፁ፣ ባለቤቱን የሚጠቁሙ፣ ሁነቶችን የሚገልፁ ወዘተ ናቸው፡፡

ማህበረሰቡ በቁሶቹ ተናጋሪነት የሚያስተላልፈው በርካታ መልዕክት አለው፡፡ አንዲት ያገባች ሴት በመጀመሪያው የትዳር ዘመኗ ሳንቡሳ የተባለውን ቁስ ትሰቅላለች ይሄም ገና አልወለድኩም የሚል መልዕክት አለው፡፡ ስትወልድ ሰጋሪ መስከምባይ ሰፍታ ትሰቅላለች፡፡ የዚህ ቁስ መስቀል ወልጃለሁ የሚል መልእክት አለው፡፡ ይቺ እማወራ ልጆቿን አሣድጋ ለወግ ማእረግ ስታበቃ በቤቷ ውስጥ አንድ ሃማትሞት ካላት አንድ ያገባ ወንድ ልጅ አላት ማለት ነው፡፡ የሀማትሞቱ ቁጥር እማወራዋ የዳረቻቸውን ወንዶች ልጆች ብዛት ጠቋሚ ነው፡፡ ይቺው እማወራ አፍላል እና ኡፋውን አካድና በትክክል ካስቀመጠች ባሏ በህይወት አለ ማለት ነው፡፡ የአፍላሉን ክዳን ብትዘቀዝቀው ደግሞ ባለቤቷ ሞቷል የሚል መልዕክት አለው፡፡

በስፌቶቹ ላይ የሚያርፉት ዲዛይኖች ከ11 በላይ ናቸው፡፡እያንዳንዳቸው መጠሪያ ስም አላቸው፡፡ በስፌቶቹ ላይ የሚያርፈው ዲዛይን የሰፊዋን የሞያ ደረጃ ይጠቁማል፡፡ ዲዛይኖቹ ለቁሶቹ ስያሜ ወሳኝ ጉዳይ ናቸው፡፡ በዲዛይኖቹ ጥበብ መካን ከልጅነት እስከ ጎልማሳነት ባለ የለመዳ ሂደት ከቀን ወደ ቀን በተግባር እያደገ የሚመጣ ነው፡፡

በእንጨት ከሚሰሩት ቁሶች በስተቀር ቁሶቹ ሙሉበሙሉ የሚሰሩት በሴቶች ነው፡፡ ወንዶች ምንም አይነት ተሳትፎ አያደርጉም፡፡ ሴቶቹም ይሄንን ተግባራቸውን አምነውበትና የሴት ስራ ነው ብለው ተቀብለውታል፡፡ ከቁሶቹ ውስጥ በተለይ የስፌት ስራ ከልጅነት ጀምሮ እስከ እርጅና ድረስ የሚለመድ ሲሆንተወዳጅና አስደናቂ ጥበብ እና ችሎታ የሚታይበት የሞያ ዘርፍ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ለእጅ ባለሙያዎች በተለይም በሰፌት ስራ ላይ ለተሰማሩ ሴቶች ያለው ከበሬታ ከፍተኛ ነው፡፡ እንደሌሎች ማህበረሰቦች ሞያውን የማናናቅ እና ሙያተኞቹንም የማግለል ተግባር አይታይባቸውም፡፡

ቁሶቹ ባሁኑ ሰአት ለውጥ እየተከሰተባቸው ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ የስፌት ቁስ በክር እና በከፋይ ጨርቅ እየተሰራ ለገበያ መቅረብ ጀምሯል፡፡ የሳሮቹ ስፌቶች ዋጋቸው በጣም ውድ በመሆኑ አቅሙ የሌላቸው ሰዎች በተቀየረው ቁስ እየተገለገሉ ይገኛሉ፡፡ በናሙና

የተመረጡት ቁሶችን የSchelerethን ዘጠኝ ሞዴሎች፣የPrown እና የFlemingን የትንተና ሂደቶች በማዛነቅ ጥናቱ ለማናበቢያነት ተጠቅሞባቸዋል፡፡

## 7.2 የይሁንታ ሀሳቦች

በአጠቃላይ በጥናቱ እንደቀረበው የተተነተኑት ቁሶች ቤትን ለማስጌጥ፣ ገቢ ለማስገኘት፣ ለቱሪስት መስህብነት እና ለተምሳሌታዊ ተግባር የሚውሉ ናቸው፡፡ ይህ ተግባራቸው ቁሶቹ ከማህበረሰቡ ጋር እንዲቆራኙና እንዲዘልቁ ያደርጋቸዋል፡፡ በመሆኑም ቁሶቹ ቀጣይነት እንዲኖራቸውና የአገልግሎት አድማሳቸው እንዲሰፋ የይሁንታ ሀሳቦችን እንደሚከተለው ጠቁሜያለሁ፡፡

- የአለላ ስራየሚለመድበት መንገድ በጣም ረጅም እና በግለሰቦች መልካም ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የአለላ ስራ ለመዳ ረቀቅ ያለ ጥበብ ስላለው ማሰልጠኛ ተቋም ቢዘጋጅለት ፣ በሞያና ቴክኒክ ስር ተካተው እንደሚቀሰሙት (የሴንጀር፣ የዳንቴል) ወዘተ. ክህሎቶች የለመዳ ሂደቱ መደበኛ ቢሆን የክህሎት ሽግግሩ አደጋ ላይ እንዳይወድቅ እና በአጭር ጊዜ የክህሎቱ ባለቤት እንዲሆኑ ያግዛል፡፡
- የአለላ ስራዎች ዋጋ በጣም የናረው የመስሪያ ንጥረ ቁሶቹ ራቅ ካለ ቦታ መምጣትና የዋጋቸው መወደድ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሳሮች በአካባቢው የተለየ ቦታ በማዘጋጀት እንዲመረቱ ቢደረግ የሳሮቹ ዋጋ ስለሚቀንስ የስፌቶቹም ዋጋ ይቀንሳል፡፡ ዋጋው በሚቀንስበት ጊዜ ለውጥ ተደርጎባቸ በርካሽ የቀረቡትን ቁሶች ከመግዛት ይልቅ ባህላዊ የሆነውን ቁስ ለመግዛት አቅማቸው ይፈቅዳል፡፡
- የአለላ ስራለቱሪስት መስህብ ከሆኑት ቁሶች መካከል ግንባር ቀደም ነው፡፡ በመሆኑም ወደ ሀረር የሚመጡ በርካታ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች የስፌት ቁሶቹን ይገዛሉ፡፡ ስለሆነም ይህ ተወዳጅ የሆነ ቁስ በሀረር ከተማ ብቻ ተወስኖ እንዳይቀር በየከተማዎቹ የመሸጫ ማእከል በማቋቋም ሁሉምጋ እንዲዳረስ ቢደረግ ለባለሙያዎቹም ሆነ ለሀገራችን ገቢ ሊያመጣ የሚችል ቁስ ነው፡፡
- የክልሉ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ኘሮግራሞች በቁሳዊ ባህሎች ዙሪያ የሚያጠነጥን ኘሮግራም ቢሰሩና፣ ቁሶቹን ለማያውቃቸው ማህበረሰብ ቢያስተዋውቁ ብዙዎችን በመሳብ ተጠቃሚ መሆን ይቻላል፡፡

# ዋቢ መፃህፍትና ፅሁፎች

## I. የአማርኛ ምንጮች

ሀብታሙ እንግዳው፣ "በደቡብ ጎንደር ዞን በሊቦከምከም ወረዳ በሸሞጎድጓዲት ገጠር ቀበሌ የሻሞ መድሃኒአለም ሸክላ ስራ ውጤቶች የአሰራር ሂደትና ጠቀሜታ ትንተና"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2001 ዓ.ም፡፡

ሀኒም ይስሐቅ፣ "የአደሬ ብሔረሰብ የልጆች ግጥም"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1974 ዓ.ም፡፡

ሂለን አላምረው፣ "ባህላዊ ሽመናና ቆዳ ስራ በደንበጫና አካባቢዋ"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያቋንቋዎችናሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1999ዓ.ም፡፡

ሐረር ብሔራዊ ጉባኤ፡፡ *የሀረሪ አመፅ፡፡* አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተር ፕራይዝ፣ 1992 ዓ.ም፡፡

ራሄል እንዳለው፣ "የአኝዋ ብሔረሰብ የባህላዊ ምግቦችና መጠጦች አዘገጃጀትና አቀራረብ ስነ ስርአት"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2000 ዓ.ም፡፡

ሰይድ ይማም፣ "በከሚሴ ከተማ ዙሪያ የሚገኙ ገጠር አካባቢዎች ወጣት ወንዶችና ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያቋንቋዎችናሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2002 ዓ.ም፡፡

በዙ እሸቱ፣ "የአባድር ትውፊት"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረ፣ 1980 ዓ.ም፡፡

በላይነህ አሰጉ፣ "ስለ ቅርስ አንዳንድ ነጥቦች"፣ መስከረም፣ ቅፅ 9፣ ቁጥር 38፣ ሰኔ፣ 1981፣ ገፅ 8፡፡

ብርሃነ ትንሳኤ ወ/ሰንበት፤ "የሸማኔና የማእድቤት እቃዎች"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1983፡፡

ተሾመ ወ/ማርያም፣ "በአደሬኛ ተረትና ምሳሌዎች"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1973 ዓ.ም፡፡

ተሾመ ፎርሲዶ፡፡ "ባህላዊ የቤት እቃዎችና የእርሻ ማሳሪያዎች ስያሜ በሀዲያ ብሔረሰብ"፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ የባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1993 ዓ.ም፡፡

አህመድ ዘካሪያና ግርማ አውግቸው ደመቀ፡፡ *አባድር ሀረሪ ለጀማሪዎች፡፡* አዲስ አበባ፣ ፋር.ኢስት. ትሬድይንግ ኃላ.የተ.የግ ማህበር፣ 2003 ዓ.ም፡፡

አለማየሁ እንግዳ፤ "የአደሬ ሰርግ"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለቲአትሪካል አርት ክፍለ ትምህርት የቀረበ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ 1981 ዓ.ም፡፡

አስቴር ሙሉ፣ "ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2000 ዓ.ም፡፡

አበበ መርዕድ፣ "በጎባ ወረዳ የኦሮሞ ብሔረሰብ የመመገቢያ ቁሳቁስ አሰራር አገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ትንተና"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2000 ዓ.ም፡፡

አብይ አስማማው፣ "የአርጎባ ብሔረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች በአማራ ክልል በደቡብ ወሎ ዞን አርጎባ ልዩ ወረዳ"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2000 ዓ.ም፡፡

አብዱላሂ ሼኽ አህመድ ሙህ፡፡ *የሐረር ከተማ ታሪክ፡፡* ድሬዳዋ፣ ኧላፍ ማተሚያ ቤት፣ 1998 ዓ.ም፡፡

አብይ አክሊሉ፤ "የክስታኒ ብሔረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁስ ጥናት"፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2004 ዓ.ም፡፡

አብዲ ተማም፤ "የባህላዊ ምግብ አዘገጃጀት በስልጤ ብሔረሰብ"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2003 ዓ.ም

አያል አድማሱ፤ "የጎጃም አካባቢ ያልባሳት ስያሜ"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1992 ዓ.ም፡፡

ኤልያስ ደሳለኝ፣ “የሐረሪ ብሔረሰብ ሀገረሰባዊ መድሃኒት”፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2000 ዓ.ም፡፡

ዚነት አብዱ ረሻድ፣ “የሐረሪ ተረቶች ስብስብና ትንተና”፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1992 ዓ.ም፡፡

ዋልተንጉስ መኮንን፤ "የሽመናና የጥል ትውፊት በአክሱም"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2000 ዓ.ም፡፡

ዉብሸት አሰፋ፤ "የወይዛዝርት አልባሳትና ጌጣጌጥ ስሞች በአማራው ባህል"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1978 ዓ.ም፡፡

ገብረ ሥላሴ ወ/አረጋይ፡፡ *ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሰ ነገሥት ዘኢትዮጵያ*፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1959 ዓ.ም፡፡

ጌታቸው ግርማ፤ "የአልባሳትና ጌጣጌጥ ስያሜ በ “ራያ”፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1980 ዓ.ም፡፡

ደግሰው ጥላሁን፣ “ባህላዊ የሽክላና የቆዳ ስራ በቡሬ እና ወንበርማ ወረዳ”፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2003 ዓ.ም፡፡

ያሬድ ተፈራ፤ "በሰቆጣና አበርገሌ ገጠራማ ወረዳዎች የሴቶችና የወንዶች የአለባበስና ያጊያጊያጥ ማህበራዊ እሴቶች"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2002 ዓ.ም ፡፡

የኔአለም አረዶ፤ "የሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ጥናት በኮኮሳና ገደብ ሀሠሣ ወረዳዎች"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 2000 ዓ.ም፡፡

ፀዳለ ካሳ፤ "የአደሬ ብሔረሰብ የሰርግ ስርአት የዘፈን ጥግሞች"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ 1983 ዓ.ም፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ *የስነ ቃል መምሪያ፡፡* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ 1991 ዓ.ም፡፡

II. የእንግሊዝኛ ምንጮች

A Azime A. Hassen. "A Need for Establishing Fund Accounting System in the Municipality of Harar', Ethiopian Civil ServiceCollege, Submitted to Accounting Department, 2000 E.C.

A Muheimen A. Nasser, "Discover Harar', 2001 E.C.

Ames, L. Kenneth, “Meaning in artifacts: Hall Furnishings in Victoria American.” *In Journal of interdisciplinary history;* Vol IX; No. 1, pp. 19-46; 1978.

Bartis, Peter. *Folk life and Fieldwork: Alayman’s introduction to field techniques.* Washington; Library of congress. 2002.

Belle Asante. Women's craft Guiilds and the traditional Basketry (GEMOT) of Harar, Ethiopia. 2005.

Dorson, Richard M. “Introduction: concepts folklore and folk life studies in Riachard Dorson. (ed). *Folklore and folk life; an introduction.*Chicago and London: the University of Chicago press. 1972.

Elisabeth- Dorothea Hecht. Harari Basketry. 1992.

Fleming, E. Mcclung. “Artifact study; A proposed moded.” On line at; URL:http://www.stor.org/stable/1180572.1974. accessed date 07/06/2012.

Glassie, Henry. *Material Culture.*Chicago and London: the University of Chicago press. 1999.

Goldstein, Kenneth S. A *Guide for field works in folklore.* Hatboro pennsyluania: the American folklore society, folklore associates I.N.C. 1964.

Jones. Michael Owen. “Concepts and perspectives in folk art and material culture” *hand book of American folklore.* Blooming on. Indian university press. 1972.

Pankhurst, Ricahrd. *“The old time handicrafts of Ethiopia”* Ethiopian observer. Published in Ethiopia and Britian. Vol. viii No. 3, 1964; 221-241.

Prown, David. Jules. “Mind in matter: An introduction to material culture theory and method” on line. Available at: http://www. Jstor. org/uc press.htm1.1982.

Richard and Rita Pankhurst. “History and the art published in Ethiopia and Britain.” Ethiopian observer (joruanl of independent opinion. Economic, History and the art. Publishedin Ethiopia. Vol. vIII. No 3. 1964.

Roberts Warren. "Field work: recording material culture.' In *folklore and folklife: an introduction.* Dorson, M Richard. (ed). Chicago and London: the University of Chicago press. 1972.

Roberts, Warren. E. Material cuitlure: Folk craft in Richard dorson (ed.),*folk lore and folklife an introduction.* Chicago and London. The University of Chcago Press, 1972.

Schlereth, J. Thomas. "Material culture research and historical explantion." Online, Available at: http://www.jstor.org/stable/33775481.1985

Silverman. *Tradtions of crativsity.* Seattle University of Washington Press, 1999.

http://wn.wikipedia.org/wiki/folklore.

http://wrightspottour.com/UNESCO_Registered-sites.htm.

http://www/rightspottour.com/unesco-registered-sites.html. Acssesdate 07-06-2012

http://www.stor.org/stable/1180572.1974. accessed date 07/06/2012.

ይህ ቴስስ (የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ) የኔ ወጥ ስራ ሲሆን ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩንቨርስቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም፡፡ ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎችም በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ገነት ሾሃኑር

ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ጥቅምት 2005 ዓ.ም

# አባሪ 1

## የአውራ መረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ሙሉ ስም | ፆታ | እድሜ | ብሔር | መኖሪያ አካባቢ | የስራ ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| ወ/ሮ ሶፊያ ኢብራሂም | ሴት | 70 | ሐረሪ | ሐረር ከተማ | የአለላ ስራ ባለሞያ |
| ወ/ሮ ኪሚያ አቡበከር | | 50 | ሐረሪ | ሐረር ከተማ | የአለላ ስራ ባለሞያ |
| ወ/ሮ ኪሚያ ዑመር | ሴት | 50 | ሐረሪ | ሐረር ከተማ | የአለላ ስራ ባለሞያ |
| ወ/ሮ አሚና አህመድ | | 40 | ሐረሪ | ሐረር ከተማ | የአለላ ስራ ባለሞያ |
| ወ/ሮ ፊቲሀ አህመድ | | 38 | ሐረሪ | ሐረር ከተማ | የሙዚየም አስጐብኚ |
| ወ/ሮ ዘቢዳ አብዱረህማን | | 40 | ሐረሪ | ሐረር ከተማ | የአለላ ስራ ባለሞያ |
| ወ/ሮ ቢፍቱ ዑመር | | 40 | ሐረሪ | ሐረር ከተማ | የአለላ ስራ ባለሞያ |
| አቶ ጃሚ ዑመር | ወንድ | 26 | ሐረሪ | ሐረር ከተማ | የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሰራተኛ |
| አቶ አብዱመሃይመን | ወንድ | 70 | ሐረሪ | ሐረር ከተማ | የሐገር ሽማግሌ |
| አቶ ኢድሪስ አብዲ | ወንድ | 48 | ሐረሪ | ሐረር ከተማ | የሙዝየም አስጐብኚ |

# አባሪ 2

## የአጋዥ መረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ሙሉ ስም | ፆታ | እድሜ | ብሔር | መኖሪያ አካባቢ | የስራ ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| አቶ ያሬድ ለማ | ወንድ | 35 | ኦሮሞ | ሐረር | ላቦራቶሪ ቴክኒሽያን |
| አቶ ተመስገን በላይ | ወንድ | 32 | አማራ | ሐረር | የጤና ባለሞያ |
| ረ/ፕሮፌሰር አህመድ ዘከሪያ | ወንድ | 50 | ሐረሪ | አዲስ አበባ | የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሙዚየም አስተባባሪ |

## የእጅ ባለሙያዎችን ለማወያየት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. የተሳታፊዎች ሙሉ ስም፣ ዕድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የቤተሰብ ብዛት፣ መተዳደሪያ መንገድ የመኖሪያ አካባቢ?
2. በእጅ ሙያው የተሰማራችሁት ከመቼ ጀምሮ ነው?
3. በሙያችሁ ተገልግላችሁ ምን ምን ቁሶችን ትሰራላችሁ?
4. የሙያው ባለቤት የሆናችሁት እንዴት ነው?
5. እንደ ጥበባቱን ለመስራት የምትጠቀሙዋቸው መሣሪያዎች ምን ምን ናቸው?
6. የእጅ ስራዎቹን ለመስራት የምትጠቀሚቸው ግብአቶች (ንጥረ ነገሮች) ምን ምን ናቸው?
7. ባህላዊ ቁሱ ለማህበረሰቡ ምን ማለት ነው?
8. ቁሳቁሶቹ ማህበረሰቡን እንዴት ይገልፁታል?
9. ለቁሶቹ የሚሰጠው ስም ምንን መሠረት ያደረገ ነው?
10. በአሁኑ ወቅት ባህላዊ ቁሶቹ ተጠቃሚ አላቸው?
11. ቁሶቹ ላይ ያረፈው ጥበብ አዘናነቅ ትዕምርቱ ምንድን ነው?
12. የምትሰሯቸው ቁሳቁሶች ዋጋ ስንት እንደሆነ በዝርዝር ብትገልፁልኝ?
13. ቁሳቁሶቹን ለመስራት ከምታወጡት ልዩ ልዩ ወጪዎች አንፃር ሸጣችሁ የምታገኙት ገቢ አዋጪ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
14. ተመሳሳይ ሙያ ያላችሁ ሰዎች ከአሁን በፊት ተደራጅታችሁ ታውቃላችሁ ከሆነ እንቅስቃሴያችሁ ምን ይመስላል? ካልሆነ ለምን?
15. ቁሶቹን በምትሰሩበት ወቅት የምትከተሉትን ሂደት ብትገልፁልኝ?
16. የአካባቢው ማህበረሰብ ለሙያችሁና ለእናንተ ያለው አመለካከት ምን አይነት ነው?
17. እናንተ ራሳችሁ ለሙያውና ለናንተ ያላችሁ አመለካከት ምን ይመስላል?

## የታሪክ አዋቂ የሀገር ሽማግሌዎችን ለማወያየት የተዘጋጁ ጥያቄዎች

1. የተሳታፊዎች ሙሉ ስም፣ ዕድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የቤተሰብ ብዛት፣ መተዳደሪያ መንገድ የመኖሪያ አካባቢ?
2. ከተማዋ እንዴት ሀረር ልትባል ቻለች አመሠራረቷ እንዴት ነበር? መቼ ተመሠረተች?
3. ሀረሪ የሚለው ስያሜ ምን ማለት ነው? ስያሜውን ማንና እንዴት ሰጠው?
4. የሀረሪ (አደሬ ) ብሔረሰብ ከአረብ ነው የመጣው የሚል አፈታሪክ አለ፡፡ ለዚህ ምን እውነታ አለ በናንተ አመለካከት?
5. የሀረሪ ብሔረሰብ ከአረብ ከመጣ መቼ ወደ ኢትዮጵያ መጣ?
6. በመጀመያ ወደ ኢትዮጵያ የገባው የሀረሪ ብሔረሰብ አባል ማን ይባላል?
7. የጀጎል ግንብ መቼ በነማን ለምን ተግባር ተሰራ?

V. ለክልሉ መስተዳድር ሃላፊዎችና ባህል ቢሮ ሠራተኞች የቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ

ስም ________________ ብሄር__________ በከተማው ያላቸው ቆይታ_______

የትውልድ ቦታ ______________ የእድገት ቦታ__________ የሥራ ድርሻ _____

ተጨማሪ የሥራ ድርሻ _________________

1. በሀረር ከተማ ምን ያህል ቀበሌዎች አሉ?
2. በሀረር ከተማ ውስጥ ያሉ ነዋሪዎች የሚተዳደሩት በምንድ ነው?
   - ሀ. ግብርና
   - ሐ. ሽመና
   - ሠ. የሸክላ ስራ
   - ለ. ንግድ
   - መ. ብረታብረት ሥራ
   - ረ. የስፌት ስራ
   - ሰ. ሌላ ካለ ይገለፅ ______________________________
3. ከእጅ ሙያ የሚገኘው ገቢ ለመተዳደሪያ በቂ ነው ብለው ያምናሉ?
4. የጥያቄ ሦስት መልስዎ አዎንታዊ ከሆነ የነዚህ ሰዎች ገቢ ለማሻሻል በክልሉ ምን የተለየ ድጋፍ ተደርጓል?
5. ድጋፍ ከተደረገላቸው ለምሳሌ ምን?
   - ሀ. የሙያ ማሻሻያ ስልጠና
   - መ. ገበያን ማመቻቸት
   - ለ. የገንዘብ ድጋፍ
   - ሠ. የማስተዋወቅ ስራ
   - ሐ. የእቃ አቅርቦት ማመቻቸት
   - ረ. ታታሪ ሰራተኞችን መሸለም
   - ሰ. ሌላ ካለ ይገለፅ ________________________
6. ድጋፍ ካልተደረገላቸው ምክንያቱ ይገለፅ፡፡
7. ክልሉ በመንግስት በጀትም ሆነ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ተባብሮ የእጅ ባለሙያዎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የመስራት ዕቅድ አለው ወይ?
8. የባህል እንዲሁም የቅርስ ጥትና ጥበቃ የተባለና ለዚሁ ተግባር የቆመ የስራ መደብ (ክፍል) በከተማው አለ?
9. ለጥያቄ ቁጥር 8 መልስዎ አለ ከሆነ እስካሁን ምንምን አበይት ስራዎችን አከናውኗል? የአሁኑ እንቅስቃሴውስ ምን ይመስላል?
10. በቀጣይ የብሔረሰቡን ባህል በተለይ ቁሳዊ ባህልን ለማስተዋወቅ ክልሉ ምን ዕቅድ ይዟል? የተጀመሩ ጅምሮች ካሉ ይገለፁ፡፡

10.ክልሉ የብሔረሰቡን ባህላዊ ቅርሶች የሚያከማችበት ቤተመዛግበት ወይም ሙዚየም አለው?

11.ቤተ-መዛግብት ካለው የስራ እንቅስቃሴው ምን ይመስላል? ያከማቸውስ ቁሶች ብዛት እንዴት ይገለፃል?

ሀ. በጣም ብዙ ለ. ብዙ ሐ. መጠነኛ

መ. ትንሽ ሠ. በጣም ትንሽ ረ. ምንም

12.የብሔረሰቡ ቁሳዊ ባህል በአሁኑ ወቅት በሚገባ ተለይቶና ተጠብቆ ይገኛል ብለው ያምናሉ?

13.ለጥያቄ ቁጥር 13 አሉታዊ ምላሽ ካለዎት ቁሳዊ ባህሎችን ለመለየትና ለመጠበቅ የሚደረጉ መንግስታዊ ጥረቶች (ለምሳሌ የምርምር ጥናቶች) በማነሳሳቱና ድጋፍ በማድረጉ ረገድ ምን እየተሰራ ነው?





ባለሙያዎች መረጃ ሲሰጡ



የባህላዊ ቁሶች መሸጫ መደብር



ወ/ሮ ዘቢዳ መረጃ ሲሰጡ